## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒትስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የጋብቻ ነውሮች በዳንግላ ወረዳ

በ

አይናዲስ ፍሬው

ሰኔ 2013 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒትስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የጋብቻ ነውሮች በዳንግላ ወረዳ

ለኤም. ኤ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ

አይናዲስ ፍሬው

አማካሪ

ዓለሙ ካሣዬ (ዶ/ር)

ሰኔ 2013

አዲስ አበባ

## የጋብቻ ነውሮች በዳንግላ ወረዳ


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒትስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

በ


አይናዲስ ፍሬው


የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ ------------------------------------------------ፊርማ------------------ ቀን------------

የውጭ ፈታኝ ------------------------------------------ፊርማ ------------- ቀን--------------

የውስጥ ፈታኝ-------------------------------------------ፊርማ--------------- ቀን------------

‹‹የጋብቻ ነውሮች በዳንግላ ወረዳ›› በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለኤም. ኤ. ዲግሪ ማሟያነት በሰኔ ወር 2013 ዓ.ም ያቀረብሁት ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ያሟላና የራሴ ወጥ ስራ መሆኑን በፊርማየ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ------------------------------------------------- ፊርማ ------------------------- ቀን --------------

# ምስጋና

ይህ ጥናት በአጭር ጊዜ እንዲጠናቀቅና አሁን ካለበት ደረጃ እንዲደርስ ገንቢ አስተያየትን ከትህትና ጋር ለሰጡኝ አማካሪየና አስተማሪየ ለሆኑት ለዶ/ር ዓለሙ ካሣዬ ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ በመረጃ ስብሰባ ወቅት መረጃውን በምፈልገው ልክ እንድሰበስብ የረዱኝን የባህልና ቱሪዝም ባለሙያ አቶ ባንቲገኝ ስሜነህን አመሰግናለሁ፡፡ መረጃ አቀባዮችን በመጠቆምና የቡድን ቃለ መጠይቅ ለማካሄድ ሰዎችን ላስተባበሩልኝ ለአቶ ድሉ ተፈራና ለአቶ ሙሉየለት እንየው ፈጣሪ አብዝቶ እድሜና ጤናን ይስጥልኝ፡፡

የትምህርት እድሉን ለሰጠኝ የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲንና የገንዘብ ድጋፍ ያደረገልኝን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ ጥናትሽ ምን ደረጃ ደረሰ እያልህ በሀሳብ ላልተለየኸኝና በየጊዜው ጠንካራ ሴት ሁኚ እያልህ ለምታበረታኝ ውድ አባቴ መርጌታ ፍሬው ምስጋናየ ይድረስህ፡፡

በመጨረሻም የጥናታዊ ፅሁፉን የፊደል ግድፈትና የቋንቋ አጠቃቀም ችግርን በማረም ለተባበረችኝ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህርት ለሆነችው ጓደኛየ እሴተ ታደለ ምስጋናየ ከልብ ነው፡፡ እንዲሁም ሁሌም ጥናትሽ ምን ደረጃ ላይ ደረሰ እያልሽ ላበረታሽኝ የኮሚኒዩኬሽን ባለሙያ ጓደኛየ ሃይማኖት በሪሁን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት ‹‹የጋብቻ ነውሮች በዳንግላ ወረዳ›› በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ ይህንን ርዕሰ ጉዳይ ለማጥናት ያነሳሳኝ ምክንያት እስካሁን በአደረግሁት የተዛማች ጥናቶችና ፅሁፎች ቅኝት የጋብቻ ነውሮችን በተመለከተ የተጠና ጥናት ስላላጋጠመኝ ነው፡፡ ጥናቱ በዳንግላ ወረዳ የሚከበሩ የጋብቻ ነውሮችን በመተንተን ያላቸውን ፋይዳ መግለፅ ዋና አላማአድርጎ የተነሳ ሲሆን በቅድመ ጋብቻ ወቅት የሚከበሩ/ለመጣስ የሚፈሯቸውን ነውሮች መተንተን ሚዜን፣ አሳዳሪን እና ሙሽሮችን የሚመለከቱ ነውሮችን ማብራራት፣ ድህረ ጋብቻን የተመለከቱ ነውሮችን መግለጽ እና የጋብቻ ነውሮች በምሳሌያዊ ንግግሮች እና በተረኮች እንዴት እንደሚገለፁ ማሳየት የጥናቱ ንዑሳን አላማዎች ናቸው፡፡ የታተሙና ያልታተሙ ፅሁፎችን፣ ቃለ መጠይቅን፣ ምልከታንና የቡድን ቃለ መጠይቅን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ አድርጎ ተጠቅሟል፡፡ በጥናቱ የተሳተፉ መረጃ ሰጭዎች የተመረጡት በአላማ ተኮር የናሙና አይነት ነው፡፡ ጥናቱ ጭብጣዊ የአተናተን ስልትን ተከትሎ ተተንትኗል፡፡ ማህበረሰቡ ነውሮችን የሚያከብራቸውና የሚፈራቸው ቅድመ ጋብቻ ላይ ባሉ ሴቶች ማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ችግሮች እንዳይደርሱባቸው በማሰብ፣ ወጣቶች ለተቃራኒ ፆታዊ ትንኮሳዎች እንዳይጋለጡ ለማድረግ፣ በጋብቻ ውል ላይ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችንና የሀሳብ ልዩነቶችን ለማጥበብ፣ በሙሽሮች ይደርሳል ተብሎ የሚታሰብን ችግር በመፍራትና የክፉ መንፈስ ተስተላልፎን ለመቆጣጠር በማሰብ መሆኑን የጥናቱ ግኝት ያመላክታል፡፡ ነውሮቹ አብሮነትን፣ አንድነትን ሀላፊነትን መወጣትንና ሚስጥር ጠባቂነትን ለማስተማርና ልጆቻቸው በመልካም ስነ ምግባር እንዲታነፁ ለማድረግ የሚያከብሯቸው መሆኑን በጥናቱ ግኝት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## ማውጫ

ይዘት ገጽ

ምስጋና ........ i
አጠቃሎ ........ ii
የቃላት መፍቻ ........ vii
ምዕራፍ አንድ:- መግቢያ ........ 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 2
1.3. የጥናቱ አላማዎች ........ 4
1.4. የጥናቱ ጥያቄዎች ........ 4
1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 4
1.6. የጥናቱ ወሰን ........ 5
1.7. ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሄዎች ........ 5
1.8. የመስክ ተሞክሮ ዘገባ ........ 6
1.9. የጥናታዊ ፅሁፉ አደረጃጀት ........ 8
ምዕራፍ ሁለት:- ክለሳ ድርሳናት ........ 9
2.1. ፅንሰ ሀሳባዊ ዳራ ........ 9
2.1.1. የነውር ምንነት ........ 9
2.1.2. የነውር አይነቶችና አመዳደባቸው ........ 12
2.2. የተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ (Functional Theory) ........ 15
2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 17
2.3.1. የነውርን ጠቀሜታ ያጠኑ አጥኚዎች ........ 17
2.3.2. የነውሮችን ጥሰትና በሰዎች ላይ የሚያሳድሩትን ተፅዕኖ ያጠኑ አጥኚዎች ........ 21

ምዕራፍ ሶስት፡- የጥናቱ ስነ ዘዴ ........ 24
3.1. የጥናቱ አይነት ........ 24
3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ........ 24
3.2.1. ቃለ መጠይቅ ........ 24
3.2.2. ምልከታ ........ 26
3.2.3. የቡድን ቃለ መጠይቅ ........ 27
3.3. የናሙና አመራረጥ ........ 28
3.4.የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ........ 29
ምዕራፍ አራት:- የዳንግላ ወረዳ ማህበረ ባህላዊ ዳራ ........ 30
4.1. ወረዳው የሚገኝበት አካባቢና አመሰራረት ........ 30
4.1.1. የወረዳው ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ አለበበስና አጊያጊያጥ ........ 31
4.1.2. የወረዳው የኢኮኖሚ ሀብት ........ 32
4.1.3. የዳንግላ ወረዳ የጋብቻ ስርዓት ........ 33
ምዕራፍ አምስት:- በጥናቱ የተገኙ "የጋብቻ ነውሮች" ትንተና ........ 38
5.1. የቅድመ ጋብቻ ነውሮች ትንተና ........ 39
5.1.1. ሴት ልጅ ከማግባቷ በፊት ማድረግ የሌለባት ነገሮች /"ነውሮች" ........ 39
5.1.2. የሴትና ወንድ ተጋቢ ቤተሰቦች የሚያከብሯቸው ነውሮች ........ 43
5.1.2.1. ከመሰል ሃይማኖት ጋር መተጫጨትና መጋባት ........ 43
5.1.2.2. ሴት ልጅ በጋብቻ ውል አፈፃፀምና ውሳኔ ከመሳተፍ መቆጠብ ........ 44
5.1.2.3. የሴትም ሆነ ወንድ ተጋቢ ቤተሰቦች የዕለተ ጋብቻ ውሳኔን ከመተው መጠንቀቅ ........ 45
5.1.2 .4. በሁለቱም ፆታ በኩል ያሉ ተጋቢ ቤተሰቦችን ማንነት ማክበር ........ 47
5.1.3. የቅድመ ጋብቻ አለባበስና አጊያጊያጥ ነውሮች ........ 48
5.1.3.1. ሌባንና ግጭት ፈላጊ አካላትን የሚለዩባቸው አለባበስ /አጊያጊያጥ ነውሮች ........ 48

5.1.3.2. የትዳር አጋር ማጣትን በመፍራት የሚከበሩ አለባበስ/ አጊያጊያጥ ነውሮች ....52

5.2. የዕለተ ጋብቻ ነውሮች ትንተና ....54

5.2.1. ዕለተ ጋብቻ ተፈፃሚ እንዲሆን በቀጣር (አጋቢ ዳኛ) የሚከበሩ ነውሮች....55

5.2.2. ሙሽሮች የሚያከብራቸው ነውሮች ....59

5.2.2.1. የተለያዩ ስራዎችን ከመስራትና ካልተገቡ እንቅስቃሴዎች መቆጠብ....59

5.2.2.2. የደም መራመድ ስርዓትን ተግባረራዊ ማድረግ ....61

5.2.2.3. የአመጋገብ ስርዓታቸውን የተመጠነ ማድረግ ....62

5.2.2.4. ሙሽሪት እንድትለምድ የሚያደርጉ ነውሮችን ማክበር ....63

5.2.2.5. ሙሽሮችን ሀብታም ያደርጋሉ ተብለው የሚታሰቡ ነውሮችን መተግበር....66

5.2.3. የስር ሚዜንና አሳዳሪን በተመለከተ የሚፈሯቸው ነውሮች....69

5.3. የድህረ ጋብቻ ነውሮች ትንተና ....73

5.3.1. የሚስት ቤተሰቦችን ጣልቃ ገብነት ለመከላከል በአማች የሚከበሩ ነውሮች....74

5.3.2. ሚስት ባሏን እንዳከበረች የሚያሳዩ ነውሮች....79

5.3.3. ስንፍናና ጾታዊ ትንኮሰሳን የሚያወግዙና በባል የሚከበሩ ነውሮች ....85

5.3.4. የከብት እና የሰው በሽታን እንዳያመጡ የሚያከብሯቸው ነውሮች....88

5.3.4.1. የማዝ በሽታን ለመሸኘትና ለመከላከል የሚጠቅሙ ነውሮች....89

5.3.4.2. የቤታቤት እምነት ሲከበር የሚጠነቀቋቸው ነውሮች....90

5.3.4.3. ለክፉ አጋጣሚ ይዳርጋሉ በሚል የሚፈሯቸው ነውሮች ....91

5.3.5. ድህረ ጋብቻ አለባበስና አጊያጊያጥ ነውሮች....94

5.3.5.1. ህፃናትን ከክፉ መንፈስ የሚከላከሉ አለባበስና አጊያጊያጥ ነውሮች....95

5.3.5.2. ለተቃራኒ ፆታ ግንኙነት መጋለጥን የሚከላከሉ የአለባበስ/አጊያጊያጥ ነውሮች ..101

5.4. የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች ....103

ምዕራፍ ስድስት፡- ማጠቃለያ ....104

**ዋቢ መጻህፍት** ........................................................................................................106

**የቃላት መፍቻ**

| ቃል (ሀረግ) | ፍቺ (ትርጉም) |
|---|---|
| አማች | የልጅ ወይም የእህት ባል |
| ብርቅጥል | እናቶች ከአንገታቸው የሚያደርጉት ከብር የተሰራና የክብ ቅርፅ ያለው ጌጥ |
| | ሴቶች እጃቸውና እግራቸው ላይ የሚያደርጉት ከብር የተሰራ ጌጥ |
| የቤታ ቤት | በቤተሰብ ደረጃ በቤት ውስጥ የምትከበር ሴት መንፈስ |
| የጋብቻ ውል | ከጋብቻ በፊት የተጋቢ ቤተሰቦች ለተጋቢዎቹ የሚሰጧቸውን ንብረት የተገባ ቃል ወይም ስምምነትን የያዘ ሰነድ |
| አጓዛ | ተለፍቶ ከለሰለሰ በኋላ ለመቀመጫነት የሚያገለግል የበግ ወይም የፍየል ቆዳ |
| ማዠ | የከብቶችን እግር ጥፍር በመቦርቦርና ወገባቸውን በመሰባበር ለሞት የሚያጋልጥ በሽታ |
| አንቀልባ | ለህፃን ማዘያ የሚያገለግል ስስና ለስላሳ ቆዳ |
| ቀለምሻሽ | ግራምጣ ከሚባል ሳር ወይም ከጥለት የሚሰራ የመሶብ ወርቅ ቅርፅ ያለው ትንሽ የምግብ ማቅረቢያ እቃ |
| ድፍድፍ | በወፍራሙ በውሃ ተለውሶ የተዘጋጀ የጥንስስ፣ የእንኩሮ እና የቂጣ ውህድ |
| ቁሌታም | ከባህሉ ያፈነገጠ የመልበስና የማጌጥ ፍላጎት፤የወሲብ ፍላጎት ያለው |
| ድንግል | የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፅሞ የማያውቅ ሰው |
| ድሪ | ከብር የሚሰራ የሀብል ቅርፅ ያለው የእናቶች የአንገት ጌጥ |
| ቀጣር (አጋቢ ዳኛ) | በዕለተ ጋብቻ ተጋቢዎች የተጋቡበትን የንብረት መጠንና የጋብቻ ሁኔታ የያዘን የጋብቻ ሰነድ ፈርመው ያጸደቁ 3 ሰዎች እና ከጋብቻ ወረቀቱ የፈረሙት 3 ሰዎች በተለያየ አጋጣሚ ባይኖሩ ባልና ሚስት ቢጣሉ የሚያስታርቁ በፍርድ ቤት ቢካሰሱ ለፍርድ ቤት ምስክርነት ተብሎ ታስቦ እንደታዛቢ የሚቀመጡ 2 ሰዎች ናቸው፡፡ በድምሩ ጋብቻን ለማፅደቅ የሚቀመጡ 5 ሰዎች ቀጣር ወይም አጋቢ ዳኛ ይባላሉ፡፡ |
| አሳዳሪ | የወንድ ሙሽራን ተቀብሎ የሚያስተናግድና የሚጋብዝ ሰው |
| የስር ሚዜ | ሙሽሪትን ለመንከባከብ በሽማግሌዎች ቃለ መሀላ የተቀበለ ሰው |
| ሰራቂያን | በወሊድ ሰዓት እናቶችን ልባቸውን በመሰወር ለሞት የምታደርስ ሴት መንፈስ |

# ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ይህ ጥናት የዳንግላ ወረዳ ማህበረሰብ የሚያከብራቸውን የጋብቻ ነውሮች መተንተንና ፋይዳቸውን መግለፅ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ነውር ማህበረሰቡ ባህላዊ መተዳደሪያ ደንብ ይሆነው ዘንድ በተለያየ ጊዜ የፈጠረው ህግ ነው፡፡ነውር እንደ ማህበረሰቡ ባህል የተለያየ ቢሆንም እንዳይበላ እንዳይለበስ፣የጋብቻ ስርዓትእንዳይጣስ፣ግጭት እንዳይከሰት የተፈጥሮ ሀብት እንዳይመናመን የወጣ ህግ ሊሆን ይችላል፡፡ ህጉ ማህበረሰቡ በባህሉ መሰረት ያወጣው መጥፎና ጥሩ የሚላቸውን ድርጊቶች የሚለይበት ነው፡፡

''ነውሮች በአብዛኛው ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ሲሆኑ ሰዎች የተስተካከለ ስነ ምግባር እንዲኖራቸው ለማድረግ የተቀመጡ ህግና ደንቦች ናቸው'' (Coldging and Folke, 2001, 584):: ነውሮች በመደበኛ ትምህርት የተገኙ እውቀቶች ሳይሆኑ ማህበረሰቡ መተዳደሪያ ይሆነው ዘንድ የፈጠራቸው ልማዳዊ ህጎች ናቸው፡፡ እነዚህ ህጎች የማህበረሰቡ ጠቃሚ ባህሎች እንዲቀጥሉ ለማድረግ የሚጠቅሙ ናቸው፡፡

ነውሮች እሴቶችን ከማስጠበቅ አንፃር በፅሁፍ ከረቀቁ ዘመናዊ ህጎች በላይ ህግን የማስከበር አቅማቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ምክንያቱም በአብዛኛው ማህበረሰብ ነውሮች ሲጣሱ በምህረት የሚታለፉ ሳይሆኑ በቀጥታ ለቅጣት የሚዳርጉ ናቸው (Omobola, 2013, 223)፡፡

ነውሮች በተለያዩ ትምህርት መስኮች የተጠኑ ቢሆንም በፎክሎር የትምህርት መስክ ግን ብዙ ጥናት አልተደረገባቸውም፡፡ ምክንያቱም የተጠኑ ጥናቶችን ቅኝት ሳደርግ አብዛኛዎቹ በስነ ልሳን ትምህርት ክፍል፣ በጤና ትምህርት ክፍልና በግብርና ትምህርት ክፍል የቀረቡ ናቸው፡፡ በስነ ልሳን ትምህርት ክፍል Mabay “Lingustic Taboo in African Marriage: the Oromo Ligguu'' በሚል ርዕስ በ2002 ዓ.ም የተጠና ጥናት ነው፡፡ ይህ ጥናት ባል ሚስቱን ሚስት ባሏን ለመጥራት እንደ ነውር የሚቆጠሩ ቃላቶችን በመተው የሚጠቀሟቸውን ተተኪ ስሞችን ላይ ያተኮረ ጥናት ነው፡፡

በጤና ትምህርት መስክ የተጠኑትን ስንመለከት ''Determinants of Food Taboos in the Pregnant Women of the Awabel Disterict in east Gojjam Zone'' በሚል ርዕስ

Wellelaw Getnet et. al ያቀረበውን ጥናት፣Food Taboo and misconceptions among pregnant Women of Shashemene Disterict በሚል ርዕስና በNejimu የቀረበውን እና በDawit et.al "Harmful traditional Practices in Ethiopia" በሚል ርዕስ በሞጁል መልክ በ2005 ዓ.ም የቀረቡትን ጥናቶች ስንመለከት የምግብ ነውሮች ያላቸውን አሉታዊ ጎን መመርመርና ነውሮችን ከጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች አንፃር ማየት ላይ የተኮሩ ናቸው።

ሌሎች በግብርና ትምህርት ክፍል የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤን በተመለከተ የተጠኑ ናቸው። Getaneh Haile ''the Contribution of GUDO Forest conservation culture is key to Biodiversity'' በሚል ርዕስ 2007 በሸካ ህዝቦች ላይ የተጠና ነው። Yoseph Maru et.al ''Indigenous ways of environmental protection in Gedeo Community, Southern Ethiopia: A sociological perspective ''በሚል ርዕስ በ2020 የቀረበ ጥናት ነው። እነዚህ ሁለት ጥናቶች የሚያቀርቡት አመክንዮ እና ተረክ ይለያይ እንጅ ባህላዊ እምልኮና ነውሮች አካባቢን እና የተፈጥሮ ሀብቶችን ከማስጠበቅ አንፃር ያላቸው ጠቀሜታ ከፍተኛ መሆኑን ያሳዩ ናቸው።

ከላይ ከተጠቀሱት ጥናቶች መረዳት እንደሚቻለው ነውሮችን ከጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች መመደብ፣ የልማት እንቅፋቶች አድርጎ የማየና አሉታዊ ጎናቸው ላይ የማተኮር ችግር ይስተዋላል። ነገር ግን ነውሮች ለማህበረሰቡ የሚያበረክቱት ሰላምን የማስከበር፣ ባህልን የማስቀጠል፣ ስነ ምግባርን የመቅረፅ ጠቀሜታች ሳይወሳ የሚታለፍ አይደለም። ጠቀሜታቸውን በተመለከተ የተጠኑ ጥናቶችም ቢሆኑ ከተፈጥሮ ሀብቶች አንፃር የታዩ ናቸው። በመሆኑም ይህ ጥናት በዳንግላ ወረዳ የሚከበሩ የጋብቻ ነውሮችን ጠቀሜታ በማጥናትና ያለውን ክፍተት በመሙላት የነውሮችን አውንታዊ ሚና ያሳያል።

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የጥናቱ ርዕስና ተጠኝውን ቦታ ለመምረጥ ያነሳሱኝ ሶስት ዋና ዋና የትኩረት ነጥቦች ናቸው።

**አንደኛ፡-** እስካሁን ባደረግሁት የጥናታዊ ፅሁፎች ቅኝት የጋብቻ ነውሮችን በተመለከተ የተደረገ ጥናት አላጋጠመኝም። የጋብቻ ስርዓትን በተመለከተ የሚደረጉ ዝግጅቶ (Marriage ceremonies) እና የተለያዩ መታሰቢያዎችን (Memorial ceremonies) በነውር ደረጃ

ያልተጠኑ ስለሆኑ በርዕስ ደረጃ ራሳቸውን ችለው መጠናት አለባቸው (Dodo, 2015, 18)፡፡ ከዚህም በመነሳት የጋብቻ ነውሮች ራሳቸውን ችለው ቢጠኑ መልካም እንደሆነ በማሰብ ነው፡፡

Birhanu ''Athematic Analysis ofLingustic Taboo and their corresponding Euphemistic expressions in Oromo'' በሚል ርዕስ በ2017 በስነ ልሳን ትምህርት ክፍል እና በሞላ ጀምበሬ ‹‹የነውር እሳቤ በሊሞ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ እምነት በሚል ርዕስ በፎክሎር የፒ.ኤች.ዲ ዲግሪ ማሟያነት በቀረቡ ጥናቶች ነውሮች በጥናት ደረጃ ገና ጅምር ላይ ያሉ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ Birhanu ስነልሳናዊ ነውሮች ላይ አተኩሮ ያጠና ሲሆን ማህበራዊ ነውሮችን (social taboos) ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸው የጎላ ነው፡፡ ነገር ግን አሁን ላይ ያለው ትውልድ ስለ ነውርያለው ግንዛቤ አናሳ ነው፡፡ ስለዚህም ቢጠኑ መልካም እንደሆነ ገልጿል (2017፣ 260)፡፡ ሞላ ጀምበሬ ጋብቻን፣ አለባበስንና አጊያጊያጥን በተመለከተ ነውሮች ለለውጥ እየተጋለጡና እየጠፉ በመሆናቸው ሊጠኑ ይገባል (2009፣9)፡፡ ስለዚህ በእነዚህ ጥናቶች ባገኙሁት ጥቁምታና ባደረግሁት ቅኝት መሰረት የጋብቻ ነውሮችን ለማጥናት አነሳስቶኛል፡፡

**ሁለተኛ፡-** የአሁኑ ትውልድ ከዘመኑ ቴክኖሎጅ ጋር ተያይዞ ነውሮችን ችላ የማለት ሁኔታዎችን ያሳያል፡፡ ይህም የሆነው ነውሮች እንደ ኋላ ቀር ባህሎች መታየታቸው ነው፡፡ ነውሮችን ችላ ያለ ትውልድ ኢትዮጵያዊነት ባህሉን ትቶ የምዕራባውያንን ባህል መቀበሉ አያጠያይቅም፡፡ ስለዚህ ትኩረቴን ነውር ላይ ማድረጌ የተጠኘውን ማህበረሰብ የባህል መበረዝን ከመታደግ አኳያ ከፍተኛጠቀሜታ እንዳለው በማሰብ ምርጫየን ነውር ላይ አድርጌዋለሁ፡፡

**ሶስተኛው፡-** ተጠኘውን ቦታ ለመምረጥ ያነሳሳኝ ምክንያት የተለያዩ ሀገረሰባዊ እምነቶች በአካባቢው ከሚፈፀሙባቸው ቤቶች ቤት እንዳንገባ፣ በቤቱ አልፈን እንዳንሄድ፣ ስማቸውን እንዳንጠራ ማስፈራሪና ማስጠንቀቂያ መሰል ትእዛዞች ሲሰጡ ለምን የሚል ሀሳብ ሳነሳ ቆይቻለሁ፡፡ ለምን ነው የምንከለከለው? የሚል ጥያቄ ስጠይቅ ነውር ነው የእናቴ መልስ ነበር፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ አዲስ ተቀጣሪ ሆኘ በሚዛን ከተማ በሚገኘው ሳላይሽ ሆቴል ከስራ ባለደረቦቸ ጋር ለመዝናናት በወጣሁበት ሰዓት ምግብ እየበላሁ ከመጨናነቄ ብዛትበጣም ነስሮኝ ነበር፡፡ ያስጨነቀኝ ነገር ቢኖር ከዚያ በፊት ባደግሁበት ማህበረሰብ ከጋብቻ በፊትም ሆነ በኋላ ሴት ልጅ ሆቴል ገብታ መታየት፣ መብላትና መጠጣት አትችልም፡፡

ለምን ሆቴል ገብቶ ለመብላትና ለመጠጣት እንደተጨነቅሁ ስፈትሽ ባደግሁበት ማህበረሰብ የተከለከለ በመሆኑ ወንጀል እንደሰራሁ ቆጥሬ ነበር፡፡ ስለዚህ የጋብቻ ነውሮችን ለማጥናት እንደ አንድ አነሳሽ ምክንያት አድርጌዋለሁ፡፡

## 1.3. የጥናቱ አላማዎች

የጥናቱ ዋና አላማ የዳንግላ ወረዳ ማህበረሰብ የሚያከብራቸውን የጋብቻ ነውሮች በመተንተን ያላቸውን ፋይዳ መግለፅ ነው፡፡ ይህንን ዋና አላማ መሰረት አድረጎ ጥናቱ የሚከተሉት ንዑሳን አላማዎች አሉት፡፡

- በቅድመ ጋብቻ ወቅት የሚከበሩ/ለመጣስ የሚፈሯቸውን ነውሮች መተንተን፣
- ሚዜን፣ አሳዳሪን እና ሙሽሮችን የሚመለከቱ ነውሮችን ማብራራት፣
- ድህረ ጋብቻን የተመለከቱ ነውሮችን መግለጽ፣
- የጋብቻ ነውሮ በምሳሌያዊ ንግግሮች እና በተረኮች እንዴት እንደሚገለፁ ማሳየት፣

## 1.4. የጥናቱ ጥያቄዎች

- የጋብቻ ነውሮችን መጠበቅ ለማህበረሰቡ ያላቸው ፋይዳ ምንድን ነው?
- ጋብቻን የተመለከቱ ነውሮች በማህበረሰቡ ያላቸው ተምሳሌታዊ ትርጓሜ ምንድን ነው?
- ጋብቻን የተመለከቱ አለባበስና አጊያጊያጥ ነውሮች ምንምን ናቸው?
- የጋብቻ ነውሮችን የሚገልጹ ምሳሌያዊ ንግግሮችና ተረኮች ያላቸው ፋይዳ ምንድን ነው?

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

1. ርዕሰ ጉዳዩ ገና በመጠናት ላይ ያለ በመሆኑ በጥልቅ ለማጥናት ለሚፈልጉ አጥኚዎች የመነሻ ሀሳብ ሊሆን ይችላል፡፡
2. የተጠኘውን ማህበረሰብ የጋብቻ ነውር አይነቶችን ያሳውቃል፡፡
3. ለወረዳው ባህልና ቱሪዝም እንደ መረጃ ምንጭ በመሆን አውንታዊ ጎን ያላቸውን የጋብቻ ነውሮች እንዲቀጥሉ ለማድረግ ያግዛል፡፡
4. የዳንግላ ወረዳ ማህበረሰብ ለሚያከብራቸው የጋብቻ ነውሮች የሚያቀርበውን አመክንዮ ያሳውቃል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከርዕሰ ጉዳይ አንፃር በሀገረሰባዊ ልማዶች ውስጥ በሚመደበው ሀገረሰባዊ እምነቶች ላይ ያተኮረ ሲሆንየጋብቻ ነውር ዋና ትኩረቱነው። የዳንግላ ወረዳ ማህበረሰብ በቤተክርስትያናት አካባቢ ያሉ ዛፎች እንዳይቆረጡ ሲል የሚያከብራቸው ነውሮች፣ አካል ጉዳተኞችን፣ ስራን፣ አነጋገርን፣ የምግብ አዘገጃጀትንና የምግብ አይነቶችን የሚመለከቱ ነውሮችን፣ ሞትን እና መካንነትን በመፍራት የሚያከብሯቸውን ነውሮች ጥናቱ አይመለከትም። ከመተንተኛ ንድፈ ሀሳቦች ውስጥ ከተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ ላይ ያተኮረ ነው።

በጋብቻ ሂደቶች ነውሮች እንዲከበሩ ለመግለፅና ለማስተማር የሚጠቀሟቸውን ምሳሌያዊ ንግግሮችና ተረኮች የጥናቱ አካል ናቸው። ምሳሌያዊ ንግግሮችና ተረኮች የተካተቱበት ምክንያት የጋብቻ ነውሮች በምሳሌያዊ ንግግሮችና በተረኮች የመገለፅ ባህሪ ስላላቸው ነው።

ከቦታ አንፃር በዳንግላ ወረዳ ከሚገኙት 32 ቀበሌዎች ውስጥ በተመረጡ አራትቀበሌዎች ላይ የተወሰነ ነው። ጥናቱ የክርስትና ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታይ ማህበረሰብን የጋብቻ ስርዓት ብቻ የሚመለከት ነው። ምክንያቱም አብዛኛው የዳንግላ ወረዳ ማህበረሰብ የክርስትና ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታይ ስለሆነ ነው።

## 1.7. ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሄዎች

ጥናቱ በሚካሄድበት ወቅት የተለያዩ ችግሮች አጋጥመውኛል። የመጀመሪያው ርዕሰ ጉዳዩን በተመለከተ የተዛማጅ ጥናት ቅኝት ለማድረግ የመረጃ እጥረት መኖር ነው። ነውርን በተመለከተ በአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍ ብዙ ጥናቶች አልተደረጉም። በመሆኑም ርዕሰ ጉዳዩን የተመለከቱ መረጃዎችን በመፈለግ ብዙ ጊዜ ጨርሻለሁ። በዚህ ትምህርት ክፍል የተሰሩ ጥናቶችን (ከሞላ ጎደል ጥናት) ውጭ ስላላገኘሁ በሌሎች ትምህርት ክፍል በተጠኑ ጥናቶች ላይ ትኩረቴን አድርጊያለሁ። በዚህም የመረጃውን ውስንነት ለመቅረፍ ችያለሁ።

ሁለተኛው ቃለመጠይቅ በማደርግበት ወቅት የጥናቱን ርዕስ እና ዋና ትኩረት ካስተዋወቅሁ በኋላ ቀጠሮ ይዤ መረጃውን በቪዲዮ እንዲሁም በመቅረፀ ድምፅ በምሰበስብበት ወቅትመረጃ ሰጭዎች ነውሩን ለመናገር መሳቀቅ ነው። ሌላው ሁሉም ባይባሉ ሴት መረጃ ሰጭዎች ፎቶ አብረውኝ እንዲነሱ እና በድምፅ እንድቀርፃቸው ስጠይቅ ‹‹ቴሌቪዥን ውስጥ እንደምናያቸው

ልታስለፈልፌን ነው፤ ስንናገር ስንቱ ይሰማናል፤ ፎቶውንስ ስንቱ ያየዋል›› በሚል ምክንያት ፈቃደኛ አለመሆናቸው ተጠቃሽ ነው፡፡

ይህንን ችግር ለመመረቂያ የሚሆን ጥናታዊ ፅሁፍ ለመስራት የሄድሁ መሆኔን በመግለጽ፤ ድምፁ ለመረጃው ታማኝነት የሚያስፈልግመሆኑን በማሳወቅ፤ ፈቃደኛ የሆኑልኝን መረጃ ሰጭዎች የተቀረጸ ድምጽና ፎቶ በማሳየት ፈቃዳቸውን ማግኘት ችያለሁ፡፡

አራተኛው ወቅቱ ዳጉሳ የሚባለው የሰብል አይነት የሚበራይበት ጊዜ፣ ሰርግና የዘመድ ግንኙነት የሚደረግበት ወቅት ስለነበር ለምልከታ ጥሩ አጋጣሚ ቢሆንም ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ግን አስቸጋሪ ነበር፡፡ መረጃ ሰጭዎች በተመቻቸው ሰዓት ቀጠሮ ይዞ በመሄድ ማግኘት ችያለሁ፡፡

### 1.8. የመስክ ተሞክሮ ዘገባ

ለመመረቂያ ፅሁፍ የሚሆን ርዕስ ለማዘጋጀት የጀመርሁት በ2012 ዓ.ም ሚያዚያ ወር እንደገባ ነበር፡፡ Field work in folklore ለሚለው ኮርስ ማሟያነት ይሆነኝ ዘንድ የሚሻ ሚሾ በዓል አከባበርን መርጬ ክዋኔውን ተመልክቸ ነበር፡፡ ነገር ግን ከኮሮና በሽታ ጋር ተያይዞ መረጃውን ለመሰብሰብ ስለማይመች ከቤተሰብ ፎክሎሮች ውስጥ አንዱን መርጣችሁ ስሩ ተባለ፡፡ ስለዚህም ሀሳቤን ቀይሬ ከቤተሰብ ፎቶዎች ይዘት ትንተናና ታሪክ ላይ ሰራሁ፡፡ የሚሻ ሚሾ በዓል አከባበርን ለመመረቂያ ፅሁፍ ለማድረግ ሳስብ ጠባብና ብዙም የማያስተነትን ሆኖ አገኘሁት፡፡

ሁለተኛው ምርጫየ የቤታቤት ሀገረሰባዊ እምነትን ማጥናት ቢሆንም አልተሳካልኝም፡፡ ምክንያቱም ተረፈ ስዩም የሚባል የአካባቢውን ማህበረሰብ ኗሪ ስለ ቤታ ቤት እምነት ስጠይቀው አምነቱ በቤተሰብ ደረጃ ታምኖበት የሚከበር እምነት ነው፡፡ ስለዚህ ባዳ አይገባም፡፡ እምነቱን ሁሉም ሰው ስለማይከተለው የሚያመልኩት ሰዎች በድብቅ ያከብሩታል፡፡ አሁን ላይ አብዛኛው ሰው እየተወው ስለሆነ ከተወሰኑ ሰዎች ቤት ብቻ ይመለካል የሚል ምላሽ ሰጠኝ፡፡ ይህንን ሀሳብ ለዶክተር የኔዓለም ሳማክራት እምነቱን እየተውት ከሆነ ማህበረሰቡ አልተቀበለውም ማለት ነው፡፡ ሁለተኛ መረጃውን በበቂ ሁኔታ ላታገኝ ትችያለሽ፡፡ ፍላጎትሽ ሀገረሰባዊ እምነትን ማጥናት ከሆነ አተያይሽን ቀይረሽ በሌላ ስልት አካተሽ አጥኝው የሚል ምላሽ ሰጠችኝ፡፡

የቤታቤት እምነት በድብቅ የሚፈፀመው ይደርሳል ተብሎ የሚታሰብ ችግር በመኖሩ መሆኑን ከተረፈ ስዩም መረጃውን ቀድሜ ስላገኘሁ ትኩረቴን ወደ ነውር አደረግሁ፡፡ ከዚያም ጥር 09/05/2013 ጉዞየን ወደ ተጠኚው ቦታ አደረግሁ፡፡ ጥር 11/05 /2013 ወደ ውፍታ ዳጢ ቀበሌ ሄድሁ፡፡ የሁለት ቀን እረፍት ከአደረግሁ በኋላ 14/05/2013 ወደ ዳንግላ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በማምራት ከቢሮው ሀላፊ ባንቲገኝ ስሜነህ ጋር ተገናኘሁ፡፡

አገውኛ ቋንቋ ካልቻልሽ ወደ ጫራና ጊሳ መሄዱን ትተሽ ናሙናሽን ወደ አጋጋ፣ ወንደፋይ እና አባድራ ብታደርጊ ይሻላል ባሉኝ መሰረት ናሙናየን ወደ ተጠቀሱት ቀበሌዎች አደርግሁ፡፡ ከዚያም እስከ 24/05/2013 ለስብሰባ ሌላ ቦታ እንደሚሄድ ነግሮኝ የሚያስፈልጉኝን መረጃዎች ለመቀበል ለ25/05/2013 ቀጠሮ ይዘን ተለያየን፡፡

ከባህልና ቱሪዝም ባለሙያ ጋር ተለያይተን አባድራ ቀበሌ ውስጥ ከሚገኘው አባድራ ከተማ ለመሄድ በመንንዣ ችግር ምክንያት ስጨናነቅ የተመለከተ ሽማግሌ ‹‹ልጄ ነይ አስቲ የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል ተረጋግተሽ መኪናውን ጠብቂ አትጨነቂ›› አሉኝ፡፡ እኔም እነዚህ አባት ማን እንደሆኑና እና የት እንደሚኖሩ ጠጋ ብየ ማውራትና አንዳንድ ነገሮችን መጠየቅሁ ጀመርሁ፡፡ አባድራ ስላሴ እንደሚገኙና ድሉ ተፈራ እንደሚባሉ ነገሩኝ፡፡ እኔም ከወረዳው የመጣሁበትን አላማ ስነግራቸው ‹‹አይ ልጄ ይህንን ነው ምትፈልጊ የማውቀውን ባህላችንን እነግርሻለሁ›› ብለውኝ ቀጠሮ ይዘን ተለያየን፡፡ ወንደፋይ ያሉትን መረጃ አቀባዮች በእሱ በኩል ተጠቁሜ መረጃውን ሰበሰብሁ፡፡

በውፍታ ዳጢ ቀበሌ ያሉትን መረጃ አቀባዮች በተለያዩ የመንግስት ተልዕኮ ቀበሌውን ወክሎ የሚሰራውን ሙሉየለት እንየው ከቀበሌው በመሄድ አናገርሁት፡፡ አሱም መረጃ የሚሰጡኝን ሰዎች ጠቆመኝ፡፡ በአጋጋ ቀበሌ ያሉትን በአቶ ገነት ደሴ መርሻ አማካኝነት ጥሩ መረጃ ይሰጡሻል ገነት ደሴ ላከኝ በያቸው ባለኝ መሰረት መረጃ ሰጭዎችን ማግኘት ችያለሁ፡፡ በተጠቆምኋቸው ቀበሌዎች ቃለ መጠይቁን አያካሄድሁ የሰርግ አጋጣሚዎችን በመፈለግ በምልከታ መረጃየን ሰበሰብሁ፡፡ በ21/06/2013 ዓ.ም የቡድን ቃለ መጠይቅ በማካሄድ መረጃ ስብሰባየን አጠናቀቅሁ፡፡ በመጨረሻም በቀን 01/07/13 ለመመለስ ሳስብ በመባቻውና በእሮብ ቀን መውጣት ጥሩ አይደለም፤ በመንገድ የሚያገጥመው አይታወቅም የሚለው የማህበረሰቡ እምነት ስላለ ጉዞየን ሀሙስ ዕለት በ02/07/2013 በማድረግ አዲስ አበባ ተመለስሁ፡፡ አዲስ አበባ በመሆን በመስክ ያገኘትን መረጃ ተንትኛለሁ፡፡

### 1.9. የጥናታዊ ፅሁፉ አደረጃጀት

ጥናቱ በዋናነት የዳንግላ ወረዳ ማህበረሰብ የሚያከብራቸውን የጋብቻ ነውሮች በመተንተን ፋይዳቸውን መግለፅ አላማ አድርጎ የተነሳ ነው፡፡ ይህን አላማ ግብ ለማድረስ ፅንሰ ሀሳባዊ እሳቤዎችን ሊያዳብሩ የሚችሉ የተለያዩ አርቲክሎችንና መዝገበ ቃላቶችን በመጠቀም እንዲሁም ጥናቱ ከሌሎች ጥናቶች ጋር ያለውን ልዩነትና ተመሳስሎ ለማሳየት ተዛማጅ ጥናቶችን ቅኝት በማድረግ ተደራጅቷል፡፡

የዳንግላ ወረዳ ማህበረ ባህላዊ ዳራን የሚገልፁ የተለያዩ ያልታተሙ ፅሁፎችን በመጠቀም የተጠኘውን ማህበረሰብ ባህል በተወሰነ መልኩ አቅርቧል፡፡ በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታና በቡድን ቃለ መጠይቅ ወቅት የተገኙ መረጃዎች ከጋብቻ ስርዓት አንፃር ቅድመ ጋብቻ፣ ዕለተ ጋብቻ እና ድህረ ጋብቻ በመባል ተከፋፍለው ቀርበዋል፡፡ ቅድመ ጋብቻ፣ ዕለተ ጋብቻ እና ድህረ ጋብቻ በተመለከተ በመቅረጸ ድምፅና በምስል የተሰበሰቡ መረጃዎችን ወደ ፅሁፍ በመቀየር ጠቀሜታቸውንና በማህበረሰቡ ያላቸውን አቀባበል መሰረት በማድረግ ተመድበው ጭብጣዊ የአተናተን ስልትን በመከተልና በተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ እሳቤ መሰረት ተተንትነዋል፡፡ በጥናቱ ማጠቃለያ ክፍል አጠቃላይ የጥናቱ ሂደት የቀረበበት ሲሆን የጥናቱ ዋናዋና ግኝቶች በትንታኔው የተነሱ ፅንሰ ሀሳቦችን መሰረት አድርጎ በጥናቱ ትንታኔ ክፍል መጨረሻ ቀርበዋል፡፡ ጥናቱ ከአጠቃላይ ወደ መዘርዝር የተደራጀ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፡- ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሶስት ዋናዋና ርዕሰ ጉዳዮች የቀረቡበት ነው፡፡ የመጀመሪያው ፅንሰ ሀሳባዊ ዳራ ሲሆን የምሁራን ሀሳቦችንና የመዝገበ ቃላትን ፍቺ መሰረት በማድረግ የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ ግልፅ ለማድረግ የተሞከረበት ነው፡፡ ሁለተኛው ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ ሲሆን ስለ ተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ ምንነት የተገለፀበት ነው፡፡ ሶስተኛው ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ጥናቶች ቅኝት የተደረጉበት ነው፡፡

## 2.1. ፅንሰ ሀሳባዊ ዳራ

በዚህ ርዕስ ስር የነውር ምንነትን፣ የነውር አይነቶችንና አመዳደባቸውን የሚመለከቱ ርዕሰ ጉዳዮች ቀርበውበታል፡፡

### 2.1.1. የነውር ምንነት

ነውር መቼ፣ የት እና በማን ተፈጠረ ለሚለው ጥያቄ አንድ ወጥ የሆነ መልስ ማግኘት አስቸጋሪ ነው፡፡ አፈጣጠሩ ብቻ ሳይሆን ነውር የሚለውን ቃል ሁሉን የሚያስማማ ብያኔም የለውም፡፡ እያንዳንዱ ማህበረሰብ እንደሚከተለው እምነትና ልማድ የሚሰጠው ብያኔ የተለያየ ነው (Freud, 1913, 22)፡፡

የአብዛኛዎቹ ምሁራን እይታና የመዝገበ ቃላት ፍቺዎች ነውርን የተከለከለ፣ ጸያፍ፣ ጉድፍ፣ መተዳደሪያ ህግና ደንብ የሚል ትርጓሜ ሰጥተውታል፡፡ Taboo የሚለው የእንግሊዘኛ ቃል በእንግሊዘኛ አማርኛ መዝገበ ቃላት ፍች የተከለከለ ወይም እያደረጉት የማይናገሩት በማለት ይፈታዋል (ኤፍሬም አሰፋ፣ 727፣ ዓ.ም ያልተጠቀሰ)፡፡ በዚህ የመዝገበ ቃላት ፍቺ መሰረት ነውር ማህበረሰቡ እንዳይጣሱ ለሚፈልጋቸው ጉዳዮች የተቀመጠ ህግ ነው፡፡ ሰዎች በራሳቸው የሚፈጽሟቸው ነገር ግን ለመናገርም ሆነ በድርጊት ለማሳየት የሚፈሯቸው ነገሮችን የሚመለከት መሆኑን ያስረዳል፡፡

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ነውርን ‹‹ህጸፅ፤ገመና›› በማለት ይፈቱታል (1948፣ 634)፡፡ የኢትዮጵያ መፅሃፍ ቅዱስ ማህበር መዝገበ ቃላት ደግሞ ነውር የሚለውን ቃል ‹‹ውርደት›› በማለት ይፈታዋል (1992፣27)፡፡ በዚህ መዝገበ ቃላት ፍቺ መሰረት የቃሉ ብያኔ ከነውር ጥሰት ላይ ያተኮረ ነው፡፡

ውርደት በተጠኘው ማህበረሰብ እሳቤ በሰዎች ፊት ተቀባይነትን አለማግኘት ነው፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ ከሚከተለው ባህል ውጭ የሆኑ ሰዎች መገለጫ ነው፡፡ አንድ ሰው ውርደት ገጠመው ከተባለ በሌላ አገላለፅ ነውሩን ጣሰ ማለት ነው፡፡ በአጠቃላይ በቀረቡት የመዝገበ ቃላት ፍች መሰረት ነውርየሰው ልጅ ባህሉ የሰጠውን መገለጫ አልቀበልም በማለት ለሚመጣ ችግር ሰለባ መሆንና ለስህተት መጋለጥን የሚያመላክት ነው፡፡

ነውር በዚህ ዘመን ተፈጠረ ብሎ ማስቀመጥ ቢከብድምከዘመነ ኦሪት ጀምሮ  የነበረ መሆኑን ከመፅሃፍ ቅዱስ ቃል መረዳት ይቻላል፡፡ ኦሪ.ዘፍ፣ ምዕ 2፣6-10 አዳም እና ሄዋን ሀጢያት በሰሩ ጊዜ ራቁት መሆናቸውን አወቁ፡፡ በቅጠልም ራሳቸውን ደበቁ ይለናል፡፡ ከዚህ ላይ አንድም የተቀመጠን ህግ መጣስንና የተከለከለ ነገር መኖሩን አንድም በፀጋ ተሸፍኖ የነበረው ሀፍረተ ስጋ መገለጡ በወቅቱ ከነበሩት አዕዋፋትና አራዊት መገለልን መፍራት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህንም የነውርን አመጣጥ ከአለባበስ ነውር አንፃርና መልካም ነገርን ከማጣት አንፃር ልናየው እንችላለን፡፡ በመሆኑም ከዚህ አንፃር ካየነው ነውር ከዘመነ ኦሪት በመጀመሪያው ሰው አዳም ተፈጠረ ልንል እንችላለን፡፡ ይህም ቢሆን ግን ሁሉንም አያስማማም፡፡ ምክንያቱም በየባህሉ እንደሚገኙት አፈ-ታሪኮች እና እምነቶች ብዙ ምክንያቶችና አተያዮች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

መፃፈ ሳሙኤል ካልዕ ምዕ. 13፣1-22 ያለውን ቃል ስንመለከት አምኖን ትዕማርን ሊደፍራት በሞከረ ጊዜ ‹‹እንዲህ ያለ ነገር በእስራዔል ዘንድ አይገባምና አታሳፍረኝ ይህን ነውረኛ ስራ አታድርግ እኔም ነውሬን ወዴት ልሸከም ትለዋለች፡፡›› አንድም የዘመዳሞችን ጋብቻ የሚከለክል አንድም ነውር የስነምግባርና የባህል ጥሰት መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ ነውሩም የአድርግ አታድርግ ህግ እንዳለ ያስገነዝበናል፡፡ ‹‹ነውሬን ወዴት ልሸከም›› ስትል ከበዚህ ጥናት ካለው ተጠኝ ማህበረሰብ አስተሳሰብ ጋር ሊዛመድ የሚችል ነው፡፡

ቅዱስ ቁርኣን ምዕ. 4፣ አል-ኒሳእ፣ ክፍል 4-5 ቁጥር 21-24 እንደተገለፀው ከሴቶች አባቶቻችሁ ያገቧቸውን አታግቡ (ትቀጡበታላችሁ)፡፡ ያለፈው ሲቀር እርሱ መጥፎ የተጠላ ስራ ነውና፡፡ እናቶቻችሁ፣ ሴት ልጆቻቸሁ፣ እህቶቻችሁ፤ አክስቶቻችሁ ያገቧቸውን አታግቡ፡፡ እያለ የዝምድና ሀረጎችን በመጥቀስ የዘመድ ጋብቻ ነውር እንደሆነ ያስረዳል፡፡

በተጠኘው ማህበረሰብ የጋብቻ ነውሮች በሚጣሱበት ጊዜ ከጣሰው ቤተሰብ ውጭ የሆነ ማህበረሰብ ቶሎ አይሰማም፡፡ ምክንያቱም ‹‹የራሳችንን ነውር ከተናገርን በዘመድ እንወቀሳለን፤ በጓደኞቻችን ፊት እናፍራለን›› በሚል እሳቤ ነው፡፡

የጋብቻ ስርዓት ነውር አመጣጥን በተመለከተ ማህበረሰቡ የራሱን ተረክ ያስቀምጣል። ለሴት ልጅ ጥሎሽ ሳይጥሉ መውሰድ ነውር የሆነበት ምክንያት ከአዳምና ከሄዋን ጀምሮ እንደሆነ በተረክ ገልፀውልኛል።

> አዳም ሄዋንን ለማውራት አፍሮ ዝምብሎ ከአጠገቧ ቆመ። ፈጣሪም ወደ አዳም ሚካኤልን ላከው። ሚካኤል ወርዶ አንተ ምነው ዝም አልሀት ብሎ ጠየቀው። አዳምም ምን ሰጥቸ ላውራት አለው። ከዚያ ከግድግዳ የተንጠለጠለ ወርቅ አውርዶ ሰጠው። አዳምም ወርቁን ሲሰጣት ሄዋን ፈገግ አለች። አዳምም በዚያ አማካኝቶ ማውራት ጀመሩ (ቃለ መጠይቅ፣ ከፋለ ነጋ፣ 03/06/2013)።

እስካሁን ስለ ነውር ምንነትና አፈጣጠር ያየናቸው ሀሳቦች መዝገበ ቃላትንና ቅዱሳት መፅሀፍትንመሰረት ያደረጉ ናቸው።

ከዚህ በታች የቀረበው ነውርን በተመለከተ ያጠኑ ሰዎች ሀሳብ ነው።

በዮርባ ህዝቦ (Yourba Peoples) እምነት ነውሮች ያላቸውን ጠቀሜታ ለማሳየት በተጠና ጥናት ስለ ነውሮች አመጣጥ ሲገልፅ፦ "ነውሮች ፈጣሪ መጥፎና ጥሩ ብሎ ካፀደቃቸው ድርጊቶ የመጡ ናቸው›› (Omobola, 2013, 222)።

ከቀረበው ሀሳብ እንደምንረዳው ሰዎች የነውሮችን አፈጣጠር የሚገነዘቡበት በአንድ ወቅት ከነበረ የሀገር አስተዳዳሪ ንጉስ፣ የእድር መሪና ባለስልጣን ሳይሆን ከሚያመልኩት አምላክ እየተላለፉየመጡ እንደሆኑ ነው። ለዚህም ነውሩ ሲጣስ ያያቸው ሰው ብቻ ሳይሆን ፈጣሪያቸው እንደሆነ በመቁጠር ንስሀ ይገባሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ በሃይማኖቱ መሪ ጸሎት እንዲደረግላቸው ይናገራሉ። ይህን ሁሉ ስንገነዘበው ነውር ከፈጣሪ የተሰጠ ትዕዛዝ እንደሆነ በመቁጠር ነው።

> ነውር ከ Polynesia ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም የተከለከለ ማለት ነው። ከታሪክ አንፃር ቅዱስ የተባሉ ሀይማታኖታዊ ትዕዛዛትን ለመጠበቅ፣ ለአማልክቶቻቸው ክብር እንዲሰጡ ለማድረግ ሲባል በሃይማኖት አባቶች፣ በተለያዩ ጊዜያት፣ ቦታዎችና ክስተቶች የተፈጠሩ ናቸው። ከዚህ ሲሰፋ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እንዲሁም ኢኮኖሚ ጠቀሜታ አለው (Osie, 2006, 43)።

ስለዚህም ነውሮች ማህበረሰቡ ያወጣቸው ደንቦች ናቸው። እነዚህ ደንቦች መሰረታቸው ቡድኑ የሚከተለው ሃይማኖት እና ልማድ ነው።

ስለዚህም ነውሮች የሚፈጠሩት በሚከተላቸውና ባወጣቸው ማህበረሰብ ነው። የሚያወጧቸውም ለሰናይ ስነ ምግባር ማስቀጠያዎች ለእኩይ ስነ ምግባር መቅጫ ህጎች ይሆኑ ዘንድ ነው። ባህላዊ ህጎች አለባበስና አጊያጊያጥን፣ አመጋገብን፣ የስራ ባህልንና ጋብቻን የሚመለከቱ ሊሆኑ ይችላሉ።

ከላይ የቀረበውን የOsieን ሀሳብ የሚቃወምም አለ። የተከለከለ የተባለው ጉዳይ አንዱ ጠብቆ ሊይዘው ይችላል። ሌላው ደግሞ ምንም ቢያደርግ ለሱ ክልከላ ላይሆን ይችላል። ስለዚህም ነውር አንድን ርዕሰ ጉዳይ ለይቶ እና መርጦ ህግ፣ ደንብና ግላዊ እምነት አድርጎ መቀበልና ማክበር ነው (Gantz, 1978,7)። ይህን ሀሳብ ስንመለከተው የተከለከለ ሁሉ ነውር እንዳልሆነ የሚያስረዳ ነው። ነውር ግላዊ እንጅ ማህበራዊ አይደለም ወደ ሚል አንድምታም ሊወስድ የሚችል ሀሳብ ነው።

ነውሮች ለስነ ምግባር መታነጽ እና ማህበረሰቡ ጥሩ ብሎ የተቀበለውን ድርጊት ለማስቀጠል ሲል የሚያስቀምጣቸው ስምምነቶች ናቸው (Maseka and Chameru, 2015, 123)። ነውሮችን መጣስ መገዳደልን፣ መናቅን፣ ትዳር ማጣትን፣ የመንቀሳቀስ ነፃነት መነፈግን፣ ከእድርና ከማህበር መገለልን፣ በሚመለኩት አማልክቶችና እምነቶች መረገምን፣ የልጅ መቅሰፍትን እና አካል ጉዳትን ያስከትላሉ ተብሎ ይታሰባል።

## 2.1.2. የነውር አይነቶችና አመዳደባቸው

ምሁራን ነውሮችን የመደቡበትን ስልት ስንመለከት ከጠቀሜታቸውና ከሚያስተላልፉት መልእክት አንፃር ነው። ከእነዚህም ውስጥ (Freud, 1913), (Osie,2016),(Alexandera,2016) እና (Chigd, 2006) ተጠቃሽ ናቸው

Freud ነውሮችን በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ከፍለዋል። አንደኛ በተፈጥሮ ከፈጣሪ የተሰጠ እና በሰዎች ላይ ያደረ ሀይልን በመፍራት የሚተገበሩ ነውሮችን ተፈጥሯዊ ወይም ቀጥተኛ በማለት አስቀምጠዋል።

ሁለተኛ በቄሶች፣ በሽሆች፤ተፅእኖ ፈጣሪ በሆኑ ሰዎች እንዲተገበሩ የሚደረጉና ሰዎች አምነው የሚቀበሏቸውን ኢ-ቀጥተኛ ወይም ተስተላልፏዊ በሚል መድበዋል፡፡ ሶስተኛ በባልና ሚስት እንደሁም በሌሎች መካከል ግጭት ሲፈጠር ለማስታረቅ ሲባል የተፈጠሩ ነውሮችን አስታራቂ (Mediatory) በሚል መድበዋል (Freud, 1913, 25)፡፡

የFreud አከፋፈል ስነልቦናዊ መሰረትነት ያለው አከፋፈል ነው፡፡ ምክንያቱም የጠቀሳቸውን የነውር አይነቶት አሳቤዎችን ስንመለከት ተፈጥሯዊ ያላቸው የማይታይን መንፈስ በመፍራት ቢጥሱ መንፈስ ቅዱስ በእነሱ ላይእንደሚፈርድ በመፍራ የሚቀበሏቸውና የሚተገብሯቸው ናቸው፡፡ አስታራቂ ያላቸው ሰዎች ከባህሉ አፈንግጠው ቢወጡ ለማስታረቅ ሲባል በምሳሌዊ አነጋገርም ሆነ በተለያዩ የስነ-ቃል ቅንጣቶች በመጠቀም ለማስታረቅ የሚያገለግሉ ነውሮችን የሚመለከት ነው፡፡

ሌላው ነውሮችን በሁለት ዋናዋና ክፍሎች የከፈሏቸው Osie ናቸው፡፡ አከፋፈላቸው ጠቀሜታቸውን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ የስነ ምግባር ህግና ደንብ በመሆን የሚያገለግሉትና ከልዕለ ሰብዕ ወይም ከፈጣሪ ትዕዛዝ ጋር የተያያዙትን (Moral value of Taboo) በሚል ይመድቧዋል፡፡ በተለያየ ጊዜና ቦታ የሚፈፀሙ አስደንጋጭ፣ አስፈሪ፣ አፀያፊ ከሆነና ያልተለመዱ ድርጊቶችን ከመፈፀምጋር የተያየዙትን (Sincetfc value of Taboo) በማለት ከፍለዋቸዋል፡፡ እነዚህን ነውሮች ለኢኮኖሚ እድገት፣ ለራስ ደህንነት፣ ወሊድን ለመቆጣጠር የሚተገበሩ፣ ራስን የማጥፋትና ሌሎችን የመግደል ነውሮች፣ ለተፈጥሮ ሀብቶች ጥበቃ ሲባል የሚከበሩ ነውሮች በማለት ይዘረዝሯቸዋል (Osie, 2006, 43)፡፡

የOsie አከፋፈል የነውሮችን ጠቀሜታ መሰረት ያደረገ የአከፋፈል ስልት ሲሆን ከሌሎች አንፃር ሲታይ ሰፋ ያለና በጥልቀት የታየ የአከፋፈል ስልት ነው፡፡

ሌላው ነውሮችን የመደቡት Alexandera, et. al, 2016 "A systematic review of resource habitat taboos and human health outcomes in the context of global environmental change" በሚለው ጥናታቸው በአምስት ዋና ዋና ክፍሎች ከፍለዋቸዋል፡፡ እነዚህም ፡-

አንደኛ በአንድ ማህበረሰብ ባህል ውስጥ እድሜንና ፆታን የተመለከቱ ነውሮችን Spatial/segment የነውር አይነቶች ይላቸዋል፡፡

ሁለተኛ የዱር እንስሳቶች የሚያደርሱትን አደጋ በመፍራት ለማደን፣ ለመንካትና ለማጥፋት የሚፈሯቸውን እንስሳቶችን የተመለከቱ ነውሮችን Spacious/specific Taboos ከሚለው ይመድቧቸዋል፡፡ እነዚህ ነውሮች የዱር እንስሳቱን ከመጠበቅ ባለፈ ደኖች እንዳይጨፈጨፉ የሚያገለግሉ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

ሶስተኛ የደረሱ ሰብሎችን ለመሰብሰብ ሲባል ለወራት እና ለሳምንታት ያህል የሚያገለግሉ ነውሮችን (Temporal Taboos) በማለት ይመድቧቸዋል፡፡

አራተኛ የሰውን ልጅ ደካማ ጎን በማየት፣ እንደ ፆታ፣ እድሜ፣ ቁጥር መብዛትንና ማነስን እንደ ክፍተት በመቁጠር ለሚፈፀሙ ድርጊቶች መከላከያ የሆኑ የነውር አይነቶችን (Life History Taboos) በማለት መድበዋቸዋል፡፡

አምስተኛው ኗሪው ማህበረሰብ የተፈጥሮ ሀብቶችን እኩል እንዲጠቀም የሚያደርጉ ነውሮችን Gear/ method taboo በሚል ርዕስ ይመድቧቸዋል፡፡

ነውሮች ለሾና ህዝቦች ያላቸውን ጠቀሜታ በተመለከተ የተጠና ጥናት በሁለት ከፍሏቸዋል፡፡ ማህበረሰቡን ለመቆጣጠር የሚያገለግሉ (Socialization and Social Control) እና ፍርሀትንና የባህሪ ውጤቶችን (Fear and Behavioural Outcomes) መሰረት ያደረጉ ነውሮች በማለት ከፍሏቸዋል፡፡ ማህበረሰቡን ለመቆጣጠር (Socialization and Social Contro) በሚለው ርዕስ ውስጥ ማህበረሰቡን ለማስተዳደር እንዲመች የሚያስችሉ ነውሮች እና ህፃናትን ማህበረሰቡ መልካም ስነ ምግባር ብሎ ወደ አመነበት ድርጊት ለማምጣትና ለማስተማር የሚጠቅሙ ነውሮች ቀርበውበታል፡፡

ፍርሀትንና የባህሪ ውጤቶችን (Fear and Behavioural Outcomes) መሰረት በማድረግ የመደባቸው ነውሮች በውስጣቸው እናትን በመፍራት (Fear for the Mother)፣ የትዳር አጋርን በመፍራት (Fear for the Spouse)፣ ልጆችን በመፍራት (Fear for one'sChildren) እናለራስ በመፍራት (Fear for One- self)የሚከበሩ ነውሮችበማለት ከፍሏቸዋል (Chigd, 2006, 177-182)፡፡

ለነውሮች አንድ ወጥ የሆነ አከፋፈልና መመደቢያ መስፈርት የለም፡፡ ነውሮች እንደ ዘመኑ ቴክኖሎጂ፣ እንደ ተጠኘው ቦታ፣ እንደ ማህበረሰቡ አቀባበልና አስተሳሰብ ይለያያሉ፡፡

ስለዚህም በሚጠናበት ጊዜ በሚገኙበት ቦታ እና ከተጠቃሚው ማህበረሰብ አንፃር መክፈሉ ተመራጭ ነው (Gantez, 1978, 9)፡፡

የዳንግላ ወረዳ ማህበረሰብ ነውሮች ጠቀሜታ እንጅ ጉዳት አላቸው ብሎ አያምንም፡፡ በማህበረሰቡ ነውሮች በባልና ሚስት፣ በትጭጭት ላይ ባሉ ተጋቢ ቤተሰቦች፣ በአማችና በአማት መካከል እንዲሁም በሌሎች ሰዎች መካከል ግጭት እንዳይፈጠር ለማድረግ፣ የጋብቻ ስርዓትን ለማፅደቅ፣ ፆታዊ ትንኮሳን ለመከላከያ፣ የአለባበስና ስርዓትን ለማስተማር ይጠቅማሉ፡፡ ከዚህም በመነሳት በዚህ ጥናት ነውሮች የተከፈሉት በተጠኝው ወረዳ ባላቸው አቀባበልና ጠቀሜታ አንፃር ነው፡፡

## 2.2. የተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ (Functional Theory)

ለጥናቱ መተንተኛተ መራጭ የሆነው የተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ (Functional Theory) ነው፡፡ ስለሆነም የንድፍ ሀሳቡ አመጣጥ ታሪክና ጠቀሜታ በአጭሩ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

የተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ እውቅና በማግኘት ጥቅም ላይ የዋለው በ1950ዎቹ ነው፡፡ ማጥናት የጀመሩትም Brown እና Malinowski የተባሉ የሶሾሎጅ አጥኝዎች ናቸው (Oring, 1976, 89)::

Brown መነሻ ያደረገው የማህበራዊ መዋቅርን (Social structure) ጠቀሜታን ነው፡፡ እያንዳንዳቸው የሰውነቶቻችን ክፍሎች ተግባራቸውን በሚገባ ማከናወን ሲችሉ ሙሉ የአካል ደህንነትና ቅርፅ ይኖረናል፡፡ ልክ እንደዚህ ሁሉ የእያንዳንዱ ማህበረሰብ ተግባር ማህበራዊ መዋቅሩ ቀጣይነት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ስለዚህም ፎክሎርን ከማህበራዊ መዋቅር አንፃር ያለውን ጠቀሜታ ማጥናት ተገቢ ነው የሚል ሀሰብን ይዞ የተነሳ ነው፡፡ ይህ ሀሳብ በተለያዩ አጥኝዎች ተቀባይነትን አላገኘም፡፡ የፎክሎርንና የባህልን ግንኙነት ማየት ይሻላል የሚል ሀሳብ በMalinowski ተነሳ፡፡ ይህም ቢሆን አጥኝዎችን ሙሉ በሙሉ አላስማማም፡፡ ምክንያቱም በፎክሎርና በባህል መካከል ልዩነት ማውጣት ወይም ድንበር ማበጀት ከባድ ነው፡፡ ፎክሎርና ባህል ልዩነት የላቸውም ብለው የሚያምኑም አሉ (Oring, 1976, 68)::

የፎክሎርን ጠቀሜታ በአራት ከፍሎ ማየት ተገቢ ነው የሚል ሌላ ንድፈ ሀሳብ ተቀነቀነ፡፡ እነሱም ለማስተማር (Education)፣ ለማጠናከር (to conformity the accepted pattern of Behavior)፣ ለማፅደቅ (validation) እና ለማምለጥ (to escap) ያገለግላል (Bascom, 1954, 345-349)፡፡

Sims and Stephens በበኩላቸው ፎክሎርና የፎክሎር ትርጉም ከሰዎች ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ ፎክሎር ትርጉም የሚኖረውከፎክ ቡድኑ ክዋኔና አውድ አንፃር ሲታይ ነው፡፡ የሚለውን የBascomን ሀሳብ በመደገፍ ፎክ ቡድኑ ሎሩን እየተጠቀመ ካለበት አውድ ወይም ሁኔታ ጋር አያይዘን መመልከት እንዳለብን ይመክራሉ፡፡ ምክንያቱም የፎክሎርን ፍቺ ከፎኩ ነጥሎ መመልከት አይቻልም (2005, 179)፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ እንደምንረዳው ንድፈ ሀሳቡ ሎሩ ለፎክ ቡድኑ ፎክ ቡድኑ ደግሞ ለሎሩ መኖር ያለውን አስተዋፅኦ ለማሳየት የሚረዳ ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ ስለዚህ የምናጠናውን የፎክሎር ዘርፍ ጠቀሜታ ሎሩ የገባበት አውድ ይወስነዋል፡፡

የተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ የሚፈፀመው ድርጊት ለተጠቃሚው፣ ለድርጊት ፈጻሚውና ለተመልካች የሚሰጠውን ጠቀሜታና የሚያስከትለውን ውጤት ለይቶ ለመተንተን የሚያስችል ነው (Diago, 2009, 107)፡፡

ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው የተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ ተጠቅመን በምንተነትንበት ጊዜ መታየት ያለበት እየተተገበረ ያለው ድርጊት (ሎሩ) ለከዋኙና ክዋኔውን ለሚመለከተው አካል (ለታዳሚው) ከሚሰጠው ጠቀሜታ አንፃር እንደሆነ ነው፡፡

የተግባራዊነት ንድፈሀሳብ ማህበረሰቡ በማህበራዊ መዋቅሩ (በተለያዩ ተቋማት፣ በባለስልጣናት፣ እና በልማዶች) የሚተገበሩ ክዋኔዎችን ከማበረታታትና ህጎችን ከማስከበር ላይ ያተኮረ ነው (Sciortion, 2020, 3)፡፡

በዚህ ጥናት የተግባራዊነት ንድፍ ሀሳብ የጋብቻ ነውሮችን ትንታኔ ለማድረግ የሚያገለግለው ቅድመ ጋብቻ፣ ዕለተ ጋብቻ እና ድህረ ጋብቻ ነውሮች ለማህበረሰቡ እያበረከቱት ያለውን ጠቀሜታ በትንታኔው በማሳየት ነው፡፡

ንድፈ ሀሳቡ የተጠኘውን ማህበረሰብ የጋብቻ ስርዓትና ህግ ለማስቀጠል፣ ሰዎች ከባህሉ እንዳያፈነግጡ ለማድረግና ለማስተማር፣ ጋብቻን በተመለከተ የሚነሱ ግጭቶችን ለመከላከልና ከጤና ጋር ተያያዥ የሆነ ችግሮችን እንዳይከሰቱ ለማድረግ የሚያስችሉ ነውሮችን ለመተንተን ጠቃሚ ሆኖ ስላገኘሁት ተመራጭ ሆኗል፡፡

## 2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥናቶች ቅኝት የተደረገበት ነው፡፡ እስከ አሁን በአደረግሁት የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት ‹‹የጋብቻ ነውሮች በዳንግላ ወረዳ›› በሚል ርዕስ የተጠናና የጋብቻ ነውሮችን ከፎክሎራዊ ጠቀሜታዎች አንፃር ያሳየ ጥናት አላጋጠመኝም፡፡ ነገር ግን ከርዕስ ጉዳዩ ጋር ቅርበት ያላቸውን ጥናቶች በሁለት ተከፍለው ቀርበዋል፡፡ መጀመሪያ የቀረቡት  የነውር ጠቀሜታ ያጠኑ አጥኚዎች ናቸው፡፡ እነዚህ መጀመሪያ የቀረቡበት ምክንያት ለርዕስ ጉዳዩ ይበልጥ ቅርበት ስላላቸው ነው፡፡ ሁለተኛ ላይ የቀረቡት ነውር የሚያሳድረውን ተፅዕኖና የሚጣስበትን መንገድ ያጠኑ ናቸው፡፡

### 2.3.1. የነውርን ጠቀሜታ ያጠኑ አጥኚዎች

የመጀመሪያው በሞላ ጀምበሬ ‹‹የነውር እሳቤ በሊሞ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ እምነት›› በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለፎክሎር የዶክትሪት ዲግሪ ማሟያነት በአማርኛ፣ ስነ-ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በ2009 ዓ.ም የቀረበ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ዋና አላማ የሊሞ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብበ ነውር ላይ ያለውን እሳቤና ነውር ለሚላቸው ጉዳዮች የሚሰጠውን መንስኤ ምክንያት በመመርመር የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፍና መግለፅ ነው፡፡ ይህንን ዋና አላማ መሰረት አድርጎ ነውር በማህበረሰቡ እምነት፣ አስተሳሰብና፣ እውቀት፣ ክህሎትና ባህሪ ውስጥያለውን ማህበራዊ ፍች መመርመር፣ በተጠኚው ማህበረሰብ ውስጥ ነውሮች የሚዘወተሩባቸው ርዕስ ጉዳዮች ነውር የሆኑት ለምን እንደሆነ የራሳቸውን ገለፃ መሰብሰብ፣ በነውሮች አማካኝነት የተጠኘውን ማህበረሰብ አካባቢያዊ፣ እውቀት፣ አስተሳሰብና ፍልስፍና መግለፅና መተንተን የሚሉትን ንዑሳን አላማዎች አካቷል፡፡ አጥኚው የተጠቀመው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ቃለ መጠይቅን፣ ምልከታና የቡድን ተኮር ውይይትን ነው፡፡

ማህበረሰቡ ነውር ለሚላቸው የምግብ አይነቶች የጤና ጠንቅ ስለሆኑ፤ ከሞት ጋር የተያያዙ ድርጊቶች ወደ ሞት ስለሚያመሩ፤ ከስራ ጋር የተያያዙ ድርጊቶች በረከትን ስለሚያሳጡ

የሚሉጉዳዮችን ዋና መንስኤ እንደሚያደርግ በጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ማህበረሰቦቹ ነውሮችን የሚፈጥረው የአባላቱን አስተሳሰብና ባህሪ ለመግዛት፣ የልጆችን ሰብእና ለመቅረፅ፣ ስጋዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶችን ለማርካት፣ ለአኗኗር መርህ፣ ለግንኙነት ህግና ደንብ ሆነው እንደሚያገለግሉ በማሰብ ነው ከሚል ግኝት ደርሷል፡፡

ጥናቱ ከተጠቀሰው ግኝት የደረሰ በመሆኑ የእኔ ጥናት ደግሞ ማህበረሰቡ ነውሮችን የሚያከብራችና የሚፈራቸው ቅድመ ጋብቻ ላያ ባሉ ሴቶች ማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ችግሮች እንዳይደርሱባቸው በማሰብ፣ ወጣቶች ለተቃራኒ ፆታዎች እንዳይጋጡ ለማድረግ፣ በጋብቻ ውል ላይ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችንና የሀሳብ ልዩነቶችን ለማጥበብ፣ በሙሽሮች ይደርሳል ተብሎ የሚታሰብን ችግር በመፍራትና የክፉ መንፈስ ተስተላልፎን ለመቆጣጠር ሲባል የሚከበሩ ሲሆኑአብሮነትን፣ አንድነትን፣ ሀላፊነት መውጣትንና ሚስጥር ጠባቂነትን ለማስተማር የሚጠቅሙ ናቸው ከሚል ግኝት በመድረሱ የሁለታችን ጥናት ይለያያል፡፡

የእኔ ጥናት ከሞላ ጥናት የሚለየው ይዞት የተነሳው ዋናአላማ ማህበረሰቡ ነውር የሚላቸውን ነገሮች ነውር የሆኑበትን ምክንያት ከህይወት ፍልስፍና አንፃር የመረመረ በመሆኑ የእኔ ጥናት የጋብቻ ነውሮችን በመተንተን ፋይዳቸውን መግለፅ ላይ ያተኮረ በመሆኑ እንለያያለን፡፡ ጥናቱ በተጠቀመው ንድፈ ሀሳብ፣ በመረጥናቸው የነውር አይነቶች የሁለታችን ጥናት ይለያያል፡፡ የሞላ ጥናት የማህበረሰባዊ ስነ ግንባታ ንድፈ ሀሳብእና የስነ ፋይዳ ንድፈ ሀሳብ ከፍልስፍና አንፃር የተጠቀመ ነው፡፡ የእኔ ጥናት ግን በተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ የተቀነበበ ነው፡፡ በእኔና በሞላ ጥናት መካከል ያለው ተመሳስሎ ቃለ መጠይቅንና ምልከታ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴን መጠቀማችን፣ በጥናቱ አይነት፣ ጭብጣዊ የአተናተን ስልትን መጠቀማችንና ከነውሮች ፋይዳ ላይ ማተኮራችን ነው፡፡

ሁለተኛው Mabay “Lingustic Taboo in African Marriage: a study of the Oromo Ligguu” በሚል ርዕስ በ2002 ዓ.ም የተጠና ጥናትነው፡፡ የጥናቱዋና አላማ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በኢሊባቡር አካባቢ የሚኖሩ ማህበረሰቦች ከጋብቻ ጋርተያይዞ በተለመደው መጠሪያ ስማቸው ለመጥራት እንደ ነውር የሚቆጥሯቸውን ቃላት ተክተው የሚጠቀሟቸው ስሞችን መመርመር ነው፡፡

በጥናቱ ሚስት ባሏን ለመጥራት እሱ፣ እሳቸውና የቤተሰቡ መሪ በሚል ምትክ ስሞች እንደምትጠራው በስራው ትንታኔ ውስጥ አሳይቷል፡፡

ባል ሚስቱን የእሱ ቤተሰቦች ባወጡላት ወይምሲያገባት በነበረው አጋጣሚና ሁኔታ በመሰየም እንደሚጠራት በጥናቱ ትንታኔ አሳይቷል፡፡ በመጨረሻም ጥናቱ በኢሊባቡር አካባቢ የሚኖሩ ባልና ሚስቶች በተለመደው ስማቸው መጠራራት ለቤተሰቡ አባላት ብቻ ሳይሆን ለአካባቢው ማህበረሰብ በሽታን፣ ሞትን የምርት መጠን መቀነስን ያመጣልበሚል እሳቤ መሆኑን በጥናቱግኝት አሳይቷል፡፡ ጥናቱን በምን አይነት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ እንደሰበሰበው አለመገለፁ እንደ ክፍተት ታይቷል፡፡

የMabay ጥናትከእኔ ጥናት ጋር የሚለያየው ዋና ትኩረት ከጋብቻ በኋላ ያለውን የነውር አይነት ከቃላት አጠቃቀም አኳያ ያጠና በመሆኑጥናቱ ይዞት በተነሳው አላማ ነው፡፡ ጥናቱ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ከጋብቻ በኋላ ያሉ ነውሮችንከቃላት አጠቃቀም አንፃር ቢሆንም እንደ አንድ ርዕሰ ጉዳይ ማንሳቱ ያመሳስለናል፡፡

ሶስተኛው Getaneh Haile "the Contribution of GUDO Forest conservation culture is key to Biodiversity" በሚል ርዕስ በጅጅጋ ዩኒቨርሲቲ (ትምህርት ክፍሉ ያልተጠቀሰ) 2007 በሸካ ህዝቦች ላይ የተጠና ነው፡፡ የጥናቱ ዋና አላማ የGUDO ባህል፣ ሀገር በቀል እውቀቶችና እሴቶቻቸው በሸካ አካባቢ ለሚገኙ ደኖች መጠበቅ ያላቸውን ጠቀሜታ መመርመርና መሰነድ ነው፡፡ ጥናቱን በቃለ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ሰብስቧል፡፡ የአካባቢው አስተዳዳሪ የነበሩ ሰዎች የተቀበሩባቸው ቦታዎች ላይ የበቀሉ ዛፎችን መመንጠር ባለቤትነቱ ለሚቹ እንደሆነ እንዲሁም አብርሃም ይስሃቅን ለመሰዋት የሄደበት ቦታ እንደሆነ መታሰቡ ለእፅዋቶች መጠበቅ ከፍተኛ ሚና እንዳለው በትንታኔው አሳይቷል፡፡

አጥኚው ምልከታ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ለአነሳው ርዕሰ ጉዳይ ወሳኝ ቢሆንም አልተጠቀመም፡፡ ይህም እንደ ክፍተት ታይቷል፡፡ በመጨረሻም ጥናቱማህበረሰቡ ስርዓተ አምልኮ ለሚፈፅምባቸው ዛፎች ያለው አሳቤ፣ ሀገረሰባዊ እምነቶች በዛፎች ስር መከበራቸውና ቅዱስ ከተባሉ ቦታዎች የሚገኙ ዛፎች እንዳይቆረጡ መከልከሉ፣ ሀገር በቀል እውቀቶችና ነውሮች በሸካ አካባቢ መኖራቸው የአካባቢው ደኖች እንዲጠበቁ ለማድረግና የአካባቢውን ስነ ምህዳር ለማስጠበቅ ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው አረጋግጧል፡፡ ጥናቱ ከተጠቀሰውን ግኝት ላይ በመድረሱ የአኔ ጥናት ጋር በግኝት እንያያለን፡፡ (የእኔ ጥናት ግኝት የሞላን ጥናት ቅኝት ሳደርግ ስላሰፈርሁት ከላይ መመልከት ይቻላል)፡፡

ጥናቱ ይዞት የተነሳው የGUDO ባህል፣ ሀገር በቀል እውቀቶችና አሴቶቻቸውበሸካ አካባቢ ለሚገኙ ደኖች መጠበቅ ያላቸውን ጠቀሜታ መመርመርና መሰነድ ያተኮረ በመሆኑ የእኔ ጥናት የጋብቻ ነውሮች መተንተንና ፋይዳቸውን ማሳወቅ ላይ ያተኮረ በመሆኑ የGetaneh Haile ጥናት ከእኔ ጥናት ይለያል፡፡ ይህ ጥናት የቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴን መጠቀሙ፣ የነውሮችን ተረክና ጠቀሜታቸውን መመልከቱ ከእኔ ጥናትጋር ይመሳሰላል፡፡

አራተኛው Maru et.al ''Indigenous Ways of Enivitomental protection in Gedeo Community, Southern Ethiopia: A sociological perespective'' በሚል ርዕስ በ2020 የቀረበ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ዋና አላማ ሀገረሰባዊ እምነቶች (ስርዓተ አምልኮዎችን ለመፈፀም የሚያገለግሉ ቦታዎች፣ ባህላዊ ህጎች (Traditional rules) እና ባህላዊ ድርጊቶች (Cultural practices) የአካባቢውን ስነ ምህዳር፣ የተፈጥሮ ሀብቶችንና ማህበረ ባህላዊ አሴቶቻቸውን ከማስጠበቅ አንፃር ያላቸውን ሚና መመርመር ነው፡፡ አጥኚው ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታንና የቡድን ተኮር ውይይትን በመጠቀም መረጃውን ሰብስቧል፡፡

ጥናቱ ዛፎቹ፣ ተራራዎችና ወንዞች ከፈጣሪያቸው ከMagenno (SkyGod) ጋር አብረው እንደተፈጠሩና ከፈጣሪያቸው ጋር እንደሚያገናኟቸው መታሰቡ (nature like mountains, hillsides, trees, rivers and forest patches are serves as bridge that connect the creature with Magenno (Sky God))፣ በአካባቢው የሚገኙ ሰዎችን እንደሚያከብሯቸው ሁሉ የተፈጥሮ ሀብቶችንም እኩል ማየታቸው፣ የምስጋና መዝሙሮችን የሚቀርቡባቸውን ዛፎች እንዳይቆረጡ መከልከላቸው፣ ለአገልግሎት ያልደረሱና በእድሜ ትልልቅ የሆኑ እፅዋቶችን መቁረጥ የተከለከለ መሆኑ፣ የዱር እንስሳቶችን መግደል የሰውን ልጅ እንደ መግደል ሀጢያት እንደሆነ መቆጠሩ አካባቢውንና የአካባቢውን ስነ ምህዳር ከማስጠበቅ አንፃር ከፍተኛ ሚና ያላቸው መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ቃለ መጠይቅን መጠቀሙና የነውሮችን አውንታዊ ሚና መመልከቱ ከእኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡

አምስተኛው Masaka and Chemhuru በተባሉ አጥኚዎች“Taboos As Sourse of Shona Peoples Enivromentale Ethics” በሚል ርዕስ2010 በClarion University of Pennsylvania በዝምባብዌ ውስጥ በሚገኙ በሾና ህዝቦች ላይ የተጠና ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ዋና አላማ በዝምባቢዌ ውስጥ የሚገኘው የሾና ህዝብ ነውር የሚሏቸው ጉዳዮች ለተፈጥሮ

ሀብቶች ጥበቃ ያላቸውን ጠቀሜታ ማሳየት ነው፡፡ ጥናቱ በምን አይነት የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ ዘዴ ተጠቅሞ እንደተነተነው አለመግለፁ እንደ ድክመት ታይቷል፡፡

ጥናቱ የሸና አካባቢ ህዝብ በየአካባቢያቸው እየሰሟቸውና በኢ ንቁስሜት (unconscious appreciation) የተቀበሏቸው ነውሮች የተፈጥሮ ሀብቶችን በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችሉ መሆናውን፣ በአካባበው የሚገኙ እፅዋቶችና እንስሳቶች ካለምንም መደበኛ ህግ የማስከበር ሚና እንዳላቸው፣ የሸና ህዝቦች ነውሮችን በራሳቸው ፍላጎት ብቻ የተቀበሏቸው ሳይሆኑ በተፈጥሮ ያገኟቸው አድርገው በመቁጠር እንደሚያከብሯቸው በጥናቱ ድምዳሜ ክፍል በማሳየት ጥናቱን ቋጭቷል፡፡

ጥናቱ ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው ነውሮች አደጋን ከመከላከል አንፃር ያላቸውንጠቀሜታ መመለከቱ ነው፡፡ የእነሱ ጥናት ይዞት የተነሳው አላማ ነውሮች ለተፈጥሮ ሀብቶች መጠበቅ ያላቸውን ፋይዳ ማሳየት በመሆኑ  እና የእኔ ጥናት የጋብቻ ነውሮች መከበር ያላቸውን ፋይዳ መግለፅ ላይ ያተኮረ በመሆኑ እንለያያለን፡፡

### 2.3.2. የነውሮችን ጥሰትና በሰዎች ላይ የሚያሳድሩትን ተፅዕኖ ያጠኑ አጥኝዎች

የመጀመሪያው ጥናት በYeslam"Breaking the taboos: the cause of Marriage education communitiesin Saudi Arabia." በሚል ርእስ በ2014 የተጠና ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ አላማ በሳውድ አረቢያ ውስጥ የተማሩ አካላት ለትዳር አጋራቸው ስለትዳር ህይወት (Marriage life) በግልፅ ለማውራት እንደ ነውር የሚቆጥሯቸውን ርዕሰ ጉዳዮችበምን መልኩ እንደሚጣሱ መግለፅ ነው፡፡

አጥኝው መረጃውን በፅሁፍ መጠይቅና በኢ ተሳትፎዊ ምልከታ የሰበሰበ ሲሆን መጠይቁን በድህረ ገፃቸው በመልቀቅ ስለጥናቱ አላማና ግብ አጭር ፅሁፍ በመፃፍ ለተጠያቂዎች ግንዛቤ ፈጥሯል፡፡

የቅርብ ጓደኛን፣ እህትን እና የትዳር አጋርን ፊት ለፊት በግልፅ ለማውራትና ለመጠየቅ የሚፈሯቸውን ነውሮች በኢንተርኔት ግንኙነት መጣስ በግንኙነቱ ከሌሎች የትዳር ህይወትና ልምድ እንዲማሩ፣ በቂ መረጃ እንዲያገኙ ማድረጉን፣ ወሲብን በተመለከተ በባልና ሚስቱ መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችና የወሲብ መፈፀሚያ አካላት ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች ሲገጥሟቸው መፍትሄ ለማግኘትና ችግሩን ለመፍታት የሚጠቀሙባቸው መሆኑን በጥናቱ

አረጋግጧል፡፡ በአንፃሩም የኢንተርኔት ግንኙነት ያሸማቀቃቸውንና ነውር የተባለውን ጉዳይ በግልፅ ለማውራት ቢጠቅማቸውም አንዳንዶቹ የገጠማቸውን መጥፎ ሁነት ስለሚነግሯቸው ትዳር ውስጥ ለመግባት እንደሚሸማቀቁና እንደሚፈሩ ማድረጉ አሉታዊ ጎን መሆኑን የጥናታቸው ግኝት ያመለክታል፡፡ ጥናቱ ከተጠቀሰው ግኝት ላይ የደረሰ በመሆኑና በመሆኑ የእኔ ጥናት ማህበረሰቡ ነውሮችን የሚያከብራችና የሚፈራቸው ቅድመ ጋብቻ ላያ ባሉ ሴቶች ማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ችግሮች እንዳይደርሱባቸው ለማድረግ፣ ወጣቶች ለተቃራኒ ፆታዎች እንዳይጋጡ ለማድረግ፣ በጋብቻ ውል ላይ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችንና የሀሳብ ልዩነቶችን ለማጥበብ፣ በሙሽሮች ይደርሳለ ተብሎ የሚታሰብን ችግር በመፍራትና የክፉ መንፈስ ተስተላልፎን ለመቆጣጠር ሲባል የሚያከብራቸው ሲሆኑ አብሮነትን፣ አንድነት፣ ሀላፊነት መወጣትንና ሚስጥር ጠባቂነትን ለማስተማር የሚጠቅሙ ናቸው ከሚል ግኝት በመድረሱ የሁለታችን ጥናት ይለያያል፡፡

በዚህም ይህ ጥናትከተማሩ ሰዎች ላይ ብቻ ያተኮረ ነው፡፡ የእኔ ጥናት ግን የተማሩትንም ያልተማሩትንም የሚያጠቃልል ሲሆን ኢተርኔትን መሰረት ያደረገ የነውር ጥሰትን አይመለከትም፡፡ ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ኢተሳትፏዊ ምልከታን በመጠቀሙ ነው፡፡

ሁለተኛው Agbemenl et. al "sex will make fingers grow thin and thin youdie": the inter play ofculture, Myth and taboo on African immigrant Mothers perceptions of Reproductive Health education with her Douthers Age 10-14 years' በሚል ርዕስ በFamily, Community & Health Sciences እና School of Nursing ትምህርት ክፍል በState University of New Yorkበ2013 የተጠና ነው፡፡ ጥናቱ ዋና ትኩረት ከአፍሪካ ሀገሮች (ናይጀሪያ፣ጋና እና ኬንያ) ተሰደው በUSA የሚኖሩ እናቶች ከ10-14 አመት ላሉ ህፃናት ከግብረ ስጋ ግንኙነት፣ ከእርግዝና፣ ከወር አበባ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ነውሮችንና አፈታሪኮችን እንዲቀበሏቸው ማድረግ የሚያስከትለውን ችግር መመርመር ነው፡፡ የAgbemenl et. alጥናት የተጠቀሰውን አላማ ይዞ የተነሳ በመሆኑና የእኔ ጥናት የጋብቻ ነውሮች ትንተናና ፋይዳ ላይ ያተኮረ በመሆኑ የሁለታችን ጥናት የተለያየ ነው፡፡

የAgbemenl et. al ጥናትየተጠቀመው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ቃለ መጠይቅ ነው፡፡ በመጨረሻም ጥናቱ ከ10-14 ዓመት ላሉ ህፃናት ወሲብን የተመለከቱ ነውሮች እርግዝና መቼ፣

የት እና እንዴት እንደሚከሰት መረጃዎችን እንዳያገኙ፣እውቀት እንዳይኖራቸውና ላልተፈለገ እርግዝና እንዲጋለጡ፣ በትምህርት ቤት ከወንድ ተማሪዎች ጋር ተቀራርበው እንዳይወያዩ እንዲሁም ስለ ወሲብ ያላቸው እሳቤ አሉታዊ እንዲሆን ማድረጉን፣ የወር አበባን በተመለከተ የሚነገሩ አፈ ታሪኮችና ነውሮች የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን ለመጠቀምና ለማስወገድ እያሸማቀቋቸው መሆኑን፣ ህመም ሲሰማቸው ለመናገር መቸገርን፣ ፈሪ ሆነው እንዲያድጉ ማድርጋቸውን የጥናቱ ውጤት ያሳያል። ጥናቱ ከተጠቀሰው ግኝት ላይ በመድረሱ ከእኔ ጥናት ይለያል። (የእኔን ጥናት ግኝት የGetaneh Haile እና የሞላ ጀመበሬን ጥናት ልዩነት ስጠቅስ ስለገለፅሁት መመልከት ይቻላል)።

ጥናት ነውርን እንደ አንድ ርዕሰ ጉዳይ አንስቶ ማየቱ እና ነውሮችን ከተረክ ጋር አያይዞ ማጥናቱ ያመሳስለናል። የቡድን ቃለ መጠይቀንና ምልከታን ባለመጠቀሙ ከእኔ ጥናት ይለያል። ከዚህም በተጨማሪ የእኔ ጥናት የነውሮችን አሉታዊ ጎን የመረመረ ባለመሆኑ ሁለቱ ጥናቶች ይለያያሉ።

# ምዕራፍ ሶስት፡- የጥናቱስነ ዘዴ

## 3.1. የጥናቱ አይነት

ጥናቱ አይነታዊ የምርምር አይነትን (Qualitative Research) የተከተለ ነው፡፡ ምክንያቱም ጥናቱ ቅድመ ጋብቻ፣ ዕለተ ጋብቻና ድህረ ጋብቻ ነውሮችን መተንተንና ፋይዳቸውን ከመግለፅ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የጋብቻ ነውሮችን ምን ያህሉ ማህበረሰብ ያምንባቸዋል? ለምን ያህል ሰዎች በጋብቻ ነውሩ ተጠቃሚ ሆነዋል? ለምን ያህሉ ደግሞ ጎድተዋል? የሚለውን በቁጥርና በመጠን መረጃው ሰብስቤ በጥናቱ ውስጥ አላሳየሁም፡፡ ይህ በመሆኑ አይነታዊ የምርምር አይነትን ተጠቅሜያለሁ፡፡

## 3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

ጥናቱን ከታሰበው ግብ ለማድረስ ቀዳማይ እና ካልዓይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተጠቅሜያለሁ፡፡ ካልዓይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ለዚህ ጥናት ተመራጭ የሆኑበት ምክንያት ከጥናቱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ የምርምር ውጤቶችን ለመዳሰስ፣ የጥናቱን ንድፍ ሀሳባዊ ማዕቀፍ ለማጠናከር፣ ስለ ነውርየሚያትቱ የተለያዩ የታተሙ መፃህፍትን እና አርቲክሎችን ለፅንሰ ሀሳባዊ ዳራ ማጠናከሪያ ስለተጠቀምሁ እንዲሁም ያልታተሙ ፅሁፎችን በመፈተሽ የዳንግላ ወረዳን አጠቃላይ ሁኔታ ለመግለፅ ወሳኝ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ስለሆነ ነው፡፡ በመስክ ምርምር ወቅት ቀዳማይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ የመስክ ምርምር የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች (ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታና የቡድን ቃለ መጠይቅ) ተግባራዊ ማድረግ የተፈለገበት ዋና ምክንያት በምልከታ ያልተገኙትን በቃለ መጠይቅ ስላገኘኋቸው ነው፡፡ በቃለ መጠይቅ ወቅት ለተሰጡ የተለያዩ መልሶች በቡድን ቃለ መጠይቅ ስላረጋገጥሁ ሶስቱንም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተጠቅሚያለሁ፡፡

### 3.2.1. ቃለ መጠይቅ

በዚህ ጥናት ከቀዳማይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ውስጥ ቃለ መጠይቅ በዋናነት አገልግሏል፡፡ ምክንያቱም ነውሮችን በተፈለገው ጊዜና ቦታ ማግኘት አስቸጋሪ ነው፡፡ የራሳቸው ቦታና ጊዜ ተሰጥቷቸው ወይም የሚከወኑበት አውድ ተዘጋጅቶላቸው አይተገበሩም፡፡

ስለሆነም ይህንን ችግር ለመቅረፍ ቃለ መጠይቁን እያካሄዱ አጋጣሚዎች ሲገኙ ምልከታ በማድረግ መረጃዎችን ለማግኘት ሲባል ቀዳሚው የመረጃ መሰብሰቢ ዘዴ ሆኖ አገልግሏል፡፡ ከቃለ መጠይቅ አይነቶች ነፃ ቃለ መጠይቅ (Structured Interview) ተጠቅሜያለሁ፡፡ ይህን የቃለ መጠይቅ አይነት የመረጥሁበት ምክንያት የጋብቻ ነውሮችን የተመለከቱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ለመረጃ አቀባዮች በሚመጥን መልኩ የተለያዩ ጥያቄዎችን በማቅረብ ነውሮች ነውር የሆኑበትን ምክንያት በተብራራ መልኩ መረጃ ለማግኘት አመቺ ስለሆነ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መረጃ አቀባዮች ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር የተያያዙና መልስ ይሆናል ብለው የሚገምቱት ሀሳብ ካለ በነፃነት እንዲገልፁ እድል የሚሰጥ በመሆኑ ዘዴው ተመራጭ ሆኗል፡፡

መረጃ አቀባዮች ሲጠየቁ በግልፅ ለመናገር የሚፈሯውን እና ያልተብራሩልኝ ሀሳቦች ርዕሰ ጉዳዩ እንደተጠበቀ ሆኖ ሌላ ሊደግፏቸው የሚችሉ ተጨማሪ ጥያቄዎችን በማንሳት መረጃውን ሰብስበቤያለሁ፡፡

ከእነዚህም ውስጥ የእርስዎ አማች (የልጅ ባል)፣ የልጅ ሚስት ምን ምን ተግባራትን ቢፈፅሙ? ምን ቢለብሱና ቢያጌጡ? እንዴት ቢቀመጥና ቢሄድ ነውር ይሆንበታል? ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚያውቁ ትተረክ ይኖራል? ነውር የሚጥሱ ሰዎችን የምትገልፁበት ምሳሌዊ አነጋገር ካለ ቢነግሩኝ? የጋብቻ ነውሮች ተጥሰው ቢገኙ ምን ችግር ያስከትላሉ? ለምሳሌ እኔ የእርሶ ልጅ ብሆን ነውሩን እንዳልጥስ እንዴት ያሳድጉኛል? የሚሉትን ተያያዥ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መረጃውን ሰብስቢያለሁ፡፡ ስለዚህም እንደነዚህ አይነት ተያያዥ ጥያቄዎችን ለማንሳት ተመራጩ ነፃ ቃለ መጠይቅ (Structured Interview) ነው፡፡

በቃለ መጠይቁ በአጠቃላይ 15ሰዎች ተሳትፈዋል፡፡ 8ቱ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች እና 7 ሌሎች መረጃ አቀባዮች በቃለ መጠይቁ ተሳትፈዋል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ 3ቱ ሴቶች ሲሆኑ 12ቱ ወንዶች ናቸው፡፡ በቡድን ቃለ መጠይቅ የተሳተፉትን ጨምሮ በአጠቃላይ 23 ሰዎች በጥናቱ ተሳትፈዋል፡፡

### 3.2.2. ምልከታ

ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በዕለተ ጋብቻ ቀን (በሰርጎች) በመገኘት ለመሰብሰብ ሞክሪያለሁ። በውፍታ ዳጢ ቀበሌ በተካሄዱ ሶስት ሰርጎች ላይ በመገኘት የጋብቻ ቀን ነውሮችን ሰብስቤያለሁ። በሰርጎቹ የተደረጉ ምልከታዎች ማን ምን ቢፈፅም በማህበረሰቡ እሳቤ ነውር ይሆናል? ለምን ነውር ተባለ? የሚሉትን ዕለተ ጋብቻ ነውሮችን በሚገባ ለማወቅ አረድቶኛል።

ዕለተ ጋብቻን ምልከታ ካደረግሁባቸው ቦታዎች ውስጥ በዘላለም ሞቴ ቤት በአቶ አማረ ዘላለም እና በወይዘሮ አልሳቤት አስራት በቀን 17/05/ 2013 በተደረግ የዕለተ ጋብቻ ስነ ስርዓት (የሰርግ ቀን)፣ በእጅጉ ታየ ቤት በወጣት ስመኝ እጅጉና በታረቀኝ አለምነህ ቤት በቀን 14/06/2013 በተደረገ የዕለተ ጋብቻ ስነ ስርዓት እና በመላክ አደላ ቤት በወጣት ሽጋው መላክ እና በወጣት ምወዳት ገነት በቀን 20/06/2013 በተደረገ የዕለተ ጋብቻ ስነ ስርዓት በመገኘት ምልከታው ተካሂዷል።

ከላይ በተጠቀሱት ቀናት ከቀጣሮች ጎን በመቀመጥ ቀጣርን የተመለከቱ ነውሮችን (በዕለተ ጋብቻ ከሙሽራውና ከሚዜዎች በፊት ከሙሽሪት ቤተሰቦች ሂደው ጋብቻውን የሚያፀድቁ ሰዎች) የሚከብሯቸውን ነውሮች፣ ከሚዜዎችና ከሙሽሮች ቤት በመግባት የሚዜ እና የሙሽራ ነውሮችን የተመለከቱ መረጃዎችን በምልከታ ሰብስቢያለሁ። የዕለተ ጋብቻ ስርዓትን ለመፈፀሚያ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ቀጣሮች የሚይዙትን ቁስና ሙሽሮች የሚቆሙበትን ንጣፍ) ለመመልከት ችያለሁ። ስለዚህም የሚጠቀሟቸውን ቁሳቁሶችን በተመለከተ ከታዳሚው ጋር በመቀመጥ ምን አይነት ቁሳቁሶች ባይጠቀሙ ነውር ይሆናል የሚለውን ጉዳይ ለመገንዘብ ችያለሁ። ድህረ ጋብቻ አለባበስና አጊያጊያጥ ነውሮችን በአገኘሁት አጋጣሚ ሁሉ ለመመልከት ችያለሁ። መረጃውን ለመሰብሰብ የተጠቀምሁት የምልከታ አይነት ኢ-ተሳትፏዊ ምልከታን ነው።

**ኢ- ተሳትፎዊ ምልከታ፡-** ይህን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተጠቀምሁበት ምክንያት ነውሮችን ለማጥናት በቀጥታ በመሳተፍ ለመሰብሰብ መሞከር አስቸጋሪ ሆኖ ስላገኘሁት ነው። ምክንያቱም ተሳትፏዊ ምልከታን ለማድረግ ነውሩን መፈፀም አለብኝ። ይህ አንዱ ሲሆን ሌላው ምክንያት የሚያከብሩትን ነውር (ለመጣስ የሚፈሩትን ነውር) በስተጀርባ ሆኖ ጉዳዩን ለመገንዘብ ስለሚያስችል ነው። ለነውሮች ለራሳቸው መፈፀሚያ ጊዜና ቦታ ተወስኖ

አልተቀመጠም። በማንኛውም ጊዜና ቦታ ሊፈፀሙ ይችላሉ። ስለዚህ ነውሮች በተገኙበት አጋጣሚ ሁሉ ከዳር ቆሞ በማየት መረጃውን ሰብስቢያለሁ።

### 3.2.3. የቡድን ቃለ መጠይቅ

በዚህ ጥናት የቡድን ቃለ መጠይቅ ተመራጭ የሆነበት ምክንያት በቃለ መጠይቅ ወቅት ተመሳሳይ ጥያቄ ቀርቦላቸው የተለያየ መልስ ለተሰጣቸው ጥያቄዎች ለቡድኑ አባላት ጥያቄውን በማቅረብ ርዕሰ ጉዳዩን ግልፅ እንዲያደርጉልኝና በእነሱ ባህል አሳቤ የትኛው ትክክል እንደሆነ ለማረጋገጥ  ስለተጠቀምሁበት ነው።

በቡድን ቃለ መጠይቅ ወቅት ቃለ መይቁን አቅራቢ ርዕሰ ጉዳዩን ቀድሞ የሚያውቅ ሲሆን ግልፅ ያልሆነለትን ርዕሰ ጉዳይ ድጋሜ ትኩረት ለመስጠትና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ሲል ቀድሞ ከሚያውቀው ወይም ካነሳው ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ ጥያቄ በማቅረብ ከቡድኑ እይታና ሀሳብ አንፃር መረጃውን የሚሰበስብበት ነው (Dawson, 2002, 230)::

(Dilshad and Latif, 2013,192, Denscombe 2007, 115)ን ጠቅሰው ሲገልፁ፡- “A focus group interview provides a setting for the relatively homogeneous group to reflect on the questions asked by the interviewe”.

ከገለፃው እንደምንረዳው የቡድን ቃለ መጠይቅ ተመሳሳይ ለሆኑ የቡድን አባላት ጥያቄ በማቅረብ አጥኚው ከቡድኑ ሀሳብ መልስ የሚያገኝበት መሆኑን ነው። በቡድንቃለ መጠይቁ የተሳተፉ ሰዎች ብዛት አንድ ሴት እና ሰባት ወንዶች በድምሩ ስምንት ሰዎች ናቸው። ለቡድን ቃለ መጠይቅ የተመረጡት ሰዎች ከ 38-70 የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ናቸው።

እነዚህ ሶስት የመስክ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች (ቃለመጠይ፣ ምልከታና የቡድን ቃለ መጠይቅ) የተሰበሰቡት በሁለት አይነት መቼት ነው። የመጀመሪያው በዕለተ ጋብቻ ያገኘኋቸውን ነውር የተባሉ ድርጊቶች በተፈጥሮ መቼታቸው ለመሰብሰብ ችያለሁ። ሁለተኛው ነውሮችን ሲተገበሩ ለማግኘት አስቻጋሪ የሆኑትንና በተገኘው አጋጣሚና በቃለ መጠይቅ ለተሰበሰቡ መረጃዎች አርቴፊሻል መቼት ተጠቅሚያለሁ። ይህ መቼት ነውር ሆነው እየተተገበሩ ያሉ ነገር ግን በክዋኔ ያላገኘኋቸውን መረጃዎች ለመሰብሰብ ተጠቅሜበታለሁ።

### 3.3. የናሙና አመራረጥ

በጥናቱ የተጠቀምሁት የናሙና አይነት አላማ ተኮር የናሙና አይነትን ነው፡፡ አድሚያቸው ከ32 እስከ 84 ዓመት ያሉ ሰዎች በመረጃ አቀባይነት ለናሙና ተመርጠዋል፡፡

በዚህ የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሰዎች ተመራጭ የሆኑበት ምክንያትነውሩን ብቻ ሳይሆን ነውር የሆነበትን ምክንያትም ለማስረዳትና በቂ መረጃ ለመስጠት የተሻለ ግንዛቤ ይኖራቸዋል ተብሎ ስለታሰበ ነው፡፡ የጥናቱን አላማና ጥያቄ ይመልሳሉ ተብለው የታሰቡት ሰዎች፣ የጋብቻ ውል ለማስጨረስ የሚመረጡ ሽማግሌዎችን፣ ከሁለት ወይም ከሶስት ጊዜ በላይ ሚዜ ሆነው የሚያውቁ ወጣቶችን እና የቤት እመቤቶችን በዋናነት ለናሙና መርጫለሁ፡፡

አቶገነት ደሴ መርሻ የተባሉ መረጃ አቀባይ ከአጋጋ በዋናነት ከፋለ ነጋን እና አዲሱ አረጋን፣ ከወንደፋይ ምናለ ጣሹን፣ ከአባድራ ድሉ ተፈራን ብትጠይቂብዙ ያውቃሉ፤ ሌሎች የሚያውቀቋቸውን ሰዎችም ይጠቁሙሻል ብለው በነገሩኝ መሰረት መረጃ አቀባዮችን መርጫለሁ፡፡ ውፍታ ዳጢ ቀበሌ የሚገኙ መረጃ አቀባዮችን በሙሉየለት እንየውና በአቶ ገነት ደሴ ጥቆማ መሰረት መርጫለሁ፡፡ አጋጋ ቀበሌ የሚገኙ መረጃ አቀባዮችን በገነት ደደሴ ጥቆማ መሰረት ያገኘኋቸውን አዲሱ አረጋና ከፋለ ነጋ ሌሎቹን እንዲጠቁሙኝ በማድረግ አግኝቻቸዋለሁ፡፡ ከአባድራ የሚገኙ መረጃ አቀባዮችን በአቶ ድሉ ተፈራና ከወንደፋይ የሚገኙ መረጃ አቀባዮችን በምናለ ጣሹ ጠቋሚነት መርጫለሁ፡፡ ከቦታ አንፃር በወረዳው ውስጥ ካሉት 32 ቀበሌዎች ለናሙናነት የተመረጡት አራት ቀበሌዎች (አጋጋ፣አባድራ፣ ውፍታ ዳጢ እና ወንደፋይ) ናቸው፡፡ እነዚህ ቀበሌዎች ተመራጭ የሆኑበት ምክንያት በውስጣቸው የሚኖረው ማህበረሰብ ሁሉም የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ በመሆኑ ነው፡፡

የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ሀላፊ የሆኑት ባንቲገኝ ስሜነህ ወደ ጫራና ጊሳ ባትሄጅ ጥሩ ነው፡፡ ከአማርኛ በተጨማሪ የአገውኛ ቋንቋ ይናገራሉ፡፡ ትርጉም የሚጠይቁ መረጃዎች ሊያጋጥሙሽ ስለሚችል ትኩረትሽን በእነዚህ ቀበሌዎች አካባቢ ባታደርጊ ጥሩ ነው ባሉኝ መሰረት የቀበሌዎችን ናሙና መርጫለሁ፡፡

## 3.4. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

አይነታዊ መረጃ ከሚተነተንባቸው መንገዶች ውስጥ የጭብጥና የይዘት ትንተና ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት ጭብጣዊ የአተናተን ስልት (Themathic analysis) ተመራጭ ሆኗል፡፡ ይህ የመተንተኛ ስልት የጋብቻ ነውሮች በጋብቻ ሂደቱ ያላቸውን አውዳዊ ትርጓሜና ጠቀሜታ ለመተንተን እንዲሁም ከጋብቻ ጋር ተያይዘው የሚነገሩተረኮችንና ምሳሌያዊ ንግግሮች የሚያነሱትን አቢይ ጉዳይ ለመግለፅ አስችሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የመተንተኛ ንድፈ ሀሳብ ሆኖ የተመረጠው የተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ ይህ የመተንተኛ ንድፈ ሀሳብ የጋብቻ ነውሮች ለተጠኘው ማህበረሰብ እያበረከቱት ያለውን አስተዋፅኦ ለማሳየት አገልግሏል፡፡

# ምዕራፍ አራት:- የዳንግላ ወረዳ ማህበረ ባህላዊ ዳራ

## 4.1. ወረዳው የሚገኝበት አካባቢና አመሰራረት

**ወረዳው የሚገኝበት አካባቢያዊ ገፅታ፡-** የዳንግላ ወረዳ ፕላን ኮሚሽን በጀት አመት ስታቲካል መፅሄት በ2013 ዓ.ም የቀረበውን የማዕከላዊ ስታስቲክስ ዘገባን መሰረት አድርጎ እንደገፈው ወረዳው በአዊ ዞን ስር ከሚገኙ 12 የገጠር ወረዳዎች እና 3 የከተማ አስተዳደሮች መካከል አንዱ ነው፡፡ ወረዳው ከክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ከተማ ባህርዳር 78 ኪሎ ሜትር እና ከዞኑ ርዕሰ መስተዳድር እንጅባራ በ38 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ በምስራቅ ሜጫ ወረዳ፣ በምዕራብ ጃዊ ወረዳ፣ በሰሜን ደቡብ አቸፈር ወረዳና በደቡብ ፋግታ ለኮማ ወረዳ ያዋስኑታል፡፡ አጠቃላይ የቆዳ ስፋቱ 73,613.36 ሲሆን መልክዓ ምድራዊ አቀማመጡ ሜዳማ 70 በመቶ፣ ተራራማ 27 በመቶ ፣ ወጣ ገባ 38 በመቶ ና ሌሎቹ 0.27 በመቶ ወረዳውን ሸፍነው ይገኛሉ፡፡ የወረዳ የአየር ንብረት ሁኔታን ሙሉ በሙሉ ወይናደጋ ነው፡፡

**የወረዳው አመሰራረት፡-** በ2001 ዓ.ም የዳንግላ ወረዳ የኢኮኖሚ ልማት ቢሮየታዋቂውን ስኮትላንድ የጀምስ ብሩስን የጉዞ ማስታዎሻ እና የዳንግላ ከተማ ልማት ማህበር ያዘጋጀውን ፅሁፍ መሰረት አድርጎ እንዳቀረበው ከተማዋ የተመሰረተችው 1676-1696 ዓ.ም የአቸፈር ገዥ በነበሩት በኪዳኑ ዲቁ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ከተማው በአገው ምድርና በአቸፈር አካባቢ ለሚመጡ ነጋዴዎች መቀመጫ ነበረች፡፡ የአሁኗ ዳንግላ ከተመሰረተች ከ240 አመት በላይ ሆኗታል፡፡ ለከተማዋ መስፋፋት መሰረት የሆኑት ከ1910-1920 ባሉት አመታት ውስጥ የታዩ የቴክኖሎጂ ለውጦች ሲሆኑ ከእነዚህም ውስጥ የመሸታ ቤቶች መስፋፋት፣ የንግድ አገልግሎት መስፋፋት እና ማህበራዊ ተቋማት መከፈታቸውና አገልግሎት መስጠታቸው እንደ ምክንያት ይጠቀሳሉ፡፡

በ1912 የፖስታ አገልግሎት በአሮጌው ዳንግላ መጀመር፣ 1914 የእንግሊዝ ቆንስላ ፅህፈት ቤት መከፈት፣ በ1926 የዘመናዊ ትምህርት ቤት እንቅስቃሴ በአቶ ሀዲስ አለማየሁ መጀመር ለከተማዋ መስፋፋት ተጨማሪ ምክንያቶች ናቸው፡፡ 1935 ዘመናዊ ትምርት ቤት በትምህርት ሚንስተሮች ተፈቅዶ መንገሻ ጀምበሬ ትምህርት ቤት ተከፈተ፡፡ በ1948 ዓ.ም መተከል እንዲሁም በ1949 ዓ.ም ባህርዳር ራሳቸውን ችለው አውራጃ ከሆኑ በኋላ በ1983 ዓ.ም የአገው ምድር አውራጃ ዋና ከተማ በመሆን አገልግላለች፡፡ በ2013 በወረዳው በወጣው ስታቲካል መፅሄት እንደተገለፀው አሁን ላይ በወረዳው በውስጡ5 የከተማና 32 የገጠር ቀበሌዎችን ይገኙታል፡፡

ዳንግላ የሚለው ስም ስያሜውን በምን መልኩ እንዳገኘ የራሱ አፈ ታሪክ አለው፡፡ አንከሻ፣ ባንጅ፣ ጫሪ፣ ቱምሂ፣ ዚገም፣ ኳኩሪ እና ዳንግሊ የሚባሉ ሰባት የአገው ወንድማማቾች ነበሩ፡፡ ብዙ ከተጓዙ በኋላ ዳንግላ ላይ ሲደርሱ ዳንግሊን ዞር ብለው ሲያዩት አብሯቸው የለም፡፡ ከዚያም ዳንግ እላ ዳንግ ወንድማችን የለም፡፡ እላ ማለት በአገውኛ የለም ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የቦታው ስም ዳንግ እላ ተባለ (ቃለ መጠየቅ፣ ዳኛው በላይ፣ 03/06/2013)፡፡

### 1.6.1. የወረዳው ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ አለበበስና አጊያጊያጥ

**ቋንቋ፡-** በዳንግላ ወረዳ የሚነገሩ ቋንቋዎች አገውኛና አማርኛ ናቸው፡፡ በዋናነት እየተነገረ ያለው አማርኛ ነው፡፡ አብዛኛዎቹ የወረዳው ቀበሌዎች የሚጠቀሙትም አማርኛን ነው፡፡ በተወሰኑ ቀበሌዎች እንደ ጫራ፣ ኳንድሻና ዱቢ ያሉት ከአማርኛ በተጨማሪ አገውኛ ቋንቋን ይናገራሉ (ቃለ መጠይቅ፣ ባንቲገኝ ስሜነህ፣25/05/2013)፡፡

**ሃይማኖት፡-** በወረዳው ውስጥ የክርስትና ኦርቶዶክስ ተዋህዶ፣ የእስልምናና የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታዮች ይገኙበታል፡፡ ከሶስቱ ሃማኖቶች በዋናነት የክርስትና ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ይመለካል፡፡ በክርስትና ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ተጋቢዎቹ የሀገርሽማግሌ ተቀምጦና ቤተሰብ ፈቅዶ ጋብቻቸውን መፈጸም ከፈለጉሁለቱም የክርስትና ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታይ መሆን አለባቸው፡፡ የክርስትና ኦርቶዶስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታይ የሆነ ከፕሮቴስታንት ወይም ከእስልምና ሃይማኖት አማኝ ጋር መጋባት ቢፈልግ ጋብቻውን ቤተሰብም ሽማግሌም ተቀምጦ አያፀድቅም፡፡ ከቤተሰብ አፈነግጣለሁ ያለ ግን መጋባት ይችላል፡፡ ከዚያ በኋላ በተለያዩ ማህበራዊ ግንኙነቶች ከቤተሰቦቹ ይገለላል (ቃለ መጠይቅ፣ ባንቲገኝ ስሜነህ፣25/05/2013 እና በቃሉ ፈጠነ፣ 13/06/2013)፡፡

**አለባበስና አጊያጊያጥ፡-** በዳንግላ ወረዳ የአለባበስ ስርዓትን ስንመለከት ወንዶቹ በአብዛኛው የሚጠቀሙት ኩታ(ጋቢን) ነው፡፡ ፎጣ በቀደሙት ዘመናት በብዛት እና በማንኛውም ቦታ ይለብሱ ነበር፡፡

አሁን ግን ለሌሊት ልብስ እና ለስራ ቦታ እንጅ ለለቅሶ ለቤተክርስተያን እና ለገበያ የሚጠቀመው የለም፡፡ የሱሪ አለባበሳቸውን በተመለከተ ድሮ የነበረው አጭር ሱሪ ቀርቶ አሁን ላይ ሁሉም ማለት ይቻላል ረጅም ሱሪ ይለብሳሉ፡፡ አባቶች በበዓል ቀን መብሩቅ የሚባል ነጭ ልብስ (በጎንና በጎን ጠርዙ ላይ ክፍተት ያለው ነጭ ሸሚዝ መሰል ልብስ እና ሱሪ) ይለብሳሉ፡፡

የሚይዙትን ባህላዊ መሳሪያ በተመለከተ ዱላ እና ከዘራ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ዱላ በእርሻ ቦታ በከብት ጥበቃ እና በአካባቢው ጠብ ሲፈጠር ይዞ ለመውጣት የሚጠቅም ሲሆን ከዘራ የሚባለው ግን በማህበር፣ በቤተክርስትያን፣ በለቅሶ እና በተለያዩ በዓላት ለግብዣሲጠሩ የሚያዝ ነው፡፡ ወንድ ልጅ ከአማት ቤት ተጠርቶ በሚሄድበት ጊዜ ጋሻ ወይም ዘመናዊ መሳሪያ ከሌለው በእነዚህ ምትክ ከዘራ መያዝ አለበት፡፡ ምክንያቱም እንደ ሚለብሳቸው ልብሶች ሁሉ የክብር መገለጫው የሽመል አይነት ነው (ቃለ መጠይቅ፣ ድሉ ተፈራ፣06/06/2013)፡፡

የሴቶችን አለባበስ በተመለከተ በጃኖ (ቀይ ጥለት) የተሰራ ነጠላ ወይም በአንድ አይነት ከለር የሚሰራ (ኳሴ ነጠላ) ይለብሳሉ፡፡ በጥቁር ከለር ብቻ የተሰራ ወይም በፋሽን መልክ የመጣውን የተለያየ ከለር ያለውን ባውንድ ከራሳቸው ይጠመጥማሉ፡፡ አጊያጊያጣቸውን በተመለከተ እርባን፣ ስንድድ አልቦ፣ እንዲሁም ከህፃን ማዘያ (አንቀልባ) የሚባለውን ለማጌጫ የሚጠቀሙበት ዛጎል የሚባሉት ማጌጫዎች በመጥፋት ላይ ያሉ እና አንዳንድ ሰዎች ቤት የሚገኙ ናቸው፡፡ አሁን ላይ ያለው የሴቶች ማጌጫ ብርቅጥል፣ ድሪ፣ ከብር የተሰራ የመስቀል ቅርፅ ያለው ሆኖ ከድሪውና ከብር ቅጥሉ በላይ ከአንገታቸው የሚደረግ ጌጥ ነው፡፡ የሚለብሱት ልብስ ረጃጅም ቀሚስ ነው (ቃለ መጠይቅ፣ ሙሉየለት እንየው፣07/06/2013)፡፡

### 4.1.2. የወረዳው የኢኮኖሚ ሀብት

ከወረዳው 83 በመቶ የሚሆነው ህዝብ የሚተዳደረው በእርሻ ስራ ነው፡፡ ወረዳው ለመስኖ ልማት የሚያገለግሉ አባይን ጨምሮ 8 የሚሆኑ ወንዞች የሚገኙበት ወረዳ በመሆኑ ሰፊ መሬት በመስኖ እየለማ ይገናል፡፡ ወረዳው በርካታ የቱሪዝም መስህብ ሀብት የሚገኝበት ወረዳ ሲሆን ወለተ ጴጥሮስ ገዳም ከወረዳው 19.5ኪሎ ሜትር እርቀትየሚገኘው አንዱ ነው፡፡

ሌሎቹ ዙርዙር ኪዳነምህረት ገዳም፣ 7ቱ የጉርቢ ዋሻዎች እና የትሰኪ ፏፏቴ ይገኙበታል (የዳንግላ ወረዳ ፕላን ኮሚሽን በጀት አመት ስታቲካል መፅሄት፣ 2013)፡፡

የዳንግላ ወረዳ የኢኮኖሚ ልማት አስተዳደር ባለሙያ እንደገለጹት ከአትክልትና ፍራፍሬ አንፃርአፈሳ፣ ጫራ፣ ጊሳ፣ ውንብሪ እና ዱቢ በመስኖ ልማት የሚጠቀሙ ቀበሌዎች ሲሆኑ ሽንኩራአገዳ፣ ሽንኩርት፣ ድንች፣ ጎመን እና ሌሎችንም ያመርታሉ፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ከብትእርባታም የመተዳደሪያ ሀብታቸው ነው፡፡ አጋጋ፣ አባድራ፣ወንድፋይ፣ ውፍታዳጢ፣ ዝጉዳ፣ ጉምድሪ፣ ላህታ፣ ጣራ ዋርኪት እና ሌሎቹ በዋናነት ዳጉሳ፣ ጤፍ፣ አተር፣ ባቄላ እና

በቆሎ አምራች ቀበሌዎች ናቸው፡፡ ከሰብል ምርቶች በዋናነት እነዚህን ይጠቀሙ እንጅ የመስኖ ልማት እና የንብ እርባታንም የሚያካሂዱ ቀበሌዎች አሉ፡፡ ጋብቻና የኢኮኖሚ ትስስራቸውን በተመለከተ በማንኛውም የኢኮኖሚ ዘርፍ የተሰማሩ ሰዎች መጋባት ይችላሉ (ቃለ መጠይቅ፣ አድማስ ጀምበሩ፣ 26/05/13)፡፡

በሽመና ስራ እና ቆዳ በመፋቅ የሚተዳደሩት ከሌሎቹ ጋር የመጋባት ሁኔታቸው ሲታይ አይጋቡም ማለት ይቻላል፡፡ በአጋጣሚ በስራ ቦታ ልጆች ተፋቅረው ሳይታወቅ ካልሆነ በስተቀር ቤተሰቦች አምነውበት ግን ጋብቻውን አያፀድቁም፡፡ ምክንያቱም ቆዳን በመፋቅ የሚተዳደሩት ሰዎች የንፅህና ጉድለት አለባቸው ተብሎ ይታሰባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቆዳ ስለሚሸከሙ የሰውነታቸው ጠረን የከፋ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ የሽመና ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ጋር መጋባት የሚከለከለው ቶሎ ተቀያሚ ናቸው ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ ይህም ሆኖ ግን አሁን አሁን እስራኤል ለመሄድ እያሉ የሽመና ስራ ከተሰማሩት ሰዎችጋር መጋባት አልፎ አልፎ እየታየ ነው፡፡

### 4.1.3. የዳንግላ ወረዳ የጋብቻ ስርዓት

በዳንግላ ወረዳ የጋብቻ ስርዓትን ለመፈፀም የሚጠቀሙባቸው ሶስት የጋብቻ አይነቶች  አሉ፡፡

**አንደኛ አሩሲ የጋብቻ ስርዓት:-** በባህላዊ መንገድየሚጋቡበትየጋብቻ ስርዓት አሩሲ የጋብቻ ስርዓት በመባል ይታወቃል፡፡ ወንድ ልጅ ቤተሰቦቹ ልጅህን ለልጄ ብለው ከላኩ በኋላ የሰውየው ዘር፣ ሃይማኖት፣ እና ስነ ምግባር ተጠንቶ የሴት አባት የሚሆነው ከሆነ ምላሹን የዚህን ቀን መጠህ ከብቶችን ወይም ንብረቷን አይተህ ሂድ ብሎ ወረቀቱን ይመልሳል፡፡ ከዚያም ሶስት ሽማግሌዎችን በመያዝ ከሴት ቤተሰቦች ይሄዳል፡፡

ከሴት ቤት የቀረበላቸውን ግብዣን ጨርሰው ሲወጡ የወንድ አባት የዚህን ቀን መጠህ እኔ ማቀርባቸውን ከብቶች እይ ብሎ ይሄዳል፡፡ የሴትአባት በተያዘው ቀጠሮ መሰረት ሂዶ ወንድ አባት ያቀረባቸውን ከብቶች ያያል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ወንዱ ለሴቷ የሚሰጣት ጥሎሽ ብር ወይም ሌሎቹን ጌጣጌጦች ሊገዛና አልባሳትን ሊያለብስ ይስማማሉ፡፡ ብር ከሆነ የወንድ ቤተሰብ ልጅ የሚያገባት ሴት ከአንድ እስከ ሶስት ከብት ብቻ ያላት ከሆነች ከ3000 እስከ 5000 ይደርሳል፡፡

የወንድ ቤተሰብ ልጅ የሚያገባት ሴት መሬት፣ባህርዛፍ ወይም ሌሎች አታክልቶችና ከተማ ቤት ያላት (ከሶስቱ አንዱ ካላት) የሚያቀርብላት ጥሎሽ 7000-12000 ድረስ ይደርሳል፡፡ ይህ የጥሎሽ አሰጣጥ ሁኔታ በአሁኑ ዘመን ያለ ነው፡፡ በቀደሙት ዘመናት ይህን ያህል ጥሎሽ አይሰጥም፡፡ ስለዚህ የጥሎሹ ሁኔታ ሴቷ ያላትን ወይም በወላጆቿ የቀረበላትን የሀብት መጠን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ይህ ክፍያ የወንድ ቤተሰብ ካቀረበው ከብት ተጨማሪ ክፍያ ነው፡፡ከተስማሙ የሰርጉ ቀን ቀጠሮ ይዘው ይለያያሉ፡፡ የተስማሙት በብር ከሆነ እንደ ፍላጎቷ ባህላዊ ጌጣጌጦችን እንደ ድሪና ብርቅጥል ያሉትን አድርጋ ወይም የአንገት ሀብልና ሌሎች ጌጠጌጦችንአድርጋ ትሄዳለች፡፡ በዚህ ሁኔታየሚያገባት ወንድ የጣትቀለበት የማድረግ ግዴታ የለበትም፡፡ ሳታደርግ የምታገባበት አጋጣሚ አለ፡፡ ይህ የሚፈጠረው ቤተሰቦቿ የሌላቸው ከሆነና ብሩን ለራሳቸው ለተለያዩ ወጭዎች ሲጠቀሙት ነው፡፡ የሰርጉ ቀጠሮ ቀን ሲደርስ 3 እስከ 5 ሰዎች ሆነው ከሚዜውና ከሙሽራው ቀድመው ይሄዳሉ፡፡ ሙሽሮቹ ደግሞ ከቀጣሮች ዘግይተsው ይሄዳሉ (ቃለ መጠይቅ፣ ከፋለ ነጋ፣ 03/06/2013)፡፡

ሙሽሪትም ይዛው ከምትሄደው ሙዳይ ውስጥ በቅባት እቃ ወይም በትንሽ ቅል የተነጠረ ቅቤ ወይም ቅባት፣ ጥፍር ቀለም፣ ኩል፣ እና ቤሳ ምላጭ አድርጋ ተዘጋጅታ ትጠብቃለች፡፡ የጋብቻው ቀን የጋብቻው ውል ሲጻፍ ውላችን እንደ **አሩሲ** ነው ተብሎ መፃፍ አለበት፡፡ ካልተባለ የሴት አባት አሺ አይልም፡፡ ምክንያቱም ከፍቅር ጠብ ቢመጣ እኩል አያካፍላትም ተብሎ ይታሰባል፡፡ በዚህ የጋብቻ ስርዓት አሩሲ ተብሎ እንዲጻፍ የሚፈለግበት ምክንያት ባልና ሚስት ቢጣሉ የሀብት ክፍፍላቸው ኢፍትሃዊ እንዳይሆን ተብሎ ነው፡፡ ይህንን ጉዳይ በእጅጉ ታየ ቤት በቀን 14/06/2013 ባደረግሁት የሰርግ ምልከታ አረጋግጫለሁ፡፡ በተጋቢዎቹ በወጣት ስመኝ እጅጉ እና ታረቀኝ አለምነህ የጋብቻ ስርዓታቸውን የሚያፀድቅ ወረቀት ተፅፎ ካላቀ በኋላ ሲነበብ ውላችን እንደ አሩሲ ነው የሚለው ቃል በስህተት ሳይፃፍ ታልፎ ወረቀቱ እንደገና ተቀይሮ ሲፃፍ ተመልክቻለሁ፡፡

ከዚህ ላይ የጋብቻ ስርዓቱ አሩሲ ተብሎ የተሰየመበትን ምክንያት በተመለከተ ከየት መጥ ተረኩን ከዳኛው በላይጋር በቀን 03/06/2013 ባደረግሁት ቃለ መጠይቅ እንደሚከተለው ገልፀውልኛል፡፡

የቀድሞው ሙቻ (የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች) መጠው ሀገሩን ወረሱት፡፡ ከወረራው በኋላ ሀራቸውን ይሂዱ ተባለ፡፡ ሌሎቹ ከሀገራችን ሲሄዱ ከመጡት መካከል ሁለት ሰዎች ቀሩ፡፡ አንዱ ዝጉዳ ኪዳነ ምህረት ውሽማ ይዞ ስለነበር በትልቅ ቅርጫት አዳፍና አስቀረችው፡፡ እዚሁ ለምዶ ቀረና ከዚያ በኃይለ ስላሴ እርስት ሲደላደል አሩሴ ሚባል ሀገር ደረሰው፡፡ ሁለተኛው አበጀውየሚባለው ደግሞ ሾልኮ አቸፈር ቀረ፡፡ አሩሲዎች ሲኖሩ አድነው ቢመጡ፣ ቢያመርቱና ተጋብተው ቢፋቱ እኩል ይካፈላሉ፡፡ አቸፈር ሚኖረውን አበጀውን አንተ ብለውታል አንገቷ ገብቶ ቂጧ ቢቀር እኩል ታካፍላታለህ? ሲሉት ቂጧን ነው እንጅ አንገቷን ምን ማደርገው ብሏል፡፡ አንተስ ለጋብቻ አትሆንም ብለው ሰድበውት ሄዱ፡፡ የአሩሲውን ደግሞ ይኸውን ጥያቄ ደግመው ቢጠይቁት ቂጧ ገብቶ አንገቷ ቢቀር አልተዋትም፡፡ ካለኝ ሁሉ አካፍላታለሁ የሚል ምላሽ ሰጠ፡፡ ከዚህም በኋላ ጋብቻችን እንደ አሩሲው ሀገር ሆኖ ቀረ፡፡

ስለዚህም ወረዳው የአሩሴን የጋብቻ ስርዓት የተዋሰው አሩሴ ከሚባል ሀገር እንደሆነ ተረኩ ያስረዳል፡፡ ይህ ደግሞ የሴቷን መብት የማስጠበቅ ፋይዳ አለው፡፡ የጋብቻ ቀን ቀጣሮች የጋብቻ ውል ወረቀቱ ተፅፎ ካለቀ በኋላ ቀድመው ቤት ይገባሉ፡፡ ሙሽሮች ትንሽ ቆየት ብለው ይገባሉ፡፡ ከገቡ በኋላ ሙሽራይቱ ከተቀመጠችበት ቤት ሙሽራው ገብቶ ካሉት ሴቶች ውስጥ ሚስቱን ለይቶ እጇን ይዞ ካወጣት በኋላ በሚዜዎቹ ታጅቦ ቀጣሩ ከሚስተናገድበት ቤት በመግባት ከእሱጋር ያስቀምጣታል፡፡ ግብዣው ካለቀና ቡናው ከተጠጣ በኋላ ቀለበት ካለ የቀለበት ስርዓት ሲደረግ ከሌለ ከምርቃት በፊት አባቶች ለሙሽራውና ለሚዜው ጥያቄ በማቅረብ ግዝት (ቃለ ምሀላ) ይፈፅማሉ፡፡

በዳንግላ ወረዳ በባህልና ቱሪዝም እሴት/ኢ/ል/ ቡድን በሰርግ ስነ ስርዓት ላይ በተዘጋጀ አጭር ፅሁፍ እንዳቀረበው በኑዛዜ ስርዓት በአባቶች ከሚጠየቁ ጥያቄዎች ውስጥ ለሚዜው ሙሉ ስሙ ማን እንደሆነ፣ ምን ሊያደርጉ እንደመጡ፣የጋብቻው ውል ያፀደቁ አባላት ስም፣ የሃይማኖቱ አስተዳደር ሃላፊዎች ስም፣ የሚዜው እህትና የሚዜው ነፍስ አባት ይጠየቃል፡፡ የስር ሚዜውም በጨለማ የነገረችኝን ሚስጥር በጨለማ፣ በቀን የነገረችኝን ሚስጥር በቀን አላወጣም፡፡ አስር ቀን እጠብቃታለሁ፣ የልብሶቿን ጭራ እፈትላለሁ፡፡ ይህን መፈፀም ባልችል ነፍሴ ገሀነም ትውረድ ብሎ ይገዘታል፡፡ ሙሽራውም በፈንታው እንጨት ደረቀባት ዘመድ አለቀባት፣ ከሳች፣ ጠቆረች፣ ጤና አጣች ብየ አልተዋትም ብሎ ቃል ይገባል፡፡

የሰርግ ቀንን በተመለከተ ሙሽራውና ግብዣው ካለቀ በኋላ ግዝት (ቃለ መሃላ) ተፈፅሞ ሚዜዎቹ እንዲሁም ሙሽሪትና ሙሽራው አንድ ላይ ከጨፈሩ በኋላ የሌለው በባጃጅ ያለው ከሆነ በህዝብ ማመላለሻ አውቶብስ ወደ ሙሽራው ቤተሰቦች ይሄዳሉ። በአሁኑ ስዓት በቅሎ የሚጠቀም የለም። ሰፈሩ መኪና ማይገባው ቢሆን እንኳ መስመር እስኪገቡ በእግራቸው ይሄዳሉ። ሙሽራው ሙሽሪትን ይዞ ከወንድ ቤተሰቦች ቤት እንደደረሱ ያለው በግ የሌለው ዶሮ አርዶ ሙሽራውና ሙሽሪት ደሙን ተራምደው ይገባሉ። ባርኮ ለመጀመሪያ የበጉንም ሆነ የዶረውን አንገት ሚቆርጠው ሙሽራው ነው (ምልከታ፣ 20/06/2013)።

ይህ የጋብቻ ቀን ካለፈ በኋላ በሶስተኛ ቀኑ ከሁለት ሚዜዎች ጋር በመሆንወደ ሙሽሪት እናት ቤት ይዟት ይመጣል። ከዚህም በኋላ አብራው ተመልሳ ሂዳ ለወራት ያህል በወንድ ቤተሰቦች ቤትትቆያለች።

***የፊት ሴት ጋብቻ ዓይነት፡-*** ይህ የጋብቻ አይነት ባልም ሚስትም አግብተው ቆይተው በተለያየ ችግር ሲፋቱ እና ባልየው የሚያገባትን ሚስት ቤት ሰርቶ ቆይቶ ከቤቱ ሚያስገባት ከሆነ ከዚህ የጋብቻ አይነት ይመደባል። በማህበረሰቡ በሌላ አጠራር የጋለሞታ ጋብቻ በመባል ይታወቃል። ይህ የጋብቻ አይነት ሲፈፀም ከጋብቻ በፊት አጭተኛው አሷን እንደዚህ አይነት ቤት አምጥቸልሽ ነበር ብሎ ሊነግራት ይችላል።ካመነችበት እሽ ብላ መመለስ ትችላለች። በመሆኑም ከአሩሲ ጋብቻ ጋር ሲነፃፀር የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ብዙም አይስተዋልበትም። በጋብቻው ከተስማሙ በኋላ ከእሷም ከእሱም ቤት ውል ከጨረሱ በኋላ አጃቢም ሚዜም ላያስፈልጋቸው ይችላል አጭተኛውና የተወሰኑ ሽማግሌዎች እና ባልየው መጠው ይዘዋት ይሄዳሉ። ከሄደች በኋላ እንደ ማደጎዎቹ (አግበብተው እንደማያቁ ሴቶች) ቁጭ አትልም። ተነስታ ቡና ታፈላለች። ይዛው የሄደችውን ዳቦ ቆሎ በወሰደችው ቆለምሻሽ ታቀርባለች። ቆለምሻሽ ይዛ የምትሄደው ለዳቦ ቆሎ ማሳለፊያበቤት ላይኖር ስለሚችል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው (ቃለ መጠይቅ፣ ድሉ ተፈራ፣06/06/2013)።

***መደበኛ ጋብቻ፡-*** ይህ የጋብቻ አይነት ሁለቱ ተጋቢዎች ተፋቅረው ከቆዩ በኋላ ለወደዳት ልጅ አባቱ ወረቀት እንዲልክለት ያደርጋል። አባትየውም ከየት እና ማን እንደሆነች ካጣራ በኋላ ዘርእና ሃይማኖቷን ጠይቆ ሚሆን ከሆነ እንዲያገባ ውል ይጨረሳል። የውል አጨራረሱ ሁለቱም ደሞዝተኛ ከሆነ በደሞዛቸው እሱ ባለደሞዝ ሆኖ እሷ የሌላት ከሆነ በመሬት ሁሉቱም ከሌላት በቤት እመቤትነት ይጋባሉ።

በጋብቻ ቀን ሙሽሪት መዋቢያዎቿን የምትይዝበት እንደ አሩሲ ጋብቻ በሙዳይ አይደለም፡፡ ዘመናዊ ቦርሳዎችን ትይዛለ፡፡ የስር ሚዜውም ሙሽሪት የምትቀይራቸውን ልብሶች በአነስተኛ የልብስ ቦርሳ ይይዛል፡፡ በትልቁ የተሰራ ሞሰብ ወርቅ በመኪና አብሮ ይሄዳል፡፡

**የዳንግላ ወረዳን አጠቃላይ ገጽታ የሚያሳይ ካርታ**




ምንጭ፡- ከዳንግላ ወረዳ የኢኮኖሚ ልማት ቢሮ

# ምዕራፍ አምስት:- በጥናቱ የተገኙ "የጋብቻ ነውሮች" ትንተና

በዚህ ምዕራፍ በዳንግላ ወረዳ ማህበረሰብ የተመረጡ አራት ቀበሌዎች የሚያከብሯቸውን (ለመጣስ የሚፈሯቸውን) ቅድመ ጋብቻ፣ ዕለተጋብቻ እና ድህረ ጋብቻን የሚመለከቱ ነውሮች ትንታኔ የተደረገበት ምዕራፍ ነው፡፡

በምዕራፍ ሁለት ለመግለፅ እንደተሞከረው ነውሮች አንድወጥ የሆነየመክፈያ ወይም የመመደቢያ መስፈርት የላቸውም፡፡ ሲከፈሉ የሚጠናው ማህበረሰብ ያለውን አቀባበልና አሳቤ መሰረት አድርገው ቢከፈሉ መልካም ነው፡፡ ስለሆነም የዳንግላ ወረዳ ማህበረሰብ ነውሮች ጠቀሜታ እንጅ ጉዳት እንዳላቸው አያምንም፡፡ በማህበረሰቡ ነውሮች በባልና ሚስት፣ በትጭጭት ላይ ባሉ ተጋቢ ቤተሰቦች፣ በአማችና በአማት መካከል እንዲሁም በሌሎች ሰዎች መካከል ግጭት እንዳይፈጠር ለማድረግ፣ የጋብቻ ስርዓትን ለማፅደቅ፣ ፆታዊ ትንኮሳን ለመከላከል፣ የአለባበስና የአመጋገብ ስርዓትን ለማስተማር ይጠቅማሉ፡፡ ከዚህም በመነሳት በዚህ ጥናት ከጋብቻ ስርዓት አንፃር ቅድመ ጋብቻ፣ ዕለተ ጋብቻና ድህረ ጋብቻ ተብለው የተከፋፈሉ ነውሮች በየስራቸው የቀረቡት አብይና ንዑሳን ርዕሶች የተከፈሉት በተጠኘው ወረዳ ካላቸው አቀባበልና ጠቀሜታ አንፃር ነው፡፡

በቅድመ ጋብቻ ሴት ልጅ ማድረግ የሌለባትን ነውሮች፣ የሴትና ወንድ ተጋቢ ቤተሰቦች የሚያከብሯቸው ነውሮች እንዲሁም ቅድመ ጋብቻ አለባበስና አጊያጊያጦች የሚሉ ርዕስ ጉዳዮች ተነስተዋል፡፡ የዕለተ ጋብቻ ነውሮች ቀጣርን የተመለቱ ነውሮች፣ ሙሽሮችን የሚያከብሯቸው ነውሮች፣ የስር ሚዜንና አሳዳሪን በተመለከተ የሚፈሯቸው ነውሮች በማለት ተከፋፍለው ቀርበዋል፡፡ ዕለተ ጋብቻ በሚለው አብይ ርዕስ ውስጥ እስከ መልስ ያሉት ነውሮች አብረው የተተነተኑበት ምክንያት በማህበረሰቡ እስከ ወር ድረስ ባሉት ቀናቶች ውስጥ ተጋቢዎቹ ‹‹ሙሽራ›› እየተባሉ ስለሚጠሩ ነው፡፡

ድህረ ጋብቻን በተመለከተ አማችን የተመለከቱ ነውሮች ሚስትን የተመለከቱ ነውሮችና ድህረ ጋብቻ አለባበስና አጊያጊያጥ ነውሮች ተተንትነዋል፡፡ ድህረ ጋብቻ አለባበስንና አጊያጊያጥ በሚለው ስር የቀረቡት ህፃናትን ከክፉ መንፈስ የሚከላከሉ አለባበስና አጊያጊያጥ ነውሮች እና ለተቃራኒ ፆታዊ ትንኮሳ መጋለጥን በመፍራት የሚከበሩ ነውሮች የቀረቡበት ሲሆን ህፃናትን የሚመለከቱ ነውሮች ድህረ ጋብቻ ላይ የተመደቡበት ምክንያት የሚከበሩት በህፃናት ሳይሆን በቤተሰቦቻቸው በመሆኑ ነው፡፡ በመረጃ ስብሰባ ወቅት የተገኙ መረጃዎችን በጭብጥ ከፋፍሎ

ለመተንተን የይዘት መመሳሰል ያላቸውን ነውሮቹ ለጭብጡ ይበልጥ ቀራቢ ወደ ሆነው ርዕሰ ጉዳይ በመመደብ ትንታኔ ተደርጓል፡፡

## 5.1. የቅድመ ጋብቻ ነውሮች ትንተና

በተጠኘው ማህበረሰብ በቅድመ ጋብቻ የወጡ ባህላዊ ህጎች እየተጠቀሙበት ያለውን ባህልና ወግ መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ በቅድመ ጋብቻ ያሉ ነውሮችን መጣስ ላላገቡ ልጆቻቸው ብቻ ሳይሆን ወላጆቻቸው በማህበራዊ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት (በማህበር፣ በእድር፣ በእቁብ እንዲሁም በቀብር ስርዓት አፈፃፀም) ተሳታፊ እንዳይሆኑ መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው፡፡ በቅድመ ጋብቻ የተገኙት መረጃዎች አብዛኛዎቹ ሴቶች ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ቢጣሱ ከወንድ ይልቅ ለሴት ልጅ የትዳር አጋር ማጣትንና ለተለያዩ ችግሮች መጋለጥን የሚያስከትሉ ናቸው፡፡ የቅድመ ጋብቻ ነውሮች ከተጣሱ በወንድና በሴት ተጋቢ ቤተሰቦች መካከል ከፍተኛ ግጭት ሊቀሰቅሱና የጋብቻ ቀን እንዳይሳካ እንቅፋቶች ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው፡፡ በቅድመ ጋብቻ የተገኙ መረጃዎች ሴት ልጅ ከጋብቻ በፊት ማድረግ የሌለባት ነውሮችና የወንድና ሴት ተጋቢ ቤተሰቦች የሚያከብሯቸው ነውሮች  በመባል ተከፋፍለው ቀርበዋል፡፡

### 5.1.1. ሴት ልጅ ከማግባቷ በፊት ማድረግ የሌለባት ነገሮች /"ነውሮች"

በማህበረሰቡ ሴት ልጅ ከማግባቷ በፊት ማድረግ ከሌለባት ነውሮች ውስጥ የመጀመሪያው ከመዝናኛ ቦታዎች መታየት፣ መብላት፣ መጠጣት፣ መንገድ ላይ ከወንድ ጋር መጫዎትና መንገድ ላይ መብላት እንዲሁም ራሷን ለአደጋ ከሚጥሉ ተግባራት አለማቀብ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

‹‹ዝሃ ሲበጣጠስ ሽማኔ አይቋጥረውም›› (ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ይመኑ መኮነን፣ 15/06/2013)

በማህበረሰቡ ሴት ልጅ ከቤቷ አብስላ እናጠምቃ መጠጣት ስርዓት ያላት ሴት ለመሆኗ አንዱ መገለጫ ነው፡፡ሴት ልጅ ከጋብቻ በፊት ጥሩ ሴት ናት ተብሎ ከሚታሰብባቸው መስፈርቶች ውስጥ ቤት ያፈራውን ከቤት መመገብ አንዱ ነው፡፡ ሴት ልጅ እንኳን መሸታ ቤት እና በመዝናኛ ቦታዎች ቤት ታይታ ገበያ ሂዳ አምሽታ ምትገባ ወይም ምትቆይ ከሆነ ማህበረሰቡ ስለ እሷ ያለው አመለካከት በጎ አይደለም፡፡ በተለያዩ መዝናኛ ቤቶች ገብተው የሚታዩ፣ የሚበሉና የሚጠጡ ሴቶች ለትዳር አይመረጡም፡፡ ሴት ልጅ በመዝናኛ ቦታዎች ገብታ የምትታይ፣ የምትበላና የምትጠጣ ከሆነ ለዝሙት ተጋላጭ ተደርጋ ትቆጠራለች፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሴት ልጅ ጠጥታ አትችልም (በእነሱ አባባል ጭንቅላቷ ቀላል ነው)

ተብሎ ይታሰባል፡፡ በዚህ ሰዓት በስካር ወድቃ ወንዶች ይደፍሯታል የሚል አሳቤ አላቸው (ቃለ መጠይቅ፣ይመኑ መኮነን፣ 15/06/2013)፡፡

ከላይ ከቀረበው ምሳሌያዊ አነጋገር እንደተገለፀው መዝናኛ ቤቶች ገብታየምትታይን፣ የምትበላና የምትጠጣን ሴት ልጅ በተበጣጠሰ ዝሃ ይመስሏታል፡፡ በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ማዕከል በተዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ፍች ገፅ 445 እንደተገለፀው ዝሃ የሚለው ቃል ድር ማለት ነው፡፡ የተበጣጠሰን ዝሃ(ድር) ሸማኔው መስራት አይችልም፡፡ ዝሃውን ለባለቤቷ ይመልሳል፡፡ ተፈትሎ በናፍጣ ለኩራዝ ማብሪያ እንኳ አያገለግልም፡፡ የተበጣጠሰውን ዝሃ አማራጩ መጣል ነው፡፡ ስለዚህ ሴት ልጅ ሰካራም ከሆነች በሸማኔው የተመሰለው ትዳር ፈላጊ ወንድ በዝሃ የተመሰለቻትን ሴት ለትርዳር አይፈልጋትም፡፡ አንድም ዝሃ ከነጭ ጥጥ ሚሰራ ወይም የሚፈተል ድር ነው፡፡ ሳይበጣጠስ ከተቀመጠ ለተፈለገው የልብስ ዓይነት መስሪያ ይሆናል፡፡ ሴት ልጅም በቅድስናና በንፅህና ከተቀመጠች የፈለገችውን ባል ታገባለች፡፡ ለወግ ለማዕረግም ትበቃላች፡፡

> በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ እችማ ሴት አይደለችም፤ ናት ተብሎም አይጨዎትም፡፡ ውሃ ቢጠማት ሻሂ ጠጭ ተብላ ካላገባች ከአባቷ ወይም ከወንድሟ ጋር ሆና ካገባች ከባሏ ጋር ሆና ብዙ ሰው ከማይበዛበትና ዞር ካለ ሻሂ ቤት ለምነው ሊያስገቧት ይችለሉ፡፡ ሆቴል ቤት ከሆነ ግን ከነሱ ጋርም አትገባም፡፡ ዋጋዋን አድርጋ ቶሎ ዞር ማለት አለባት፡፡ እንደዚህ አይነት ሴትን ስትሆን አይ የገሌ ልጅ መታደሏ የተባረከች ናት እንላለን፡፡ ካለበለዚያ ባለጌ እና ለትዳር ማትመች ናት፡፡ ሰክራ አንዱ ይቀልድባታል፡፡ ያገባም ይፈታታል፤ ያላገባም አያገባትም (ቃለ መጠይቅ፣ ድሉ ተፈራ፣ 06/06/2013)፡፡

በመሆኑም ይህ ነውርከመጠጥ ጋር ተያይዘው የሚፈጠሩያታዊ ትንኮሳዎችን ለመከላከልና ሴት ልጅ የትዳር አጋር እስክታገኝ ድረስ ላሉት ጊዜያት ጠብቆ መልካም እናት እንድትሆን ለማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ ያላገቡ ሴቶች አብዛኛዎቹ ወጣቶች ናቸው፡፡ የወጣትነት ፊት ደግሞ ለስላሳ ነው፡፡ ሰዎችን ከሩቅ ይስባል፡፡ በዚህ ስዓት ወንዶች በዝሙት መንፈስ ይሳባሉ፡፡ በመሆኑም ሴት ልጅ በመዝናኛ ቦታዎች መታየት፣ መብላትና መጠጣት የተከለከለ መሆኑ የሴታዳሪነት ህይወት እንዳይስፋፋ ለማድረግ ይጠቅማል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ሴት ልጅ ገበያ ውላ ስትመጣ መንገድ ላይ ውኃ ቢጠማት እንኳ ለጥማትዋ ሽንኩራገዳ መብላት ወይም ሌሎችን መጠጦች ይዛ መጠጣት፣ ቢርባት መንገድ ላይ ከሆነች የቋጠረችውን ግብጦ (ተቆልቶ ከውሃ ውስጥ ከ3-5 ቀናት ከተነከረ በኋላ ወጥቶ እየተፈለፈለ የሚበላ ባለ ሁለት ግርባብ የጥራጥሬ አይነት) ፈትታ መብላትም የተከለከለ ነው፡፡ ስርዓት አልባና ሆዳም እንደሆነች ትቆጠራለች፡፡

ሌላው ሴት ልጅ ከማግባቷ በፊት ማድረግ ከሌለባት ነውሮችውስጥከወንድ ልጅ ጋር መንገድ ላይ ቁማ ማውራት ነው፡፡በማህበረሰቡ ሴት ልጅ በአነጋገሯ ቁጥብና ጠንቃቃ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ሰላምታዋ በልክ የሆነ ከሆነች ለትዳር ፈላጊዋ ብዙ ነው፡፡ ምክንያቱም በተጠኘው ማህበረሰብ የሴት ልጅ ውስጣዊ ማንነት የሚለካው በውጭ ከወንዶች ጋር ባላት ግንኙነት ነው፡፡ ከወንድ ልጅ ጋር ሳቅ፣ ጨዋታና ቀልድ የምታበዛ ከሆነ በቀላሉ በፍቅር የምትሸነፍና ለዝሙት የምትጋለጥ ተደርጋ ትታሰባለች፡፡ በተለይም ዲያቆን ከሆነ ስልጣነ ክህነቴን ታስፈርሳለች በሚል እሳቤ እንደዚች አይነት ሴትን ማግባት ይፈራል፡፡

ይህችን አይነት ሴት በማህበረሰቡ ለትዳር መምረጥ ከትዳር በኋላ ባለው ህይወት ከባሏ ላይ ሌላ ወንድ ደርባ ታጣላዋለች፡፡ ለትዳር የሚፈልጉ ወንዶች ወይም የወንድ ቤተሰቦች ለጋብቻ የፈለጓትን ሴት ማንነት ያጣራሉ፡፡ ስለ ልጅቱ ሌላ ሰው ሲጠይቁም እችስ ከማንም ጋር መቆም ነውስራዋአንዱንም አንዱንም ስትል የኖረች አትለምድልህም፤ ተረጋግታ አትቀመጠም፤ በየሄደችው እያወራች ስራ ትፈታለች የሚል ምላሽ ያገኛሉ (ቃለ መጠይቅ፣ ቄስ ገባሁ ታገለ፣ 12/06/2013)፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ሴት ልጅ ከማግባቷ በፊት ማድረግ ከሌሉባት ነውሮች ውስጥ ለአደጋ ያጋልጣሉ ተብለው ከሚታሰቡ ተግባሮች ራሷን አለማቀብ ነው፡፡ ሴት ልጅ ለአቅመ ሄዋን ከደረሰች በኋላ እናት አባት አጭቶ ያጋባታል፡፡

ለጋብቻ የጠየቃት ካለና የምትፈልገው ከሆነ ለቤተሰብ ታሳውቃለች፡፡ ከዚያ በኋላ ዘሩንና ሃይማኖቱን አጣርተው እነሱን የሚመጥናቸው ከሆነ ያጋቧታል፡፡ ከዚህ ውጭ በሆነ መንገድ ከቤተሰቦቿ ቤት በመውጣት ከወንድ ልጅ ጋር ኮብልላ ምትሄድ ከሆነና የተወሰኑ ወራትን አሳልፋ ምትመጣ ከሆነ በማህበረሰቡ የተከለከለ ነው፡፡ ለዚህም ምክንያት ኮብልላ የሄደች ሴትከወሰዳት ወንድ ጋር ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ወንዶች ጋርም ግንኙነት ይኖራታል፤በአንድ አትወሰንም ተብሎ ይታሰባል፡፡

በዚህም ለተለያዩ በሽታዎች ተጋላጭ ሆና ትመለሳለች የሚል አሳቤ አላቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከማህበረሰቡ ወግና ባህል ያፈነገጠችና ከእናት አባት ትዕዛዝ የወጣች ለመሆኗ መገለጫ ተደርጎም ይወሰዳል፡፡ በመሆኑም እንደዚህ አይነት ሴት ለትዳር አትፈለግም (ቃለ መጠይቅ፣ ሙሉየለት እንየው፣07/06/2013/)፡፡

በማህበረሰቡ ሴት ልጅ ለአቅመ ሄዋን ከደረሰች በኋላ በተለያዩ ግብዣዎች ሰርግ፣ ማህበር፣ ቤት ስራ እና ሌሎችንም ቀናት ሂዳ እንድታድር አይፈቀድላትም፡፡ ጠላ ወይም እንጀራ ተሸክማ ከእናቷና ከአባቷ ጋር አብራ ሂዳ ስትጫወት ቆይታ ከእናት አባቶቿ ቀድማ ወይም ከእናት አባቶቿ ጋር በጊዜ ወደ ቤት ትመለሳለች፡፡ ከሄደችበት ቤት ማደር የምትችለው ወንድም ወይም አጎት አብሯት (ዘመድ የሆነ ሰው) የሚያድር ከሆነ ብቻ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ካሉ ከፆታዊ ትንኮሳዎች ይጠብቋታል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ ሴት ልጅ ባዳ ቤት ሂዳ ማደር ከቤት ያለ ጎረምሳ ባዳ ስለሆነ እንደ ዘመዷ ከመንከባከብና በስርዓት ከመሸኘት ይልቅ ይደፍራታል፤ እሱ ባይደፍራት እንኳ ለማታውቃቸው ጓደኞቹ አሳልፎ ይሰጣታል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በዚህም ምክንያት ላልተፈለገ እርግዝና በመጋለጥ ትወልዳለች፡፡ ከዚህ በኋላ ላለው ህይወቷ አግብታ ለመኖር ባል አይመጣላትም ተብሎ ይታሰባል፡፡ በእናት አባት ትዕዛዝ ስር ያደረችና ከዝሙት ራሷን ጠብቃ የኖረች ሴት ለመልካም ትዳር ትታጫለች (ቃለ መጠይቅ፣ ድሉ ተፈራ፣ 06/06/2013)፡፡

ዘመድ ካልሆነ ሰው ቤት የሄደች ልጅ ዘመዷ ካልሆነ ጎረምሳ ጋር አብራ መጨፈርም እንደ ነውር ይቆጠራል፡፡ ታዳሚውም እንደ ባለጌ በመቁጠር በቃል ግጥም ይሰድባታል፡፡ ዘመድ ከሆነ ሰው ጋር ብትጨፍር ግን ‹‹ኸረ እነዚህ ልጆች ምንና ምን ናቸው የጀሮ ጉትቻ የአንገት መስቀል ናቸው›› በማለትቃል ግጥም ይገጥሙላቸዋል፡፡ የቅርብ ዝምድና ያላቸው መሆኑ በዚህ ይታወቃል፡፡

በአጠቃላይ ሴት ልጅ ራሷን ለአደጋ ከሚያጋልጡ ችግሮች አለማቀብና በመዝናኛ ቤቶች መታየት፣ መብላትና መጠጣት በሚሉትን ነውሮች ስር የተጠቃለሉት ሴት ልጅ በድንግልና እንድትቆይ ለማድረግ፣ ከሚደርሱባት ማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ቀውሶች ቀድማ ራሷን ለመከላከል፣ ፆታዊ ትንኮሳዎች የሚከሰቱባቸውን መንገዶችና ቦታዎች ለማስተማር ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ አላቸው፡፡

### 5.1.2. የሴትና ወንድ ተጋቢ ቤተሰቦች የሚያከብሯቸው ነውሮች

በቅድመ ጋብቻ በትጭጭት ላይ ያሉ ተጋቢዎችና የተጋቢ ቤተሰቦች የሚያከብሯቸውና የሚፈሯቸው ነውሮች አሉ፡፡ እነዚህ ነውሮች ተጋቢዎቹ የጋብቻ ስርዓታቸውን እንዲፈፅሙ፣ በወንድና በሴት ተጋቢ ቤተሰቦች መካከል ግጭት እንዳይከሰት ሲባል የሴትና ወንድ ተጋቢ ቤተሰቦች የሚያከብሯቸው ናቸው፡፡ ነውሮቹ ቢጣሱ የመደባደብ፣ ራስን የማጥፋት፣ ከእድርና ከእቁብ መለየት፣ የዕለተ ጋብቻ ስርዓት በተፈለገው ስርዓትና በተፈለገው ስዓት አለማለቅ እንዲሁም ለታዳሚዎች መጉላላት መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ነውሮቹ አብዛኛውን ጊዜ ሲጣሱ አይስተዋሉም፡፡ የሴትና ወንድ ተጋቢ ቤተሰቦች ከሚያከብሯቸውና ለመተግበር ከሚፈሯቸው ነውሮች ውስጥ ከመሰል ሃይማኖቶች ውጭ መተጫጨትና መጋባትን፣ሴት ልጅ በጋብቻ ውል አፈፃፀምና ውሳኔ ላይ መሳተፍ፣ ዕለተ ጋብቻ ቀኑ ከተወሰነ በኋላ የሴት ወይም የወንድ ተጋቢ ቤተሰቦች ጋብቻውን መተውና በሁለቱም ፆታዎች በኩል ያሉ ተጋቢ ቤተሰቦችን ማንነትን መንካት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

### 5.1.2 .1. ከመሰል ሃይማኖት ጋር መተጫጨትና መጋባት

ከመስል ሃይማኖት ጋር መተጫጨትና መጋባት በማህበረሰቡ የሚከበር ተግባር ነው፡፡ በተጠኝው ማህበረሰብ ውስጥ የክርስትና ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታዮች ብቻ ይገኙበታል፡፡ የዳንግላ ወረዳ ማህበረሰብ በዳንግላ ከተማ ውስጥ ከሚገኙ ከእስልምናና ከፕሮቴስታንት ተከታዮች ጋር ተወዳጅተው አብሮ በመብላት በመጠጣት ሀዘንና ደስታቸውንይጋራሉ፡፡ ነገር ግን በተመረጡት4 ተተኳሪ ቀበሌዎች ከሚመስላቸው ሃይማኖት ውጭ የጋብቻ ስርዓታቸውን አይፈፅሙም፡፡ ጋብቻውን ተቀምጦ የሚያፀድቅ አጋቢ ዳኛም የለም፡፡ በእነዚህ ቀበሌዎች ውስጥ የአንድ ሰው ልጅ ሃይማኖቱን ቢቀይር ወይም ብትቀይርና ቤተሰቦቹ ከሚከተሉት ሃይማኖት ውጭ ለማግባት ቢያስቡና አጋቡኝ ብለው ቢጠይቁ ቤተሰብ ፈቃደኛ አይሆኑም፡፡ ከእናት አባታቸው ትዕዛዝ ወይም ከማህበረሰቡ አፈንግጠው መኖርና መጋባት ግን ይችላሉ፡፡

የሴት ቤተሰብና የወንድ ቤተሰብ ለጋብቻ የተፈላለጉት ልጆቻቸው ሃይማኖት የተለያየ መሆኑን ካጣሩና ከአወቁ በኋላ የጋብቻን ውል ለመፈፀም አይሄዱም፡፡ ከሄዱ በኋላ ቢሰሙ እንኳ እርስ በእርሳቸው ባለመግባባት ተመልሰው ይመጣሉ፡፡

አብዛኛውን ጊዜ ይህ አይነት ችግር የሚፈጠረው ተዋደው ቆይተው ቤተሰቦቻቸው ጋብቻቸውን እንዲፈፅሙላቸው በሚጠይቁ የተማሩ ወጣቶ ላይ ነው (ቃለ መጠይቅ፣ ድሉ ተፈራ፣ 06/06/2013)።

ቤተሰቦቻቸው የልጆቻቸውን ሀሳብ ተቀብለው ካጋቧቸውና ሃይማኖታቸውን ከቀየሩ ልጆቻቸው ጋር ግንኙነታቸውን ከቀጠሉ የአካባቢው ማህበረሰብ ከእነሱ ጋር ማህበራዊ ግንኙነቶች ማድረግ የተከለከለ ነው። ከማይመስላቸው ሃይማኖት ጋር በጋብቻ የተቆራኙ ቤተሰቦችን የሾሙትን ጠላና የጋገሩትን እንጀራ የሚበላላቸው የለም። ለቤተክርስትያን አስራት በኩራት ብለው የሚያመጡት ገንዘብም በቀበሌ ህዝብ ተቀባይነት የለውም። ምክንያቱም እንደ ልጆቻቸው ሃይማኖታቸውን ቀይረው ይሆናል በሚል እሳቤ ነው። ሃይማኖቱን የቀየረ ሰው ደግሞ ሲሞት መቃብሩ እሽ ብሎ አይቆፈርም፤ መሬቱ መቆፈሪያውን ወደ ላይ እያስፈነጠረ ይጥለዋል የሚል እምነት አላቸው (ቃለ መጠይቅ፣ በቃሉ ፈጠነ፣ 13/06/2013)።

ነውሩ እንደ ተጠኘው ማህበረሰብ አስተሳሰብ ተቀባይነት ያለው ቢሆንም አብሮነትን ከማጠናከርና የሃይማኖት ብሄርተኝነትን ከማስፋፋት አኳያ ግን አሉታዊ ጎን አለው።

### 5.1.2 .2. ሴት ልጅ በጋብቻ ውል አፈፃፀምና ውሳኔ ከመሳተፍ መቆጠብ

ሴት ልጅ መጋብቻ ውል አፈፃፀምና ውሳኔ ላይ ከመሳተፍ መቆጠብ አለባት። ወንድ ቤተሰቦችም ሆነ የሴት ቤተሰብ ሴቶች በጋብቻ ውል አፈፃፀምና ውሳኔላይ መሳተፍ የሚደገፍ ተግባር አይደለም። የሴትም ሆነ የወንድ ተጋቢ ቤተሰቦች ለተጋቢዎቹ በሚያቀርቡት ሀብት አቀራረብና አሰጣጥ ሁኔታ በመካከላቸው አለመግባባቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ። በዚህ ስዓት የሴት ቤተሰብም ሆነ የወንድ ቤተሰብ ሴቶችበሀብት አቀራረብና አሰጣጥ ዙሪያ ቅሬታ ቢኖራቸው አስተያየት መስጠትና ቅሬታቸውን ማቅረብ የተከለከለ ነው። ቅሬታቸውን ማቅረብ የሚችሉት ለወንድ ልጅ ወይም ለሌላ ሰው መልእክቱን በስውር በመላክ ነው። የተላከው ሰውም ለልጅቱ ወይም ለልጁ አባት ሂዶ ይናገራል። የልጅቱ ወይም የልጁ አባት ጉዳዩን የራሱ ቅሬታ አስመስሎ ይናገራል። ሚስቴ መልዕክት ልካ አልስማማ ብላለች ብሎ መናገር በራሱ እንደ ነውር የሚቆጠር ነው።

ከዚህ ውጭ በሆነ መንገድ ከተቀመጡት ሽማግሌዎች መኃል ገብታ ብትናግር በሴት የተነሳ ነገርናጠብ ቶሎ አይበረድም። በሴት ልጅ ተመስሎ ሰይጣን በነገራቸው መካከል ገብቶ መልካሙን ሀሳባቸውን በመበተን እርስ በርስ አለመግባባትን ይፈጥራል።

ነገሩ ተባብሶ ሽማግሌዎችም ሆነ የተጋቢ ቤተሰቦቻቸው ይሄዳሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡ በተለይም በውሳኔ አሰጣጡና አፈፃፀሙ ወጥታ የተናገረችው የሴት ቤተሰብ ከሆነች ልጇም ነገረኛና ተሳዳቢ እንደሆነች ስለምትታሰብ ጋብቻውን ሊተውት ይችላሉ (ቃለመጠይቅ፣ ድሉተፈራ፣ 06/06/2013)፡፡

ይህ ነውር ውል[1] በሚጨረስበት ቀን ብቻ ሳይሆን በዕለተ ጋብቻ ቀጠሮ ቀን ጭምር የሚሰራ ነው፡፡ ነውሩበተጠኘው ማህበረሰብ የጋብቻ ስርዓቱን የሚያስተጓጉሉ ድርጊቶችን ለመከላከል የሚጠቅምነው፡፡ በጋብቻ ውል አፈፃፀም ቀን ለግጭት መፈጠር መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ድርጊቶችን በማስወገድ የጋብቻው ማፅደቂያ አንድ መንገድ በማድረግ የተጠቀሙበት ነው፡፡ምክንያቱም ሴት ልጅ በንግግሯ ቶሎ ስሜታዊ ስለምትሆን የጋብቻውን ስምምነቱ የተመለከቱ ነገሮች እንዳይበላሹ ብለው በማሰብ ስለሚያከብሩት ነው፡፡ ይህ ነውር የሴትን ልጅ ፊት ለፊት ቀርቦ የመናገር (ቀጥተኛ ተሳትፎ) ከማረጋገጥ አንፃር የጎንዮሽ ጉዳት ቢኖረውም ተጠኘው ማህበረሰብ ግን እንደ መልካም ጎን አይቶ እየቀጠለ ነው፡፡

### 5.1.2 .3. የሴትም ሆነ ወንድተጋቢ ቤተሰቦች የዕለተ ጋብቻ ውሳኔን ከመተው መጠንቀቅ

በሁለቱም ፆታ በኩል ያሉ ተጋቢዎች ጋብቻቸው ከመፅደቁ በፊትአለመስማማቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ በሚፈጠሩ የተለያዩ ችግሮች ምክንያት የጋብቻ ሀሳባቸው ፍፃሜ ላያገኝ ይችላል፡፡ ለጋብቻው አለመፅደቅ በሴትና ወንድ ተጋቢ ቤተሰቦች መካከል የሃይማኖትና የዘር አለመመሳሰል እንዲሁም የስነ ምግባር ችግሮች መኖር እንደ ምክንያት ይጠቀሳሉ፡፡ የጋብቻ ውል ከተጨረሰ በኋላ በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ዕለተ ጋብቻው ፍፃሜ እንደማያገኝ የሴት ቤተሰቦች ለወንዱ ወይም የወንድ ቤተሰቦች ለሴት ቤተሰቦች መላክ የሚቻለው ቀኑ ከመድረሱ በፊት ነው፡፡

---

[1] የውል ቀን እና የቀጠሮ ቀን ልዩነት አላቸው፡፡ የውል ቀን የመጀመሪያው የጋብቻ ስርዓት አፈፃፀም ሲሆን የወንድ ቤተሰቦች መጀመሪያ ከሴቲቱ ቤተሰቦች ከሄዱ በኋላ በሌላ ጊዜ የሴት ቤተሰቦች በፈንታቸው ከወንድ ቤተሰብ በመሄድ የሚያቀርቡትን ንብረት የሚተያዩበት ቀን ነው፡፡ በዚህ ቀን የሽማግሌዎች ብዛት ሶስት ነው፡፡ ይህ ቀን በሰላም ከተጠናቀቀ በኋላ የሰርጉ ቀን ተወስኖ ከሙሽራው ቀድመው በመሄድ ጋብቻውን በሰነድ የሚያፀድቁበት ቀን የቀጠሮ ቀን ይባላል፡፡ በዚህ ቀን የሽማግሌዎች ብዛት ከ 3-5 ይደርሳል፡፡በቀጠሮው ቀን የነበሩ ሽማግሌዎችም ቀጣሮች ወይም አጋቢ ዳኞች ይባላሉ፡፡ መረጃው በቃለ መጠይቅ ወቅት በቀን 06/06/2013 ከድሉ ተፈራና በቀን 03/06/2013 ከከፋለ ነጋ የተገኘ ነው፡፡

ቀኑ ከመድረሱ በፊት ቀደም ብሎ ካሳወቀ የሚፈጠር ችግር የለም፤ ነውርም አይደለም፡፡ የዕለተ ጋብቻ ዝግጅት ከተጀመረ በኂላ ከሁለቱ ተጋቢ ወገኖች መካከል በአንዱ በኩልጋብቻውን እንደማይፈልጉት መግለጽ በተመረጡት ተጠኝ ማህበረሰብ ከፍተኛ ችግር የሚያደርስ ነውር ነው፡፡ በመሆኑም አብዛኛውን ጊዜ ሲጣስ የማይታይ ነው፡፡ ሴቷ ወይም ወንዱ ተጋቢዎች ጋብቻው እንዳላስደሰታቸው ቢገልፁና ማግባት ባይፈልጉ የጋብቻውን ቀን እንደምንም መፈፀም እንዳለባቸው ቤተ ዘመዱ ይመክራል፡፡

እንደዚህ አይነት ችግሮችን የሚፈጥሩት የተጋቢዎችን ቤተሰቦች የተጣላ ወይም በሁለቱ ወገን ጋብቻ መደረጉ ያላስደሰታቸው ሰዎች እንደሆኑ ይታመናል፡፡ ነውሩ ሲጣስ ከኢኮኖሚ አኳያ ከፍተኛ ኪሳራ የሚያደርስ ሲሆን ምን ሰምቶብኝ? ምን ጎድሎኝ? ለምን ከእኔ ጋር መጋባቱን ጠላው? የዕለተ ጋብቻው ዝግጅት ሳይጀመር ማይነግረኝ? የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳትበሁለቱ ወገን መካከል ጥላቻ ይነሳል፡፡ ከሁለቱ ወገን በተጨማሪ ለምን አመጣህብኝ በሚል አጭተኛው ይወቀሳል (ቃለ መጠይቅ፣ በቃሉ ፈጠነ፣ 13/06/2013)፡፡

አጭተኛው የወንድንም የሴትንም ቤተሰቦች ከመሀል ሆኖ ይመክራል፡፡ ዕለተ ጋብቻው እንዲፈፀምም የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል፡፡ ይህ ሁሉ ጥረት ተደርጎ የሴት ወይም የወንድ ወገን በእምቢታቸው ከፀኑና ጋብቻውን አልፈልግም ካሉ አልፈልግም ያለውን ወገንለበቀል ይነሳሱበታል፡፡ አቶ በቃሉ ፈጠነንበቀን 13/06/2013 ባደረግሁላቸው ቃለ መጠይቅ ሲገልፁ፡- ‹‹በዚህ ቀን የተጋቢዎችና እናት አባቶቻቸው መዘባበቻ ከሚሆኑት ቢሞቱ ይሻላቸዋል፡፡ ታንቀው ሚሞቱ ልጆችም አሉ›› በማለት የነውሩን ክብደት ገልፀውልኛል፡፡ ይህ ነውር ከሚጣስባቸው ምክንያቶች ውስጥ በልጅቱ ወይም በልጁ የተለያዩ አሉባልታዎች መሰማት አንዱ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት የጋብቻ ቀን እንደቀረ ከዚህ በታች የቀረበው ተረክ ያስረዳል፡፡

> የዛሬ ሁለት አመት የአበራች ልጅ የሞተች ተደግሶ የሰርጉ ቀን ተቆርጦ ሲጠባበቁ የወንድ ቤተሰቦች ልትሰጠን የነበረቻትን ልጅህ ትተናታል፡፡ ፈቃደኛ ከሆንህ ትንሿን ልጅ ስጠን ብለው ላኩበት፡፡ ከዚህ በኂላ የልጅቱ አባት የሰጠሁህና ውል የጨረስነትልቋን ነው ብሎ እምቢ አለ፡፡ ለምን እንደተዋት በሽማግሌ ሲይዘው ሶስት ጊዜ ወልዳ ጥላለች አሉኝ ብሎ ምላሽ ሰጠው፡፡ በውሸት የልጅቱን ስም ያጠፋውነገረ ሰሪ ሰው ወዲያው ታወቀ፡፡ ልጅቱም በንዴት ታንቃ ሞተች፡፡ አንገቷን ደፍታ እናት አባት ምታገለግሊቱን ልጅ ነገረ ሰሪ ክፉ ስም ሰጣት፡፡ ወዲያው ሊጋደሉ በሽማግሌ ምክር ነው የቀሩት፡፡

ነገረ ሰሪው እና የሴት ቤተሰቦች እስካሁን በጠላትነት እየተያዩ አብረው አይበሉም፤አይጠጡም (ቃለ መጠይቅ፣ አዲሱ አረጋ፣ 04/06/2013)፡፡

ሁለት ተጋቢዎች ዕለተ ጋብቻቸውን በጉጉት ይጠብቃሉ፡፡ ለጋብቻ የሚያስፈልጋቸውን ቁሳቁስ ሁሉ ያሟላሉ፡፡ ውስጣቸውም በሃሴት ይሞላል፡፡ በመሆኑም ይህ ደስታቸው በመጥፎ ዜና ሲሞላ የሚያሳድረውን ስሜት መገመት አያዳግትም፡፡ በተለይም ሴት ልጅ ከዚህ በኋላ ያላት ስም ጥሩ አይሆንም፡፡ የትዳር አጋር እስከማጣት ትደርሳለች፡፡በመሆኑም የነውሩ መኖር በተጋቢዎቹ የስነ ልቦና መጎዳት ምክንያት ከሚመጣ መጥፎ ውሳኔና ችግር ለመታደግ ይጠቅማል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የጋብቻን ጥያቄ መሰረት ያደረገ ግጭት እንዳይፈጠር በማድረግ የጋብቻ ስርዓት ህግና ደንብ ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡

## 5.1.2.4. በሁለቱም ፆታ በኩል ያሉ ተጋቢ ቤተሰቦችን ማንነት ማክበር

የጋብቻ ውል ሲፈፀም እንደሴቷ ፍላጎትና የወንድ ቤተሰብ እንዳለው የሀብት መጠን ልጅቱ በባህሉ መሰረት ማጫዋን (ጥሎሽ) ብር ሊሰጣትወይም ወርቅ ሊያስርላትና አልባሳትን ሙሉ ሊችል ይስማማሉ፡፡ በውሉ መሰረት ሙሉውን ክፍያ ባያቀርብ ወይም ከልጅቱ ፍላጎት ውጭ በሆነ መንገድ ደረጃውን ያልጠበቀ ቀለበትና አልባሳት አለብሳለሁ ቢል በልጅቱ ቤተሰቦችና እና በሚያገባት ልጅ መካከል አለመግባባቶች ይፈጠራሉ፡፡ በዚህ ሰዓት የሚያገባት ባል ወይም ከእሱ ጋር የመጡ ቤተሰቦቹ ክፉ ቃል ከአንደበታቸው ከወጣ ጋብቻውን ለመሰረዝ ባያደርስም ለጋብቻው ቀን ታዳሚን የማጉላላት ችግር ይገጥማል፡፡

በቀን 14/06/2013 በእጅጉ ታየ ቤት ወጣት ታረቀኝ አለምነህ እና ወጣት ስመኝ እጅጉ ሲጋቡ የዕለተ ጋብቻን ነውሮች በምልከታ ለመሰበሰብ በሄድሁበት አጋጣሚ ጉዳዩን እና የታዳሚውን መጉላላት ተምልክቻለሁ፡፡ ቀጣሩ ከሙሽራው በፊት ከመጣ በኋላ አዲሱ የተባለው የሙሽሪት ወንድም ምን ብላችሁ መጣችሁ እህቴን አትወስዱም፡፡ ጌጣጌጡን በሚገዛበት ሰዓትበተፈጠረ የቀለበት ደረጃ ምርጫ አብሮት የመጣው ዘመዱ ‹‹የሰይጣን ዘር›› ብሎ ተሳድቧል፡፡ ስለዚህ የኛዘር ለእናንተ ሰይጣን ከሆነ ተመልሳችሁ ሂዱ በሚል በተፈጠረ አለመግባባ በ7 ስዓት የተጀመረ ከምሽቱ 10 ስዓት ድረስ በመቆየት ቀጣሩ፣ ሚዜና ሙሽራው ሲጉላላ ተመልክቻለሁ፡፡

ቀጣሮች የጋብቻውን የውል ሰነድ አፅድቀው ከጨረሱ በኋላ ሙሽራይቱን በ12፡30 ይዘው ሂደዋል፡፡ ግጭቱ የተፈታው ተሳዳቢው በሌላ ጊዜ እንዲቀርብና እንዲጠየቅ የሙሽሪትን ወንድም ይቅርታ ጠይቆ እንዲታረቁ በሚል ነው፡፡ በዚህ ነውር ምክንያት ታዳሚው ሙሽሪትን እልል ብለን ሳናወጣ አንሄድም ቶሎቶሎ ጉዳዩን እልባት ስጡት በሚል ሲጉላላ አምሽቷል (ምልከታ፣ 14/06/013)፡፡

[2]በሁለቱ ተጋቢ ቤተሰቦች መካከል ያለውን ማንነት ለመንካት መፍራት ወይም ነውሩን ማክበር የዕለተ ጋብቻዕለት ታደሚውን በሰዓት ወደ እየቤቱ ለመሸኘት ሙሽራውም ሙሽሪትን ይዞ ከቤተሰቦቹ በጊዜ እንዲደርስ ለማድረግ የጋብቻ ቀኑ ያለ መጉላላት እንዲፈፀም ይጠቅማል፡፡ ነውሩ ተጋቢዎችም ሆነ የተጋቢ ቤተሰቦች በአነጋገር ስርዓታቸው እንዳያፈነግጡ የመቆጣጠር ፋይዳ አለው፡፡

### 5.1.3. የቅድመ ጋብቻ አለባበስና አጊያጊያጥ ነውሮች

በመረጃ ስብሰባ ወቅት የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመለከቱት ቅድመ ጋብቻ አለባበስና አጊያጊያጦች የወጣቶችን ማንነት ለመለየት የሚያስችሉ ናቸው፡፡ ማህበረሰቡ የወጣቶችን የስነ መግባር ሁኔታና ለወደፊት ያላቸውን አቋም በአለባበሳቸው ይለካል፡፡

#### 5.1.3.1. ሌባንና ግጭት ፈላጊ አካላትን የሚለዩባቸው አለባበስ /አጊያጊያጥ ነውሮች

ማህበረሰቡ የሰዎችን አለባበስንና አጊያጊያጥ በማየት ሌባንና ግጭት ፈላጊን አካላትን መለያ መስፈርት አድርጎም ይጠቀምበታል፡፡

ለምሳሌ በማህበረሰቡ የአንድን ሰው ቤት ከብት ከቤት አውጥቶ ለመውሰድ ፈልጎ የቤታቸውን ሁኔታ ለመሰለል የፈለገ ሰውና ለመስረቅ የመጣ ሰው ከሆነ ቀይ ወይም ነጭ ልብስ አይለብስም፡፡

---

[2]ለጋብቻ ቀን አለመሳካት መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ነውሮችቅድመ ጋብቻ  በሚለው ርዕስ ስር የቀረቡበት ምክንያት የሚፈፀሙት ከጋብቻ በፊት ሆነው ጠቀሜታቸው ግን ለጋብቻ ቀኑ መሳካት የጎላ በመሆኑ ነው፡፡ ከጋብቻ በፈት ያሉ ነውሮች ካልተከበሩ የጋብቻ ቀን የሚለው አይታሰብም፡፡ መረጃው ከአቶ እጅጉ ታየ ቤት በተደረገ የጋብቻ ቀን ምልከታ፣ ከአቶ በቃሉ ፈጠነና ከአቶ አዲሱ አረጋ ለጋብቻ ቀን አለመሳካት ምትጠቅሷቸው ምክንያቶች ካሉ በማለት ባቀርብሁላቸው ጥያቄዎች በተገኙ ምላሾች የተገኘ ነው፡፡

ጠቆር ያለ ቡኒ ልብስ ለብሶ ይመጣል፡፡ አለባበሱም ዘርፈፍ አድርጎ ተከናንቦ ነው፡፡ይህንን የሚያደርገው በቀላሉ እንዳይለይ በመፍራት ነው፡፡ እንደዚህ አይነት አለባበስን የለበሰን ሰው አልፎ የሄደበት ቤት ባለቤት ሲያይ ተጠንቀቁ ተከናንቦ ጥቁር ለብሶ የሄደ ሰው አለ ሌባ ነው የመሰለኝ ብሎ ለልጆቹ ከብቶችን እንዲጠብቁ ያስጠነቅቃል፡፡ ተከናንቦ ጥቁር ቡኒ ለብሶ ለእንግድነት ከሰው ቤት ለመሄድ ቤቱ ጠፍቶት እሚጠይቅ ሰው ቢኖር እንኳ የማህበረሰብ አካል የሚነግረው ማንነቱን ካጣራ በኋላ ነው፡፡ በቀላሉ የሰውን ቤት አያሳዩም፡፡ ምክንያቱም አለባበሱን በማየት ሰውየው ሰላማዊ ሰው አለመሆኑን ስለሚጠራጠሩ ነው፡፡

የአለባበስና አጊያጊያጥ ነውሮች ሲጣሱና ነውሩተለውጦ ሲጠፉ ማንነትን ገላጭ የሆኑ የተጠኘው ማህበረሰብ ባህሎች ይጠፋሉ፡፡ ለምሳሌ አሁን ላይ አልቦ (ከእግር የሚደረግ ጌጥ)፣ እርባን (ከአንገት የሚደረግ ጌጥ)፣ አርባ ሽንሽን (የሴቶች የልብስ ስፌት አይነት)፣ ተጨባብ (በጎንና በጎን ክፍት የሆነ የወንድ ህፃናት ልብስ)ና አጭር ሱሪ ጋር የተያያዙ አለባበስና አጊያጊያጥ ነውሮች በመጥፋት ላይ ያሉ አንዳንዶችም የጠፉ አለባበስና አጊያጊያጦች ናቸው፡፡ አሁን ላይ በተለያዩ ከተማዎች የሚታዩ ኢትዮጵያዊ ባህል የማይመስሉ አለባበሶች የሚታዩት ምናልባትም ለነውሮች ቦታ አለመስጠታቸውና ነውሮችን እንደ ኋላቀር ባህል መታየታቸው ሊሆን ይችላል፡፡

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞረው በተመረጠው ማህበረሰብ ሰዎች ምን አይነት ስነ መግባር እንዳላቸው፣ ምን መስራት እንደፈለጉ፣ አቋማቸው ምን እንደሆነ የራሳቸው የሆነ የማንነታቸው መለያ አለባበስና አጊያጊያጥ አላቸው፡፡ በተጠኘው ማህበረሰብ አንድ ወጣት አለባበሱና የፀጉር አስተካከሉ ታይቶ ሌባ፣ ተደባዳቢ፣ ጭምትና ሰነፍ መሆን አለመሆኑ ይለያል፡፡ አዛውንት ሴቶችም ልክ እንደዚሁ አለባበሳቸው እድሜያቸው የሚመጥን ካልሆነ እንደ ነውረኛ ይቆጠራሉ፡፡ አጠቃላይ ከማህበረሰቡ አለባበስና ባህል ከሚፈቅደው ውጭ መልበስ ነውር ነው፡፡ ተረፈ ስዩም የተባሉ መረጃ አቀባይ ‹‹ከአባት ባህልና ከበሬ ወርች አትለፍ›› የሚለውን አባባል በመናገር ከባህላቸው የወጣና ያፈነገጠ አለባበስና አጊያጌጥ ያዩባቸውን ወጣቶች ባለጌና ስርዓት የሌላቸው አድርገው እንደሚቆጥሩ ገልጸውልኛል፡፡

በመሆኑም ተጠኘው ማህበረሰብ ቅድመ ጋብቻ ላይ ያሉ ወጣቶችን አለባበስና አጊያጊያጣቸውን በማየት ደረጃ ይሰጣቸዋል፡፡ መጥፎና ጥሩ ስነ መግባር ያላቸውን ልጆች ይለዩበታል፡፡ ለጋብቻ ሲመረጡም የአለባበስና የአጊያጊያጥ ሁኔታቸውን አንድ መስፈርት አድርጎ ይወስዳል፡፡

የሰዎችን ማንነት ለመለየት ከሚያገለግሉ የአለባበስና አጊያጊያጥ ነውሮች ውስጥ ክንብንብን ሳያወርዱ/እንደተከናነቡ ሰላምታ መስጠት፣ ሱሪን ዝቅ አድርጎ መታጠቅና ፀጉርን አንጨፍርሮ መጓዝ የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

‹‹ራሱን ተከናንቦ ቂጡን ገለበው›› (ቃለ መጠይቅ፣ ከፋለ ነጋ፣ 03/06/2013)፡፡

በዚህ ምሳሊያዊ አነጋገር የተገለፀው ሁለት አይነት ነውር ነው፡፡ የመጀመሪያው ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው መከናነብ የሰላማዊ ሰው መለያ የሆነውን የሚገልጽ ሲሆን ሁለተኛው ሱሪን ዝቅ ማድርግ የሚለውን ነውር ለመግለፅ የገባ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ክንብንብን ሳያወርዱ ሰላምታ መስጠት ወይም ከሰው ፊት ሲደርሱ ተከናንቦ ማለፍ የመጥፎ ስነ ምግባር መገለጫ ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሰው ምሳሌያዊ አነጋገርም የሚያመለክተው ወጣቱ ወይም ሰውየው ሁለት ነውር መጣሱን ነው፡፡ ምሳሊያዊ አነጋገሩ ጥልቅ ትርጉም ያለው ነው፡፡ በማህበረሰቡ ነውር የተባለውን ተከናንቦ መልበስ የሚለውን በመግለፅ ባህሉን እና የማህበረሰቡን ህግ አላይም አላከብርም ያለውን የወጣቱን ትዕቢተኛና ከባህሉ ያፈነገጠ መሆኑን ‹‹መከናነብ›› በሚለው መረዳት ይቻላል፡፡

በአጭሩ ወጣቱ ወደና ፈቅዶ ነውሩን ፈፅሟል፤ ህሊናው ባህሉን ከማሰብና የአለባበስ ስርዓቱን ተከትሎ ሰላምታ ከመስጠት ይልቅ እንደ ጥሩ ነገር ተቀበሎ የሱ መገለጫ አድርጎ ወስዶታል የሚል መልዕክት አለው፡፡ ሌላው ‹‹ቂጡን ገለበው›› የሚለው ሌላ መልእክት ያለው ነው፡፡ ቂጡን ገለበው ሲል እራቁትነትን ያስረዳል፡፡ እራቁት መሆን ደግሞ በአለባበሱ ብቻ ሳይሆን በአስተሳሰቡም ጭምር ባህሉን የሚፈቅደውን ባለማድረጉ ማንነቱን ያጣ መሆኑን እንረዳበታለን፡፡

ሰዎች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ሲንቀሳቀሱ የተለያየ ሰዎችን ያገኛሉ ወይም ለመልዕክት ከተለያየ ቤት ተልከው ከሰው ቤት ይሄዳሉ፡፡ በዚህ ሰዓት ወንድም ይሁን ሴት ክንብንባቸውን ገልጠው ጎንበስ በማለት ሰላምታ ይሰጣሉ፡፡ ሰላምታ ተቀባዩም ጎንበስ ብሎ ስላምታውን ይቀበላል፡፡

ሰላምታ ተቀባዩም ሆነ ሰላምታ ሰጭው የተከናነበውን ልብስ ከራሱ አውርዶ መሆን አለበት፡፡ ክንብንብን ሳያወርዱ ሰላምታ የሚሰጥ ከሆነ ትዕቢተኛ እንዲሁም ባለጌና ምግባረ ብልሹ እንደሆነ ይቆጠራል (ቃለ መጠይቅ፣ ከፋለ ነጋ፣03/06/2013/)፡፡

ይህ ነውር የማህበረሰቡን የሰለምታ አሰጣጥ ባህል በማስቀጠል መከባበርንና ትህትናን ለትውልዱ ለማስተማር ይጠቅማል፡፡ ምክንያቱም ክንብንብ አውርዶ ሰላምታ የሚሰጥ ሰው በማህበረሰቡ ጥሩ ስነ ምግባር ያለው እንደሆነ አንዱ መለያቸው ነው፡፡

ከላይ በምሳሌያዊ አነጋገሩ ትንታኔ ለመግለፅ እንደተሞከረው በማህበረሰቡ ሱሪን ዝቅ አድርጎ መታጠቅ የተከለከለ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ሱሪ ሲታጠቁ ገንዘብ ያለው ቀበቶ በመግዛት ሱሪውን ከፍና ጠበቅ አድርጎ ይታጠል፡፡ የሌለው ከተለያዩ ልብሶች በማዘጋጀት ይታጠቃል፡፡ ህፃናት ከሆኑ ደግሞ የሱሪ መታጠቂያ ቁልፍ ሱሪው ሲሰፋ አብሮ ይተከልላቸዋል፡፡ በመሆኑም በእነዚህ አማራጮች ተጠቅመው ሱሪያቸውን ይታጠቃሉ፡፡ ከዚህ ውጭ በሆነ አለባበስ ሱሪን ዝቅ አድርጎ መታጠቅ ነውር ነው፡፡ የተመረጡት ተጠኝ ማህበረሰቦች ሱሪውን ዝቅ አድርጎ የሚለብስን ወጣት ምን አይነት ሰው ነው? ለሚለው የራሳቸውን ግምት ያስቀምጣል፡፡ ማህበረሰቡ ስራ የማይወድና በውስጡ ቁም ነገር የሌለው ጉረኛ መሆኑን መለያ አድርጎ ይወስደዋል (ቃለ መጠይቅ፣ ሙሉየለት እንየው፣ 07/06/2013)፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ጠላት ቢመጣና አጋጣሚ ከሰው ጋር ቢጣላ እራሱን ለመከላከል ያስቸግረዋል፤ ሱሪን ዝቅ አድርጎ መልበስ የተገዥነት ተምሳሌት ነው ብለው ያስባሉ፡፡

ሱሪን ዝቅ አድርጎ መታጠቅ ጠላት ሳያስወልቅና ሳያሸንፍ እንደተሸነፍን እንሰብካለን የሚል መልክእት ያለው ነው፡፡ ስለዚህም ሱሪውን ዝቅ አድርጎ የሚለብስ ሰው በራሱ ጊዜ ተሸናፊ እንደሆነ  እና ፈሪ እንዶሆነ ወይም ጠላትን የመከላከል አቅም እንደሌለው የሚያስረዳ ነውር ነው፡፡

ሌላው ቅድመ ጋብቻ ላይ ያሉ ወጣቶችን ማንነት ለመለየት የሚያገለግለው የነውር አይነት ወንድ ልጆች ፀጉራቸውን አንጨፍርረው መሄድ ወይም ፀጉራቸው ከመጠን በላይ እስኪያድግ መቆየት ነው፡፡ በተመረጠው ተጠኝ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ሴት ተማሪዎች ፀጉራቸውን አሳድገው ይሰሩታል፡፡ ካላሳደጉ በአጭር ተስተካክለው ያጌጣሉ፡፡ ወንዶችም በአጭሩ ተስተካክለው በጣም ሳያድግ በሳሙና ፈርዘው ያጌጣሉ፡፡

ከዚህ ውጭ በሆነ መንገድ ፀጉርን መስተካከልና ማሳደግ እንደ ነውር የሚቆጠር ተግባር ነው፡፡ አንድ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ከዩኒቨርስቲ ቆይቶ ሲመጣ ፀጉሩን አንጨፍርሮ ቢመጣ ትምህርት ሲማር ቆይቶ የመጣ ሳይሆን በስርቆት ወይም በዝሙት ካለበለዚያም ደግሞ ሰውን በመደብደብ

የቆየ መሆኑን የሚለይበት ነው፡፡ ይህ በአሁኑ ስዓት እየተከበረ ያለ ነውር ነው፡፡ በመሆኑም ፀጉርን ማንጨፍረር ነውር የሆነበት ምክንያት ተደባዳቢ፣ ሌባና በትምህርቱ ሰነፍ ሰው እንደሆነ መለያ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

> በአንድ ወቅት እንደ ዘመን አመጣሽ ፀጉር ማንጨፍረር ተስፋፍቶ ነበር፡፡ ወላጅ መክሮት አልሰማ ያለውን ለፖሊስ አስይዘን እስከ ማስመከር ደርሰናል፡፡ ከትምህርት ቤትም ሳይስተካከሉ እንዳይገቡ ተደርጓል፡፡ አሁንም ወጣት ተማሪዎች ፀጉራቸውን አንጨፍርረው አይሄዱም፡፡ እንደዚህ አይነት ሰው ከቀበሌያችን ካለና ፀጉሩን አንጨፍርሮ የሚሄድ ከሆነ ወይም የተለየ ቁርጥ ሚቆረጥ ከሆነ ከብት ሲጠፋን እንጠረጥራለን፡፡ ከዚያም የእገሌ ልጅ ነው ብለን በምህላ እንይዘዋለን፡፡ ምክንያቱም ፀጉሩን የሚያጨፈርር እና የሚያሳድግ ሰው ሌባና ተደባዳቢ ነው ብለን እናስባለን (ቃለ መጠይ፣ ሙሉየለት እንየው፣ 07/06/2013/)፡፡

ይህ ነውር ትውልዱን በመልካም ስነ ምግባር ለማነፅ ይጠቅማል፡፡ ወንጀለኛን የመለየት አንድ መስፈርት ሆኖም አገልግሏል፡፡ በማህበረሰቡ ያለውን የፀጉር አጊያጊያጥ ባህል ተሸርሽሮ እንዳይጠፋና ባህል ቀጣይነት እንዲኖረው በማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡

### 5.1.3.2. የትዳር አጋር ማጣትን በመፍራት የሚከበሩ አለባበስ/ አጊያጊያጥ ነውሮች

በተጠኝው ማህበረሰብ በተለይም ሴቶች የአለባበስና አጊያጊያጣቸው ከባህሉ እንዳያፈነግጡ መጠንቀቅና ባህሉ የሚፈቅደውን አለባበስ መልበስ የሚደገፍ ተግባር ነው፡፡ አንድን ሴት ለትዳር ለመምረጥ ወንዱ አለባበሷን ያያል፡፡ አዛውንት ሴቶችም ልክ እንደዚሁ አለባበሳቸው እድሜያቸው የሚመጥን ካልሆነእንደ ነውረኛ ይቆጠራሉ፡፡

የማህበረሰቡን የሚከተለውን ባህል ተከትላ ከለበሰች ጭምትና ስነ ምግባር ያላት ተደርጋ ትታሰባለች፡፡ አለባበሷ ከባህሉ ያፈነገጠ ከሆነ ለዝሙት ተጋላጭና ዝሙትል ለመፈፀም የተዘጋጀጅ ተደርጋ ስለምትቆጠር የትዳር አጋር አስከማጣት ልትደርስ ትችላለች፡፡

ሌላው በተጠኝው ማህበረሰብ በቅድመ ጋብቻ ያሉ ሴቶችን ማንነት ለመለየት ከሚያገለግሉ ነውሮች ውስጥ በመጠናቸው ትላልቅ የጆሮ ጌጦችን ማድረግ ነው፡፡ ያላገቡ ሴቶች የተለያ ዲዛይን ያላቸውን የጆሮ ጌጦች ያደርጋሉ፡፡

ነገር ግን በመጠናቸው ትላልቅ የጀሮ ጌጦችን ማድረግ እንደ ነውር ይቆጠራል፡፡ ለዚህም የሚያቀርቡት ምክንያት ሰውን ይስባሉና ለዝሙት ያጋልጣሉ፤ እሷንም ለዝሙት የተዘጋጀች እንደሆነች ያስቆጥራል የሚል ነው፡፡

> በኛ አካባቢ ትልልቅ የጀሮ ጌጦችን ሲለብሱ አንድያውን አንወድም፡፡ ትልልቅ የጆሮ ጌጥ ሚለብሱ ትግሬዎች ናቸው እንጅ በኛ ባህል የለም፡፡ በኛ አካባቢ ለብሰው ካየነ አችስ ወንድ ምናምን ፈልጋ ያለች ናት ነው የምንል አንድያው እንደ ባለጌ እንቆጥራታለን (ቃለ መጠይቅ፣ በቃሉ ፈጠነ፣ 13/06/2013)፡፡

ይህ ነውር በአጊያጊያጥ ምክንያት የሚመጡ የተቃራኒ ፆታዎች ግንኙነት በመከላከል ለዝሙት የሚጋለጡ ሰዎችን ለመቀነስ አገልግሏል፡፡ ሁለተኛም የጆሮ ጌጥ አለባበስ ባህል ቀጣይነት እንዲኖረው በማድረግ ክፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡

በማህበረሰቡ ሴት ልጅ ሱሪ መልበስ ጡቶቿንና ጭኖቿን የሚያሳዩ ስስ ልብሶችን መልበስ የተከለከለ ነው፡፡ ለዚህም የሚያቀርቡት ምክንያት ወንዶችን ለተቃራኒ ፆታ ግንኙነት ይገፋፋሉ የሚል ሲሆን ሁተኛው በማህበረሰቡ አሳቤ ሱሪ የሚለብሱና ጭናቸውን ሊያሳዩ የሚችሉ አጭር ልብሶችን የሚለብሱ ሴቶች ድንግልና የላቸውም፤ ለዝሙት የተጋለጡ ናቸው፡፡ ስለዚህም የትዳር አጋራቸውን ቶሎ ይፈታሉ፤ አይለምዱም ተብሎ ይታሰባል፡፡

ድሉ ተፈራ የተባሉ አንድ መረጃ አቀባይን ቅድመ ጋብቻ ነውሮችን ማክበር ያለው ጠቀሜታ ምንድን ነው? ብየ የጠየቅኋቸውን ጥያቄ እንደሚከተለው ገልፀውልኛል፡፡

> ልጄ ነውርን ማክበር የፈጣሪን ህግ ማክበር ነው፡፡ ዛሬ ነውሩ እየጠፋ ነው ትውልዱ ቃናያጣ፡፡ ነውርን የሚያከብሩ ልጆችን እንመርቃቸዋለን፡፡ ሀብታቸው ይባረካል፤ እድሜያቸው ይረዝማል በማለት መልሰውልኛል፡፡

በመሆኑም ማህበረሰቡ ነውርን ከፈጣሪ የተሰጠ ትዕዛዝ አድርጎ እንደሚቆጥረውና ነውርን መጣስ ፈጣሪን ማስቀየም ባህልን መርሳት እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ በቅድመ ጋብቻ ያሉ ነውሮች ወጣቱን በስነ ምግባርለማነፅ፣ ባህልንና ትውፊትን በማስተማር ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ፣ በትጭጭት ላይ ያሉ ተጋቢ ቤተሰቦች በመካከላቸው አለመግባበቶች እንዳይፈጠሩ፣ ወጣቶች ከተለያየ ችግሮች እራሳቸውን እንዲከላከሉ

ለማድረግ የሚያገለግሉ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ የቅድመ ጋብቻ አፈፃፀም ስርዓት ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው።

በመረጃ ትንተናው ወቅት የተገኙ ቅድመ ጋብቻ ነውሮች ቅድመ ጋብቻ ላይ ባሉ ሴቶች ማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ችግሮች ከመድረሳቸው በፊት ቅድመ መከላከሎች በመሆን የሚያገለግሉ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ ቅድመ ጋብቻ ማንነት ገለጭ አለባበስና አጊያጊያጥ ነውሮች ማህበረሰቡ ወንጀል ለመስራት የተዘጋጀን ሰው ለመለየት፣ ወጣቶች ለተቃራኒ ፆታዎች ግንኙነት እንዳይሳቡ ለማድረግ የሚያገለግሉ ናቸው።

## 5.2. የዕለተ ጋብቻ ነውሮች ትንተና

ከጋብቻ በፊት ያሉ ተግባራት ተከናውነው ካለቁ በኋላ የጋብቻ ቀን ይቀጥላል። የቅድመ ጋብቻ ነውሮች ለዕለተ ጋብቻ መሳካት ከፍተኛ ሚና አላቸው። የዕለተ ጋብቻ ነውሮች ሙሽሪትና ሙሽራውን አጋቢዳኞችን (ቀጣሮችን)፣ሚዜዎችን እና አሳዳሪዎችን እንዲሁም የተጋቢዎችን ቤተሰብ የሚመለከቱ ናቸው። የዕለተ ጋብቻ ነውሮች ከጋብቻ በኋላ ላለው የሙሽሮች ህይወት መሳካት፣ ለትዳራቸው መፅናትና ሙሽሮች ሀብት እንዲረባላቸው ሲባል የሚከበሩ ናቸው። ሙሽሪትና ሙሽራው ለክፉ መንፈስ እንዳይጋለጡ ለማድረግ፣ በጋብቻ ቀኑ ሰላምናመረጋጋት እንዲኖርና ሙሽሪትና ሙሽራው ለሀፍረት እንዳይጋለጡ ለማድረግ ከፍተኛ ሚና አላቸው።

በዕለተ ጋብቻ ነውሮች ውስጥ ሙሽሮችን ለክፉ መንፈስና ለአደጋ እንዳይጋለጡ ሲባል የሚከበሩ ነውሮች የቀረቡበት ሲሆን በስር ሚዜ እና በአሳዳሪ፣ በቀጣሮችና በሙሽሮች የተለያዩ ጥንቃቄ ጉድለቶች ከተጣሱ ከፍተኛ ችግር የሚያስከትሉ ናቸው። በማህበረሰቡ ‹‹ሙሽራና አራስ አንድ ነው›› የሚል አስተሳሰብ አለ። ተጠኚው ማህበረሰብ ሙሽራውና ሙሽሪት በክፉ መንፈስ አማካኝነት ለተለያዩ ችግሮች እንዳይጋለጡ እንደ ወላድ መጠበቅ አለባቸው ብሎ ያምናል። በተጠኚው ማህበረሰብ ሙሽሮች በዕለተ ጋብቻ ወቅት ያሉ ነውሮችን በጥንቃቄ አክብረው ማለፍ ካልቻሉ በክፉ መንፈስ ምክንያት ከፍተኛ የሆነ ስነልቦናዊና ማህበራዊ የጤና ችግሮችን ያስከትላል ተብሎ ይታሰባል። በመሆኑም የዕለተ ጋብቻ ነውሮች በማህበረሰቡ በጥንቃቄ የሚተገበሩ ሲሆኑ ለዚህም የስር ሚዜና አሳዳሪ ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳሉ።

ሙሽሮች ለክፉ መንፈስ እንዳይጋለጡና ዕለተ ጋብቻው እንዳይረበሽ ሲባል የሚከበሩ ነውሮች እንዳይጣሱ ለማድረግ የስር ሚዜና አሳዳሪ ያላቸው ሚና ቀላል አይደለም፡፡ በዕለተ ጋብቻ ውስጥ ሊጠቃለሉ የሚችሉ ነውሮች በሶስት ዋና ዋና አቢይ ርዕሶች ተከፋፍለው ቀርበዋል፡፡

የመጀመሪያው ርዕስ ቀጣርን የተመለከቱ ነውሮች የቀረቡበት ሲሆን ሁለተኛው ሙሽሮች ማክበር የሚገባቸው ነውሮች እና ሶስተኛው አሳዳሪንና የስር ሚዜን በተመለከተ የሚፈሩ ነውሮች የቀረቡበት ነው፡፡

### 5.2.1. ዕለተ ጋብቻ ተፈፃሚ እንዲሆን በቀጣር (አጋቢ ዳኛ) የሚከበሩ ነውሮች

ቀጣር (አጋቢ ዳኛ) የሚል ስያሜ የተሰጣቸው ሰዎች በዕለተ ጋብቻ ከሙሽራው በፊት በመሄድ የጋብቻውን ቀን እና ሙሽሮች ያላቸውን ንብረት የሚያፀድቁ ናቸው፡፡

ቀጣር ወይም አጋቢ ዳኛ በመባል የሚጠሩ ሰዎች በዕለተ ጋብቻ ብቻ ሳይሆን በድህረ ጋብቻ ለተጋቢዎቹ መካሪና በችግር ደራሽ ናቸው፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ ዕለተ ጋብቻ ተፈፃሚ ይሆን ዘንድ ቀጣሮች ወይም አጋቢ ዳኞች ማክበር እንደሚገባቸው አምኖ የተቀበላቸው ነውሮች አሉ፡፡ በቀጣሮች የሚከበሩ ነውሮች ለዕለተ ጋብቻ መሳካት ከፍተኛ ድርሻ አላቸው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በዕለተ ጋብቻ ቀን ቀጣሮች አረቄና ዳቦ ቆሎ ሳይዙ መሄድ እና የያዙትን አረቄና ዳቦ ቆሎ ሳይቀምሱ ከሙሽሪት ቤተሰቦች ቤት መግባት የተከለከለ ነው፡፡

አረቄ በማህበረሰቡ ለመዝናኛ፣ ለሰርግ፣ ሰው ሲሞት ለማስተዛዘን እና ሰው ሲወልድ ተይዞ የሚሄድ የመጠጥ አይነት ነው፡፡ በተጠኘው ማህበረሰብ አንድ ሰው ለእንግድነት ቢሄድ ከጠላ በተጨማሪ የሚቀርብለት መጠጥ አረቄ ነው፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ ለአረቄ የሚሰጠው ቦታ ሰፊ ነው፡፡

ቀጣሮች (አጋቢ ዳኞች) አረቄ በጠርሙስ እና ዳቦቆሎ በሙዳይ አድርገው ከሙሽራው ቀድመው ይሄዳሉ፡፡ ቀጣሮች ከደረሱ በኋላ ወንድ ቤተሰብ እና የሴት ቤተሰቡ ያቀረቡትን ሀብት ወይም መሬት በጋብቻ ወረቀቱ ተፅፎ ተፈራርመው ይፀድቃል፡፡ ከዚህም በኋላ በስንቡል አጋሰስ (የቀጣርን ዳቦቆሎና አረቄ እንዲሁም የሙሽሪትን ልብሶች በሚይዝ ሰው) አማካኝነት ይዘውት የሄዱት አረቄ ተቀድቶ ይጠጣል፡፡

አረቂው በቀጣሮች ብቻ ተጠጥቶ የሚያልቅ ሲሆን ዳቦ ቆሎው ግን ለቀጣሮች ከደረሰ በኋላ ከሙሽሪት ቤተሰቦች ቤት ላሉት ሁሉ ይቀመሳል፡፡

አረቂው እንደ ዳቦ ቆሎው ሁሉ ቤት ላሉት ሰዎች የማይሰጥበት ምክንያት በማህበረሰቡ ተጠጥቶ በማለቅ ላይ ያለን አረቄ (ከጠርሙሱ የጎደለን አረቄ) ከሰው ፊት ማቅረብ ነውር ስለሆነ ነው፡፡

ከሰው ፊት የሚቀርብ አረቄ ጠርሙሱ እንደሞላ መሆን አለበት፡፡ ስለዚህ ቀጣሮች ሲጠጡ ስለሚያጎድሉት ከሙሽሪት ቤት ላሉት ሰዎች አይሰጥም፡፡

ቀጣሮች የያዙትን አረቄ ሳይቀምሱ ወደ ሙሽሪት ቤተሰቦች ቤት አይገቡም፡፡ ከሌሎች መጠጥ አይነቶች አረቄ የተመረጠበት ምክንያት ቆሌን የማስታረቅ ሃይል አለው ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ ለዚህም ተጠኚው ማህበረሰብ ዛር ያለባቸው ሰዎች ሲነሳባቸው ከቡና ቀጥሎ እንደማቋደሻ ይቀርብላቸዋል፡፡ በመሆኑምአጋቢ ዳኞች (ቀጣሮች) ወደ ሙሽሪት ቤት ጋብቻውን ለማፅደቅ ሲሄዱ ከመንገድ ጋብቻውን ለማፍረስ ተከትሎ የሄደ ሰይጣን ባረቂው መቅረብ ምክንያት ተቋድሶ ይመለሳል የሚል እምነት አላቸው፡፡ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ዕለተ ጋብቻ ተፈፃሚ እንዲሆን በቀጣሮች በኩል የሚከበሩ ነውሮች መከበራቸው በክፉ መንፈስ ምክንያት ይመጣሉ ተብለው የሚታሰቡ አለመግባባቶች እንዳይፈጠሩበማደረግ ዕለተ ጋብቻ ተፈፃሚ እንዲሆን የማድረግ ፋይዳ አለው፡፡

ለእንግድነትና ለጥናትና ምርምር የሄደ ሰው ባይወድም አልቀምስም ማለት አይችልም፡፡ ምክንያቱም በዚህ አውድ አረቄ የደስታ መግለጫ በመሆንና የሀሳብ ልዩነትን አጥብቦ ያጣላል የሚባለውን ክፉ መንፈስ ደልሎ በመስደድ ጋብቻውን ለማሳካት ከፍተኛ ሚና እንዳለው ስለሚታሰብ ነው፡፡ ይህንን ነውር በእጅጉ ታየ ቤት በቀን 14/06/2013 በምልከታ ማረጋጋጥ ችያለሁ፡፡

አጋቢ ዳኞች በድህረ ጋብቻም ባልና ሚስቱ ሲጣሉ እስከ ሶስት ቀን በባልና ሚስቱ ጉዳይ ተቀምጠው በችግራቸው ዙሪያ ሳይመክሩ ማፋታት በማህበረሰቡ የተከለከለ ነው፡፡ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው አጋቢ ዳኞች ከመጀመሪያ ባልና ሚስቱ ሲጋቡ የነበሩና የጋብቻ ውሉን ያፀደቁ በመሆናቸው ባልና ሚስቱ ቢጣሉና አለመግባባቶች ቢፈጠሩ ሚስት ወይም ባል መጀመሪያ የሚናገሩት ለእነዚህ ሰዎች ነው፡፡

አጋቢ ዳኞቹም ቀነቀጠሮ ይዘው ባልና ሚስቱ የተጣሉበትን ምክንያት ይጠይቃሉ፡፡ ባልና ሚስትም ጠባቸውን ተራ በተራ ከተናገሩ በኋላ እንዲስማሙ ይመክራሉ፡፡ ባልና ሚስቱ በአንድ ቀን እምቢ ቢሉም ድጋሜ ቀነ ቀጠሮ ይዘው ይለያያሉ፡፡

በሁለተኛው ቀንም አልስማማ ቢሉ ማፋታት ወይም አይስማሙም ብለው መተው የለባቸውም፡፡ እንደ ፍርድቤት ቀጠሮ በተደጋጋሚ ነገሩን ተቀምጠውና ተረጋግተው ያዩታል፡፡ በአንድ ቀን እና በሁለት ቀን የሚያፋቱ አጋቢ ዳኞች በማህበረሰቡ ነውረኞች ናቸው፡፡ ምክንያቱም አድረው ሲውሉ ስህተታቸውን ሊተራረሙና ይቅር ሊባባሉ ስለሚችሉ ለባልና ሚስቱ የቁጣቸው ማብረጃ ሰፊ ምክር መሰጠት አለበት ተብሎ ስለሚታሰብ ነው (ቃለ መጠይቅ፣ድሉ ተፈራ፣ 06/06/2013)፡፡

ይህ ነውር ባልና ሚስቱ በስሜት እንዳይወስኑ እና አብሮነታቸው እንዲዘልቅ ትዳራቸው እንዲፀና የሚያደርግ ነው፡፡ የባልና ሚስት ግጭትን በማብረድ ጋብቻን የመትከልና የማጠናከር ተግባር እንዲሁም ትዕግስትንና ይቅር ባይነትን ለማስተማር ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ አለው፡፡



**ፎቶ አንድ፡-** በእጅጉ ታየ ጓሮ በቀን 14/06/2013 ወጣት ስመኝ እጅጉን እና ወጣት ታረቀኝ አለምነህን ለማጋባት የተቀመጡት አምስቱ አጋቢ ዳኞች አረቄ እየጠጡ የጋብቻ ስርዓቱን ሲያፀድቁ የሚያሳይ ፎቶ

በፎቶ አንድ እንደምንመለከተው አጋቢ ዳኞች ወይም ቀጣሮች የጋብቻ ውሉን የሚያፀድቁት ከጓሮ ሆነው ነው፡፡ ከጓሮ የሆነው በሁለት ምክንያቶች ነው፡፡ አንደኛ በማህበረሰቡ በጋብቻ ውል እና ቀጠሮ ቀን ስምምነት ሳይፈጠር ወይም የጋብቻ ስርዓት ሳይፀድቅ (ወረቀቱ ሳይፃፍ) ቤት አይገቡም፡፡

ምክንያቱም ቤት ከገቡ የሚበላ ወይም የሚጠጣ ነገር ምግብ ሳይዙ አይቀመጡም፡፡ የተከበረን እንግዳ አስቀምጦ  ምግብ ሳያቀርቡ ዝም አይባልም፡፡ ስለዚህም በማህበረሰቡ ከምግብ መሀል ነገር ማንሳት እንደነውር ይቆጠራል፡፡ በተጋቢ ቤተሰቦች መካከል አለመግባባ ቢፈጠር ልጅህን እንጅ እንጀራህን ፈልገን አልመጣንም፡፡ ልጅህን ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆንህ ገብተን አንበላም፤ አንጠጣም የሚል መልስ ይሰጣሉ፡፡

ሁለተኛ በልተውና ጠጥተው ከአጠገቡ የስካርመንፈስ ቢሰማቸው ነገር እንዳያበላሹ ፍርድ እንዳያጓድሉ ተብሎ ስለሚታሰብ ምግብ ከመብላታቸውና ከመጠጣታቸው በፊት የዕለተ ጋብቻ ስርዓቱን ከጓሮ ሆነው ያፀድቃሉ (ቃለ መጠይቅ፣ ድሉ ተፈራ፣06/06/2013)፡፡



**ፎቶ ሁለት፡-** በቀን17/05/2013/የሙሽሮችን ጋብቻ ለማፅደቅ አጋቢ ዳኞች አረቂና በሙዳይ ዳቦ ቆሎ ይዘው ወደ ሙሽራት ቤት ሲሄዱ አጥኝዋ ምልከታ ስታደርግ የሚያሳይ ፎቶ

ከዚህ ላይ ሳይገለፅ መታለፍ የሌለበት በሙዳይ ዳቦ ቆሎ ሳይያዝ ቢሄድ ነውር የሆነበት ምክንያት ምንድነው? የሚለውጥያቄ ነው፡፡ በተጠኘው ማህበረሰብ የራሱ አስተምህሮና ለዳቦ ቆሎው እና ለመያዣ ሙዳይ የሚሠጠው ተምሳሌታዊ ትርጓሜ አለ፡፡

ዳቦ ቆሎ በሙዳይ የሚያዘው ሙሽራት ገና ማደጎ (ከሌላ ወንድ ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፅማ የማታውቅ ሴትና አግብታ የማታውቅ ሴት) ከሆነች  ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ አግብቶ ቆይቶ ትዳር ይዞ የኖረ እንደገና ሲያገባ ዳቦ ቆሎ በሙዳይ አለመውሰድ ነውር አይደለም፡፡ በመሆኑም በሙዳይ ዳቦ ቆሎ መያዣ የሙሽሪትን ንፅህናና ቅድስና ለመግለፅ ሲባል ነው፡፡

ሙዳይ የተያዘበት ምክንያት የራሱ ምሳሌ ስላለው ነው፡፡ ድንግል ማሪያምን ሙዳየ መና ይላታል፡፡ በሀቱም ድንግልና ኢየሱስ ክርስቶስን የወለደች መሆኗን ሲገልፅ ነው፡፡ ከሙዳዩ ውስጥ ያለው ዳቦ ቆሎ ፈውስና ድህነት የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ስጋውን ቆርሶ ደሙን አፍሶ ያዳነን መሆኑን ለመግለጽ ነው፡፡ በመሆኑም ሙሽራይቱ በሙዳይ ስትመሰል የሙሽራይቱን ማደጎነትና ንፅህናን ለመግለፅ ነው፡፡ ከማደጎ ሰርግ ሙዳይና ዳቦ ቆሎ ሳይያዝ አይሄድም (ቃለ መጠይቅ፣ ቄስ ገበየሁ ታገለ፣12/06/2013)፡፡

በአጠቃላይ ቀጣሮች ከሙሽሪት ቤተሰቦች ቤት አረቄና በሙዳይ ዳቦ ቆሎ ሳይዙ መሄድ የተከለከለ መሆኑ በማህበረሰቡ እሳቤ በክፉ መንፈስ ምክንያት የሚመጣን አለመግባባት በአረቄው ድል ለመንሳት ተጠቅመውበታል፡፡ ሌላው የሙሽሪትን ቤተሰቦች ለማስደሰት ነውሩ ጠቀሜታ የጎላ ነው፡፡ምክንያቱም ሙዳዩን ይዘው ሲሄዱ የልጃቸውን ንፅህና በወንድ ቤተሰቦች መታመንን የሚያሳይ በመሆኑ የጋብቻው ፍፃሜ በደስታ እንዲቀበሉ ያደርጋቸዋል፡፡፡

## 5.2.2. ሙሽሮች የሚያከብራቸው ነውሮች

በተመረጠውተጠኝማህበረሰብ ሙሽሮች ማክበር የሚገባቸው ነውሮች አሉ፡፡ ሙሽሮች ከጋብቻ ቀናቸው አስከ መልስ ድረስ ከአመጋገባቸውና ከእንቅስቃሴያቸው ጋር ተያይዞ ያላቸው ሁኔታ የተመጠነ መሆን አለበት፡፡ በማህበረሰቡ ‹‹ሙሽራና አራስ አንድ ነው›› የሚል አስተሳሰብ አለ፡፡ አራስ በተለይም አስር ቀን አስኪሞላት ምንም አይነት ስራና እንቅስቃሴ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡ ሙሽሮች ማክበር ከሚገባቸው ነውሮች ውስጥ ከዕለተ ጋብቻ አስከ መልስ ባሉት ቀናት የተለያዩ ስራዎችን መስራት ወደ ካልተገቡ እንቅስቃሴዎች መቆጠብ፣ የደም መራመድ ስርዓትን ተግባራዊ ማድረግ፣ የአመጋገብ ስርዓታቸውን የተመጠነ ማድረግ፣ የቤት መዞር ክዋኔን ተግባራ ማድረግ፣ ሙሽሪት እንድትለምድ የሚያደርጉ ነውሮችን ማክበር፣ሙሽሮችን ሀብታምና ያደርጋሉ ተብለው የሚታሰቡ ነውሮችን ማክበር ተጠቃሽ ናቸው፡፡

### 5.2.2.1. የተለያዩ ስራዎችን ከመስራትና ካልተገቡ እንቅስቃሴዎች መቆጠብ

በተጠኘው ማህበረሰብ የሙሽራ አጫዋጮች(ሙሽሪት የሚያጫውቱ ሴቶች) አጅበዋት ወይም የስር ሚዜው ባልና ሚስቱን እየጠበቃቸው ሽንት ቤት መጠቀምና መዝናናት ከፈለጉ ይዘዋቸው መውጣት ይቻላል፡፡ የዕለተ ጋብቻ ቀን የሙሽሪትን ሴትነት ለመፈተን የሚታዘዙ ስራዎችም የሉም፡፡

ሙሽሪት ባለ ሙያ ሴት መሆን አለመሆኗ የሚረጋገጠው ከመልስ በኋላ ነው፡፡ ሙሽሮች መልስ እንደጨረሱ ሙሽሪት ከባሏ ቤተሰቦች ጋር በምትቆይባቸው ቀናት ቡና እንድታፈላ ትታዘዛለች፡፡ የመክፈልት ማሳለፊያ የሚሆን ወራንታ(ቤተክርስትያን እንጀራ ለመውሰድ የሚያገለግል ከጥለት ወይም ከግራምጣ የተሰፋ እቃ) ወይም የዘር መዝሪያ የሚሆን ቁና (ዘር የሚዘሩ ወንዶች ዘሩን ለመያዝ የሚጠቅም ከወራንታ የሚያንስ ዕቃ) ስፊ ትባላለች፡፡እነዚህ ተግባራት በዕለተ ጋብቻ ቀን ተግባራዊ አይሆኑም፡፡ ሙሽሪት ስራ እንድትሰራ የምታዝዝ የሙሽራው እናት ካላች እንደ ነውረኛ ትቆጠራለች (ቃለ መጠይቅ፣ አገውላንች መንግስቴ፣ 07/06/2013)፡፡

ሙሽሪት ውሃ እንድትቀዳ ወንዝ ማስወረድ ወይም በአሷ ፈቃድ መውረድ፣ ጓዳ ውስጥ መግባትና ቡና ማስፈላት ወይም በራሷፈቃድ ማፍላት ፈፅሞ የተከለከለ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ጠላ የሚደረግበት ቦታ ጓዳ ውስጥ ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ከአስር ቀን በፊት ሙሽሪት ብትገባ ሰይጣን ይይዛታል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ምክንያቱም ሰይጣን ከሚወዳቸው ምግቦች ውስጥ ድፍድፉን ወይም የደፍድፍ አተላን እና የቡና አተላን ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ በመሆኑም ጓዳ ውስጥ ሙሽሪት ብትገባ አዲስ በመሆኗ አተላውን ለመጠቀም የመጣ ክፉ መንፈስ ከእሷ ላይ ያርፋል፤ የቡናውን እጥብጣቢ ስትደፋ ይይዛታል የሚል እምነት አላቸው፡፡ ጓዳ ውስጥ መግባትና ገብቶ ስራ መስራት፣ ወንዝ መውረድ እንዲሁም የቡናን አተላ ለመድፋትና የተደፋበትን ቦታ ለማፅዳት እንቅስቃሴ ማድረግና መስራት ለሙሽራ ያልተገቡ ስራዎችና የስራ ቦታዎች ናቸው፡፡ የስር ሚዜ ዋና ተግባሩም በዚህ ቀንም ሆነ እሰከ አስር ቀን ባሉት ቀናቶች ሙሽሮች ብቻቸውን እንዳይሆኑ መጠበቅ ነው፡፡ ብቻቸውን ቢሆኑ ሰይጣን አእምሯቸውን በማወክ እብደትን ወይም የአካል ጉዳትን እና ሌሎችን በሽታዎች ጭምር ያስከትላል ተብሎ ይታሰባል(ቃለ መጠይቅ፣ አገው ላንች መንግስቴ፣ 07/06/2013)፡፡

ይህ ነውር የሙሽርነት ቀን እንቅስቃሴ የተመጠነ እንዲሆን በማድረግ ሙሽሪትን የአካልና የአእምሮ ደህንነቷን በመጠበቅ ለቤተሰቦቿ በሰላም ለማስረከብ እንዲሁም ከጋብቻቸው በኋላ ከሚመጣው የጤና ችግር ለመታደግና ለመቆጣጠር ይጠቅማል፡፡ በማህበረሰቡ እምነት ክፉ መንፈስ የያዘው ሰው ወዲያውኑ ላይነሳበት ይችላል፡፡ ነገር ግን ከተወሰኑ ቀናት በኋላ ባደረበት ሰው ላይ ይነሳል፡፡ በመሆኑም ይህ ነውር መጣስ ከጋብቻ በኋላ ላለው ደህንነትም ጠንቅ ሊሆን የሚችል በመሆኑ ማህበረሰቡ አብዝቶ ይጠነቀቃል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሙሽሪትን እናት በተመለከተ ሙሽራው ሲጠራ ከሳሎን ቤት ውሃ መድፋትና የወዳደቁ እቃዎችን ካሉ

አለማንሳት እንደ ነውር ይቆጠራል፡፡ ምክንያቱም ሙሽራው የፈሰሰው ውሃ አድጦት እንዳይወድቅ ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ ስለዚህም የሙሽሪት እናት ሙሽራው ሲገባ መሰናክል የሚሆኑ ነገሮችን እንዳይከሰቱ ቀድማ ቤቱን ማፅዳት አለባት፡፡

### 5.2.2.2. የደም መራመድ ስርዓትን ተግባረዊ ማድረግ

በተጠኘው ማህበረሰብ በዕለተ ጋብቻ ቀን የሚተገበረውን የደም መራመድ ስርዓት ተግባራዊ ማድግ ሙሽሮችን ከተለያዩ ችግሮች ይከላከላል የሚል እምነት አላቸው፡፡

ሙሽራ ሲገባ በግ፣ ፍየል ወይም ዶሮ ታርዶ ሙሽራው በጉን ወይም ዶሮውን አንገቱን ከቆረጠ በኂላ ከሙሽሪት ጋር ተያይዘው ደሙን ተራምደው ወደ ተዘጋጀላቸው ቦታ ይሄዳሉ፡፡ የደም መራመድ ስርዓትን በቀን 20/06/2013 በተደረገ የሰርግ ስነ ስርዓት በመላክ አደላ ቤት በመገኘት ተመልክቻለሁ፡፡

ሙሽሮች በግ (ፍየል ወይም ዶሮ) ሳይታረድና ደሙን ሳይራመዱመግባት የተከለከለ ለመሆኑ የሚያቀርቡት ምክንያት ሙሽራው ከቤተሰቦቿ ሙሽሪትን ይዞ ከቤተሰቦቹ ቤት እስኪደርስ ባሉት መንገዶች ውስጥ ሰይጣን ተከትሏቸው ይመጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ስለዚህም ተከትሎ የመጣው ክፉ መንፈስ ደሙን ልሶ እንዲመለስ ሙሽሮች የታረደውን፣ ፍየል ወይም ዶሮ ታርዶ የደም መራመድ ስርዓት ይፈፅማሉ፡፡ ሳይታረድላቸው ቢቀር ክፉ መንፈስ በሙሽሮቹ ላይ በመስፈር ጤና ያሳጣቸዋል፤ አእምሯቸውን በማወክ ሊያሳብዳቸው ይችላል ተብሎ ይታሰባል (ቃለ መጠይቅ፣ በቃሉ ፈጠነ፣ 13/06/2013)፡፡

በማህበረሰቡ የበግ ደም የመራመድ ባህል በሙሽራ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ በዓላት በሚታረድበት ሰዓት የሚስተዋል ተግባር ነው፡፡ የታረደውን ስጋ ሳይቀምሱ ለተለያዩ ስራዎች ወጥቶ መሄድ የተከለከለ ነው፡፡ ለክፉ መንፈስ ያጋልጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በጎች በአጠገብ ካሉም በጎች ጭምር የታረደውን በግ አንገቱን እንደተቆረጠ ተራምደው እንዲሄዱ ይደረጋል፡፡ ይህ ባይደረግ ደግሞ ከደሙ ላይ አረቂ ይጨመራል፡፡ ይህ የሚሆነው በጎች እንዲረቡ በሚል አሳቤ ነው (ቃለ መጠይቅ፣ ሙሉ አድማስ፣ 20/06/2013)፡፡

ይህንን የበግ ደም የማራመድና  አረቄ ከደሙ ላይ የመጨመር ስርዓት ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል አያከብረውም። ከሃይማኖት አስተምህሮ ውጭ እንደሆነ የሚያምኑ ሰዎች አሉ። ማህበረሰቡ ለተለያየ አላማ እንደሚጠቀምበት ከመረጃ አቀባዮች ሀሳብ መረዳት ይቻላል። የሙሽሮች ደህንነት እንዲጠበቅ ለማድረግ፣ ይደርሳል ብለው ከሚያስቡት የክፉ መንፈስ በሽታ ለማምለጥና ለመከላከል ነውሩ ጠቀሜታው የጎላ ነው።

### 5.2.2.3. የአመጋገብ ስርዓታቸውን የተመጠነ ማድረግ

ሙሽሮች በጋብቻ ቀናቸው አመጋገባቸው የተመጠነ መሆን አለበት። በተለይም ሙሽሪት የምትመገባቸው የምግብ አይነቶች የተመረጡ መሆን አለባቸው።

ለምግብነት ከሚመረጡት የምግብ አይነቶች ውስጥ ገንፎ እና በቅቤ የተመታ አዋዜ (የቅቤ ኩርፍ ይሉታል) ተመራጭ ናቸው። የቅቤ ኩርፉ ሆዷን የምትበላው ምግብ ሆዷን እንዳይረብሻት ታስቦ ሲሆን ገንፎ ቶሎ የመፈጨት ባህሪ አለው የሚል እምነት አላቸው። በመሆኑም ሙሽራ ያገኘውን ሁሉ መብላት የለባትም። ሽንታቸው ቶሎ ቶሎ ስለሚመጣቸው ለመነሳት ያፍራሉ። በምግብ ማብዛት ምክንያት ለሚመጣ የጤና መታወክ ችግር ይጋለጣሉ። ከዚህም በተጨማሪ ለወንዱ ሙሽራም ለመልስ ከአማት ቤት ሂዶ በመጠን መብላትና መጠጣት ይመከራል። ሙሽራውን በተመለከተ ሙሽሪት ለመልስ ተጠርቶ ቀን ላይ ሽንት ቤት እንደፈለገ የመጠቀም መብት ቢኖረውም ማታ ላይ ግን የተለያዩ ችግሮች ይደርስበታል ተብሎ ይታሰባል።

> ሙሽራው ለመልስ ተጠርቶ ከሙሽሪት ቤተሰቦች ቤት ሲሄድ ብዙ መጠጣትና መብላት በምሽታ ሰዓት ለመውት ይቸገራል። ለሙሽሪት ቤት ገና አዲስ ነው የቤቱን አከፋፈትና አዘጋግ አይችልበትም። ክፈቱልኝ ብሎ ሰውን መቀስቀስ ያሳቅቀዋል፤ይገመግሙታል። ውሻ ካለም ስላልለመዱት ይበሉታል። የመኝታ ቦታው ከከብቶች ቤት ከሆነ የከብቶችን ጸባይ አያውቅም ከብቶች ይወጉታል። ቤቱን እስኪለምደው መብሉንና መጠጡን በልክ ማድረግ አለበት። አንድያውን መጠጥ ማብዛት የለበትም እኔ ላውራ ነው ሚል እነሱም ምን አይነት ክልፍልፍ ነው ብለው ይንቁታል (ቃለ መጠይቅ፣ ይመኑ መኮነን፣ 15/07/2013)።

ሙሽሪትም እንደ ሙሽራው የቀረበላትን ሁሉ የምትበላ ከሆነ ችግር ያጋጥማታል፤ ከበቅሎ ወይም ከመኪና አውርዱኝ ትላለች ተብሎ ይታሰባል።

ሴት ልጅ እንኳንስ ሙሽራ ሆና በመንገድ እየተጓዘች ወይም ሰው እያያት  ሽንት ቤት መጠቀም እንደ ነውር ይቆጠራል፡፡ ተጠኝው ማህበረሰብ የሙሽራ አመጋገብን ስርዓት ለማስተማር ተረኮችን ይጠቀማል፡፡

> ከዕለታት አንድ ቀን ሙሽራው ያገኘውን ሁሉ ከመጠን በላይ በልቶ በልቶ ሆዱ ቁንጣን ይይዘዋል፡፡ ከዚያም ሽንት ቤት ለመውጣት ብሎ ሲነሳ ከቤት ያለው ውሻ ያስደነግጠዋል፡፡ እሱም በድንጋጭ ፈሱን ይፈሳል፡፡ አማቱም ውሻውን እየደበደበች ስታባርር ጎረቤት ምን አድርጎሽ ነው ብሎ ይጠይቃታል፡፡ ኸረ አፈር ይብላ የልጄን ባልአስፈሳብኝ ትለዋለች፡፡ እሱም ኸረ እማማ ከውሻውስ የእርስዎ ባሰ ይተውት አያባሩት ብሎ አላቸው ይባላል፡፡ ስለዚህ ሙሽራ የቀረበለትን ሁሉ መብላት የለበትም አመጋገቡ በመጠንና በልክ መሆን አለበት (ቃለ መጠይቅ፣ ተረፈ ስዩም፣ 30/05/2013)፡፡

ከዚህ ተረክ ላይ ሙሽራው ከመጠን በላይ በመመገቡ በአማቱና በሌሎች ፊት የማፈር ወይም የመሳቀቅ ችግር ብቻ ሳይሆን የሴት አማትን ነውርንም መረዳት ይቻላል፡፡ በተመረጠው ተጠኝ ማህበረሰብ የሴት እናት የልጇን ባል ችግር ብታይበት እንኳ ለሌሎች ተናግራ ሀፍረቱንና ድንጋጤውን ከማባባስ ይልቅ በሚስጥር እንድትይዝለት ይመከራል፡፡ ሙሽራውን የልጅ ባሏን ለሀፍረት የሚያጋልጡ ነገሮች እንዳይከሰቱ ቀድማ እንድትጠነቀቅም ይመከራል፡፡

### 5.2.2.4. ሙሽሪት እንድትለምድ የሚያደርጉ ነውሮችን ማክበር

የወንድም ሆነ የሴት ቤተሰቦች ልጆቻቸው ከተጋቡ በኋላ ሀብት ኑሯቸው ልጅ ወልደው እንዲኖሩ ይፈልጋል፡፡ ይህንንለማድረግ በዕለተ ጋብቻ የሚከውኗቸው የተለያዩ ክዋኔዎች አሉ፡፡ ክዋኔዎችን ሳይፈፅሙ መተው ከትዳር በኋላ ሙሽሮች ድሃ ይሆናሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሰዎች እንደተጋቡ እና ልጅ ከወለዱ በኋላ እንዳይፋቱ ለማድረግ ይጥራሉ፡፡ተጋቢዎቹ በጋብቻቸው ጸንተው እንዲኖሩም ለማድረግ የተለያዩ ክዋኔዎችን ይፈፅማሉ፡፡ በተለይም ሙሽሪት እንድትለምድ ሲባል የሚፈፀሙ ክዋኔዎችን ማለፍሙሽሮች ከጋብቻ በኋላ ለመፋታታቸው መንስኤ ይሆናሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡

በዚህ ስር ከሚጠቃለሉ ነውሮች ውስጥ የቤት መዞር ክዋኔን ተግባራዊ ማድረግ ተጠቃሽ ነው፡፡ሙሽራው ሙሽሪትን ለማምጣት ሲሄድ መጀመሪያውኑ የቤተሰቦቹን ቤት (የወንድ ቤተሰብን ቤት) ሶስት ጊዜ ዙሮ ወደ ሙሽሪት ቤት ይሄዳል፡፡

ሶስት ጊዜ መዞሩ አስፈላጊ አይደለም ብለው ካሰቡ አንድ ጊዜ ብቻ ቢዞርም ነውር የለውም፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ ወንድ ሙሽራ ሙሽሪትን ወደ ቤተሰቦቹ ቤት ይዟት ሲገባ ጡሩምባ እየተነፋ ሃይ ሎጋ እየተባለ ሙሽሪትና ሙሽራው በታዳሚዎች ታጅበው የወንድ ቤተሰብን ቤት ዙረው ይገባሉ፡፡ ይህንን ክዋኔ በቤተልሄም አስራት እና በአማረ ዘላለም የጋብቻ ስርዓት በዘላለም ሞቴ ቤት በቀን 17/06/2013/ እና በሽጋው መላክ እና በምወዳት ገነት የጋብቻ ቀን በመላክ አደላ ቤት በቀን 20/06/2013 ተመልክቻለሁ፡፡ ይህ የሚደረገው በማህበረሰቡ እምነት ሙሽራ ዙራ ካልገባች አትለምድም ቶሎ ትፋታለች በሚል አሳቤ ነው፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ህግና ስርዓትን እንዲሁም ሃይማኖት ሲያስተምር በተለያየ ቦታዎች እየዞረ ነው፡፡ ሐዋርያትም አብረውት ይዞሩ ነበር፡፡ ስለዚህም ሙሽራው ሙሽሪትን ይዞ በታዳሚዎች ታጅቦ መዞሩ የዚህ ተምሳሌት ነው፡፡ ህግና ስርዓትን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳስተማረ የአሁኑ ትውልድም የጋብቻ ህግና ስርዓትን ለማስተማር የተጋቢዎቹ ትዳር ዘላቂ እንዲሆን ሙሽሪትና ሙሽራው ሶስት ጊዜ ወይም አንድ ጊዜ ብቻ ዙረው ይገባሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሐዋርያት ጋር በመሆን በተለያየ ቦታዎች እንደዞረና ህግናስርዓትን ለእነሱም እንዳስተማራቸው ሁሉ ሙሽሪትና ሙሽራውም በታዳሚዎች ታጅበው ህግና ስርዓቱን ለሌሎች በማሳየት ተምሳሌት ይሆናሉ(ቃለ መጠይቅ፣ ቄስገበየሁ ታገለ፣ 12/06/2013)፡፡

አሁን አሁን ሶስት ጊዜ መዞሩ ቀርቶ በአንድ ጊዜ ብቻ ዙረው የሚገቡ ሙሽሮች ቢኖሩም ሶስት ጊዜ መዞር እንዳለባቸውና የራሱ ትርጉም እንዳለው መረጃ አቀባዮች ይገልፃሉ፡፡ በህልሙ የሚያስለፈልፈውን ሰው በእጅ ሳይነኩ በትንሽ ዱላ ሶስት ጊዜ መታመታ ካደረጉት የሚያስለፈልፋቸው ክፉ መንፈስ ይሸሻል፡፡ በትሩን ትተው አንድ ጊዜ ብቻ በእጃቸው ከመቱት እነሱን አዙሮ ያስለፈልፋቸዋል ብለው ያስባሉ፡፡ በሌላ በኩል ታቦታት ከወጡ በኋላ ወደ መንበረ ክብራቸው ሲገቡ ሶስት ጊዜ ዙረው ነው፡፡ ሰኔ እና በሐምሌ ወር መስቀል ወጥቶ ሶስት ጊዜ ዞሮ ይገባል፡፡ ይህም በበረድ የሚመሰል ስይጣን አዝመራቸውን እንዳያጠፋባቸው፣ ከቦታው እንዲሸሽ እና በሰላም እንዲከርሙ በማሰብ ነው (ቃለ መጠይቅ፣ በቃሉ ፈጠነ፣13/06/2013)፡፡

ይህ ነውር ሙሽሪት ሰፈሩን፣ የባሏን የቤተሰብ አባላት እንዲሁም ከትዳር አጋሯ ጋር ጋብቻቸውን ዘላቂነት እንዲኖረው በማድረግ የማጠናከርና የመትከል ተግባር አለው፡፡ የባልና ሚስት መፋታት ተረጋግቶ፣ አለመቀመጥ ክፉ መንፈስ የሚያሴረው ሴራ አንዱ ምክንያት እንደሆነ ይታሰባል፡፡

የትዳር መፍረስ የልጆችን መበተን፣ የሀብት መመናመን፣ እንዲሁም ለቤተሰብ ጥገኛ መሆንን ያስከትላል፡፡ በመሆኑም ይህ ነውር ሁሉ ችግር ጭንቀትና አለመረጋጋት እንዳይከሰት ለማድረግ ይጠቅማል፡፡ ሙሽራው ሙሽሪትን የቤተሰቦቹን ቤት ሶስት ጊዜ አዙሮ ማስገባቱ አብሮነትን የሚያጠናክርና ዘላቂ የሆነ የትዳር ህይወትን የመመስረት ባህልን አጠናክሮ ሊያስቀጥል የሚችል የነውር አይነት ነው፡፡

ሌላው ከቤት መዞር ክዋኔ ጋር ተያይዞ ሊታይ የሚችለው ሙሽራይቱ ከሙሽራውና ከሚዜዎች ጋር ስጦታ (ሽልማት) ለመቀበል አብራ መዞር የተከለከለ ነው፡፡ በጥናቱ የተመረጡት ማህበረሰቦች ለሙሽሮች ስጦታ(ሽልማት) በሁለት መልኩ ያበረክታሉ፡፡ የመጀመሪያው ሙሽራው ሙሽሪትን ይዞ ከቤተሰቦቿ ቤት ከመውጣቱ በፊት ሙሽሮች ቁመው ከተመረቁ በኋላ ሙሽራውና ሙሽሪት አብረው ጭፈራ ሲገቡ ብር ወይም አልባሳት ይበረከትላቸዋል፡፡ ሁለተኛው ሙሽራውና ሚዜዎች በጎረቤት እየዞሩ ሲጨፍሩ ለሙሽራውና ለሚዜዎቹ ቤት ያፈራውን ምግብና መጠጥ (ስጋ፣ እርጎ፣ ብር፣ ዶሮ ) እና ሌሎቹንም ይሸልሟቿዋል፡፡

ለሚዜውና ለሙሽራው የተበረከተው ምግብና መጠጥ ከሆነ ከሙሽራው ቤተሰቦች ቤት ወስደው ይበሉታል፡፡ ብር ወይም አልባሳት ከሆነ ለሙሽራውና ለሙሽሪት ብቻ ይበረከታል፡፡ በዚህ ስዓት ሙሽሪት ዙረው እስኪመጡ ድረስ ከቤት መቆየት አለባት፡፡

> ሙሽራ ሚዜና ከሙሽራው ጋር ስጦታ ለመቀበል አብራ አትዞርም ነውር ነው፡፡ ለአካባቢው ማህበረሰብ አዲስ ስለሆነች የሰው አይን ያርፍባታል፤ ቡዳ ይበላታል፡፡ የአካባቢው ሴቶችም ስትዞር ጋሬጣ ቢወጋት ውሻ ቢበላት አሁን መጥታ አሁን ምን አዞራት ሴት አትመስልም ይሏታል፡፡ ከሙሽራውና ከሚዜዎች ጋር አብራ የዞረች ሙሽራ ባልና ሚስቱ ከተጋቡ በኋላ ዟሪ ትሆናለች፡፡ በዚህም ከባሏ ጋር ባለመስማማት አስከ መፋታት ይደርሳሉ (ቃለ መጠይቅ፣ ድሉ ተፈራ፣ 06/06/2013)፡፡

ይህ ነውር ሚስት ከጋብቻ በኋላ ከማህበረሰቡ ጋር ያላት እንቅስቃሴ የተመጠነ እንዲሆን በማድረግ ሂሪ ሆና ስራ እንዳትፈታ የሚለውን ስጋት ለመቀነስ አገልግሏል፡፡ የሙሽራይቱን ደህንነት ለመጠበቅም ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከላይ የቀረበውን ‹‹ሴት አትመስልም አሁን መጥታ አሁን ምን ያዞራታል›› የሚለውን አገላለፅ ስንመለከት የአካባቢው ማህበረሰብም የመጣችውን ሙሽራ ስነ ምግባር መለያ አድርጎ እንደተጠቀመበት መረዳት ይቻላል፡፡

### 5.2.2..5. ሙሽሮችን ሀብታም ያደርጋሉ ተብለው የሚታሰቡ ነውሮችን መተግበር

በተመረጡት ተጠኝ ማህበረሰቦች በዕለተ ጋብቻ ለሙሽሮቹ የመልካም ምኞት መግለጫ የሆኑ ቁሳቁሶችን ይጠቀማሉ፡፡ የመልካም ምኞት መግለጫ የሆኑ ቁሳቁሶች የሙሽሮችን የወደፊት ህይወት የተስተካከለ በማድረግ ሙሽሮችን ሀብታም ያደርጋሉ ተብለው የሚታሰቡናቸው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ዕለተ ጋብቻ ሲፈፀም ሙሽሮች የሚስተናገዱበት መቆሚያና መቀመጫ ቦታዎች ላይ የሚነጠፉ ንጣፎችና የሚነሰነሱ ሳሮች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህን በወጉ አለመጠቀሙ ከጋብቻ በኋላ ያለው የሙሽሮች ህይወት የተለያዩ ችግሮች ይገጥመዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ የሙሽሮች ቁሳቁሶች በአይነታቸው የተመረጡና የራሳቸው የአጠቃቀም ስርዓት ያላቸው ናቸው፡፡የመልካም ምኞት መግለጫ ከሆኑት የቤት ቁሳቁሶች መካከል የበግ አጓዛ ተጠቃሽ ነው፡፡

ሙሽሮች ቁመው ሲመረቁ የበግ አጓዛ አለማንጠፍ የተከለከለ ነው፡፡ የበግቆዳ (በማህበረሰቡ) በክብር ተቀምጠው ለማጌጫና ለመቀመጫ ከሚያገልግሉ የእንስሳት ቆዳዎች አንዱ ነው፡፡ በአብዛኛው ሰው ቤት የበግ ቆዳ ተንጠልጥሎ ይገኛል፡፡ ለማጌጫ ከመሆኑም ባለፈ የክብር እንግዳ ሲመጣ ከተንጠለጠለበት ቦታ አውርደው ያነጥፉታል፡፡ የበግ ቆዳ የሚሸጠው የታረደው በግ ጥቁር ከሆነናበመጠኑ ትንሽ ከሆነ ነው፡፡ ምክንያቱም ጥቁር መልክበማህበረሰቡ የሚፈለግ አይደለም፡፡ ትንሽ በግ ከሆነም ያንጠለጠሉት ሰዎች በኢኮኖሚ ዝቅተኛ እንደሆኑ አመላካች ነው፡፡ ስለዚህም የሙክት በግ ቆዳ እና የትልቅ በግ ቆዳ ከሆነ ተወጥሮ በመዘርጋት ከደረቀና ከለዘበ በኋላ ለመቀመጫና ለግድግዳ ጌጥ ያገለግላል፡፡ የስር ሚዜው፣ ሙሽራውና ሙሽሪት ገብተው የቃል ኪዳን መሀላቸውን ከጨረሱ በኋላ ለሙሽሮች የበግ አጓዛ ተነጥፎላቸው እንዲቆሙ ይደረጋል፡፡ ከዚያም በኋላ ሽማግሌዎች ይመርቋቸዋል (ምልከታ፣ 14/06/2013)፡፡

የበግ አንዛ አለማንጠፍ ነውር የሆነበትን ምክንያት ሙሽሮች ከተጋቡ በኂላ ሀብታም አይሆኑም ስለዚህ ሙሽሮች ሀብታም እንዲሆኑ በተለይም ከብት እንዲረባላቸው ተብሎ ነው፡፡

ስለዚህ በዕለተ ጋብቻ ቀን የበግ አንዛ አለማንጠፍ ሙሽሮች ድሀ ይሆናሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡ የባልም የሚስትም እድል የተቃና ይሆን ዘንድ ሁለት አንዛ ይነጠፋል፡፡

በሚስት ወይም በባል በኩል ብቻ ቢነጠፍ አንዱ ብቻ ቢሆን የሚስት እጣ ፈንታሀብታም የባል እጣፈንት ድሀ ይሆናል፡፡ የሁለቱም እጣ ፈንታ ሀብት እንዲኖራቸው ሲባል ሁለት አንዛ ይነጠፋል፡፡ ልጆች የጨዋ ቤተሰብ እንደሆኑም ማሳያ ተደርጎ ይወሰዳል(ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ይመኑ መኮነን፣ 15/06/2013)፡፡

ይህ ነውር ባህላዊ የማጌጫ እንስሳት ቆዳዎች ተጠብቀው እንዲቆዩ ከማድረግ ባለፈ ዘመናዊ ንጣፎች በሌሉበት ቦታ ተተክተው እንግዳን በክብር ለመቀበል አገልግለዋል፡፡ ሌላው በዚህ ውስጥ ካለው ተምሳሌት መረዳት የሚቻለው ትውልዱን በእንስሳት ቆዳ ማስተማር ነው፡፡ ለምን የፍየል ወይም የበሬ ቆዳ አልተነጠፈም ነበር የሚለውን ስንመረምርበሬ ሊዋጋና አደጋ ሊያደርስ ወይም ባለቤቱን አልጠመድ ብሎ ሊረብሽ ይችላል፡፡ ፍየልም የክፉ መንፈስ ተምሳሌትና የነገረኛ ሰው ተምሳሌት ተደርጋ ትወሰዳለች፡፡ በግ ግን በሜዳው አሰማርተው ሲተውት አይረብሽም፡፡ ካየው ሁሉ አዝመራ እንደፍየል እሩጦ በመግባት ከሰው ጋር አያጣላም፡፡ በመሆኑም ሙሽሮች ተስማምተው የሚኖሩ ታዛዥና የዋህ እንዲሆኑና በማህበረሰቡ እምነት ሀብታም እንዲሆኑ ለማድረግ ሲባል የበግ አንዛ የመልካም ምኞት መግለጫ ንጣፍ ሆኖ አገልግሏል፡፡

ሌላው ሙሽሮች ሀብታም እንዲሆኑ ለመልካም ምኞት መግለጫ ሆነው ከሚያገለግሉ ቁሶች ውስጥ እርጥብ ሳር ነው፡፡ ሙሽሮች ቁመው በሚመረቁበት ወቅት ደረቅ ሳር መነስነስ የተከለከለ ነው፡፡ በተመረጠው ተጠኝ ማህበረሰብ እርጥብ ሳር ለተለያዩ አገልግሎቶች ይውላል፡፡ እርጥብ ሳር መነስነስ በዕለተ ጋብቻ አውድ ሙሽሮች ሀብታም እንዲሆኑና በሰብል ምርት ውጤታማ እንዲሆኑ ሲባል የመልካም ምኞት መግለጫ ሆኖ ያገለግላል፡፡ መረጃ አቀባዩ አቶ ይመኑ መኮንን  ሲገልፁ እርጥብ ሳሩም ይሁን የበግ አንዛው ሙሽሮቹ ሀብታም ከብታም እንዲሆኑ ብለን እንጠቀመዋለን የሚል ጠቅለል ያለ መልስ ሰጥተውኛል፡፡ እርጥብ ሳር ካልተገኘ በአካባቢው የተገኘው እርጥብ ቅጠል ይነሰነሳል፡፡

በተጠኘው ማህበረሰብ የተለያዩ በዓላት ሲከበሩ እርጥብ ሳር ወይም እርጥብ ቅጠል መነስነስ የተለመደ ነው፡፡ ከብዓላት አንፃር ለመደሰትና ለቤቱ ውበት እንዲሁም ለበዓሉ ድምቀት ሲባል ይነሰንሳሉ፡፡ በመሆኑም በጋብቻ ቀን ደረቅ ሳር መነስነስ ተጋቢዎቹ ሀብት ያጣሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡

ሙሽሮች ከጋብቻ በኋላ ሀብታም እንዲሆኑ ተብለው ከሚከበሩ ነውሮች ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚችለው ጋብቻቸው እንዲባረክ ሲባል የሚመረጡ ቀናት ናቸው፡፡ በተጠኘው ማህበረሰብ ዕለተ ጋብቻ ተግባራዊ የሚሆነው ተጋቢዎች ስለፈቀዱና እነሱን ደስ ስለሚላቸው ብቻ ሳይሆን የማህበረሰቡን ፍላጎት መሰረት አድርገው መሆን አለበት፡፡ በራሳቸው አሳቤ ቀኑን ቢመርጡ በዕለተ ጋብቻቸው ታዳሚና አጃቢ አያገኙም ይህ የሚሆነው ማህበረሰቡ ለቀናት የሚሰጠው ትርጉም ከፍተኛ በመሆኑ ነው፡፡

በአሁኑ ስዓት እየቀረ ያለ ነገር ግን እየተፈፀመ የነበረ  የማደጎ የጋብቻ ቀን እሁድ ማድረግ የተከለከለ ነበር፡፡ ለዚህም የሚያቀርቡት ምክንያት አግብታ የማታውቅ ሴት አሁድ ቀን ካገባች ጋለሞታ (አግብታ ቤት ሰረታ የኖረች ሴት እንደገና ስታገባ የሚሰጥ ስያሜ) መሆኗን ማሳያ ተደርጎ ይወሰድ ነበር፡፡ ስለዚህ የሚጋቡት ማደጎ ከሆኑ ጋብቻቸው ሰኞና ማክሰኞ ተመራጭ ነበር፡፡

እሮብ ቀንዕለተ ጋብቻን መፈፀም ለተለያዩ ችግሮች ያጋልጣል፡፡ እሮብ ቀን አይሁድ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመያዝምክራቸው የጸናበትቀን ነው፡፡ የመጀመሪያው ምክንያታቸውአሮብ ቀን እየሱስ ክርስቶስና ዮሐንስ በመልክ ስለሚመሳሰሉ ይሁዳ እየሱስ ክርስቶስን ለአይሁድ ወንበዴዎች ሰላም ብሎ ያሳየበት ቀን ነው፡፡ በመሆኑም ጋብቻቸውን እሮብ ቀን የፈጸሙ ወጣቶችም ከጋብቻ በኋላ ለሚኖራቸው ህይወትም ሆነ በጋብቻ ቀናቸው ችግር አያጣቸውም ተብሎ ይታሰባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከሩቅ ቦታ የሚመጡ የተጋቢ ቤተሰቦች ዕለተ ጋብቻውን ላይታደሙ ይችላሉ በሚል አሳቤ ነው፡፡ ምክንያቱም እሮቡ ቀን መንገድ መውጣት አደጋ ያጋጥማል ተብሎ ስለሚታሰብ አብዛኛውን የማህበረሰብ ክፍል ከቤቱ እርቆ መሄድአይፈልግም፡፡ ሁለተኛው ለዚህ ቀን የሚያቀርቡት ምክንያት የስራ ቀንስለሆነ በመደበኛ ጋብቻ ለሚጋቡ ሰዎችም ሆነ በጋብቻ ቀኑ ለሚታደሙ የመንግስት ሰራተኞች አይመችም፤ስራን ለመስራት እንቅፋት ይሆናል ተብሎ ይታሰባል (ቃለ መይቅ፣ ባንቲገኝ ስሜነህ፣ 25/05/2013/)፡፡

ሶስተኛው ለዚህ ቀን የሚቀርብ ምክንያት ፆም ነው የሚል ሲሆን በፆም ቀን ዕለተ ጋብቻን ማድረግ ተጋቢዎቹ ከጋብቻ በኂላ ሀብት አያገኙም፤የያዙት ሁሉ በረከት አይኖረውም ተብሎ ይታሰባል፡፡

በአጠቃላይ እሮብ ቀን ጋብቻን ማድረግ ሙሽሮች እለተ ጋብቻቸውምሆነ ከጋብቻ በኂላ ያለው ህይወታቸው አይባረክም የሚል እምነት አላቸው፡፡ በመሆኑ ለጋብቻ የሚመረጡትቀናት እሁድና ናቸው፡፡

### 5.2.3. የስር ሚዜንና አሳዳሪን በተመለከተ የሚፈሯቸው ነውሮች

ከዕለተ ጋብቻ ነውሮች ውስጥ የስር ሚዜንና አሳዳሪን የተመለከቱ ነውሮች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ የጋብቻ ቀን ሲታሰብ የስር ሚዜና አሳዳሪ ተያይዘው የሚነሱና ለጋብቻው መሳካት ወሳኝ የሆኑ ሰዎች ናቸው፡፡ ማህበረሰቡ የስር ሚዜንና አሳዳሪን በተመለከተ የሚፈራቸው ነውሮች አሉ፡፡

የስር ሚዜና አሳዳሪ በዘፈቀደ የሚመረጡ ሰዎች ሳይሆኑ በጥንቃቄ ለሙሽሮችና ለእለቱ ታዳሚዎች ታማኝ ሆነው ሀላፊነታቸውን የሚወጡ መሆን አለባቸው፡፡ በማህበረሰቡ እሳቤ ሙሽሮችን ለክፉ መንፈስ እንዳይጋለጡና ዕለተ ጋብቻ እንዳይረበሽ ለማድረግ የስር ሚዜና አሳዳሪ ዘመድ መሆን አለባቸው፡፡ የስር ሚዜንናአሳዳሪን ባዳ ማድረግ የሚፈራና የተከለከለ ነው፡፡

የሙሽሮች ሰርግ በሰላም ይጠናቀቅ ዘንድ የስር ሚዜ ከፍተኛ የሆነ ድርሻ አለው፡፡ የስር ሚዜ የሙሽሪትን ሚስጥር እጠብቃለሁ፤ እሱ የነገረኝን ለእሷ እሷ የነገረችኝን ለእሱ አልናገርም፤ ልብሷን አጥባለሁ በማለት ቃለ መሀላ ይፈፅማል፡፡ በመሆኑም የሙሽሪትን ልብስ አጥቦ መታጠቢያ ሳሙና ከሌላት ሳሙና አቅርቦ፣ የምትወደውንና የምትጠላውን በመጠየቅ ምግብ ማቅረብ የስር ሚዜው ሀላፊነት ነው፡፡ በሙሽራው ቤተሰቦች እምነት ተጥሎበት እንደፈለገ የመንቀሳቀስ መብት ኖሮት ቢያንስ እስከ አስር ቀን ከጎኗ መለየት እንደሌለበት ቃለ መሀላ ይገባል፡፡ በመሆኑም ይህንን ሁሉ ቃለ ምሀላ የሚጠብቅ ዘመድ እንጅ ባዳ እንዳልሆነ በተመረጠው ተጠኝ ማህበረሰብ ዘንድ የሚታመን ነው፡፡

አሳዳሪ ልክ እንደ ሚዜ ሁሉ በሰርጉ ቀን የተለያዩ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ ከፍተኛ የሆነ ሚና አለው፡፡ የዕለተ ጋብቻ ቀን በሰላም ይጠናቀቅ ዘንድ የወጣቶች የርስ በርስ ግጭት እንዳይፈፀም ለማድረግ እንዲሁም ሙሽሮችን ከጠላት ለመከላከል ከፍተኛ የሆነ የስራ ድርሻ አለው፡፡

በመሆኑ የስር ሚዜም አሳዳሪም ባዳ አይደረግም፡፡ ማህበረሰቡ ዘመድ ካልሆነ ሰው ጋር አብሮ መብላት፣ አብሮ መጠጣት፣ በችግር ጊዜ መረዳዳት የዘወትር ተግባሩ ነው፡፡

ነገር ግን ከፍተኛ የቤተሰብ ሃላፊነቶችን በተለይም ጋብቻን የተመለከቱ ተግባሮች ለማስፈፀም፤ በቋሚነት ዕለተ ጋብቻን እንዲያስተናግድ ማድረግ ችግር ያስከትላል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ስለዚህም ዘመድ ያልሆነን ሰው ሀላፊነት አይሰጡም፡፡

የስር ሚዜንና አሳዳሪን ባዳ ማድረግ የሚያስከትለው ችግር ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ የቀረበላቸው መረጃ አቀባዮች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ችግሮች እንደሚደርሱ ጠቅሰዋል፡፡

አንደኛ የስር ሚዜና አሳዳሪ ባዳ ማድረግ ቃለ መሀላቸውን ያፈርሳሉ የሚል እምነት አላቸው፡፡ የስር ሚዜና አሳዳሪን ባዳ ማድረግ ከላይ የተዘረዘሩትን ማለትም ሙሽሪትን ለመንከባከብ፣ ከሙሽራው ጋር የመጡትን እንግዶች ንብረታቸውን ቆጥሮ ለማስረከብ፣ ከሚዜዎችና ከሙሽሮች ውጭ ያሉ ሰዎች ሙሽሮች ካሉበት ቤት እንዳይገቡ ለማድረግ የገቡትን ቃለ መሀላ ያፈርሳሉ የሚል እሳቤ አላቸው፡፡ ስለዚህ የስር ሚዜው ባዳ ከሆነ የሙሽሪት ወይም የሙሽራውን ሴት ዘመዶች ይደፍራል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ከጋብቻ ቀን እስከ መልስ ከዚያም ባለፈ እስከ 10 ቀን ያለውን ጊዜ ታምኖ የስር ሚዜው ሙሽሪትን ተንከባካቢና ጠባቂ እንዲሆን ሀላፊነት ይሰጠዋል፡፡ ስለሆነም ሙሽራው ሙሽሪትን አምኖ ከሚዜው ጋር ይተዋታል፡፡ በዚህ ሰዓት የስር ሚዜው ባዳ ከሆነ የሙሽራውን ሚስት ይደፍርበታል የሚል እምነት አላቸው፡፡ (ካሳየ ፈቃዱ፣ቃለ መጠይቅ፣ 05/06/2013/)፡፡

ልክ እንደ የስር ሚዜ ሁሉ አሳዳሪን ባዳ ማድረግዕለተ ጋብቻን ሊረብሹ የሚችሉ ወንጀሎች እንዲፈፀሙ ያደርጋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ የእርስ በእርስ ግጭት፣ የሀብትና ንብረት መጥፋት ችግር ይደርሳል፡፡ አሳዳሪ ባዳ ከሆነ የሙሽሪት ቤተሰቦች ያዘጋጁትን ምግብ ለሚዜዎችና ለሙሽሮች በስርዓት አያስተናግድም፤ የሙሽሪትን ቤተሰቦችም ቤት ያላፈራውን አምጡ እያለ በሚዜዎች ፊት ያሳቅቃቸዋል የሚል እምነት አላቸው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ሙሽሮች ከተቀመጡበት ቦታ ሌላ ሰርጎ ገብ ጠላት መጥቶ የሙሽሮችን ንብረት ይሰርቃል፡፡ እነሱንም ለጠላት አሳልፎ ይሰጣል የሚል እምነት አላቸው፡፡ በሚዜዎች ንብረት መጥፋት ምክንያት ግርግር ይፈጠር እና አጋጣሚውን የሚፈልግ ሰው በመጠጥ

መንፈስ እረብሻ ያነሳል፡፡ ሙሽሪት ከዛሬ ቀደም ሌላ ሰው የማያውቀውንቃል ኪዳን ፈፅማ በአለመግባባት የተወችውሰው ካለ እረብሻ አንስቶ ሙሽሪትን ለመንጠቅ ያስባል፡፡

አሳዳሪው ዘመድ ከሆነ ግን ለእንደዚህ አይነት ሰዎች አሳልፎ አይሰጥም፤ የቤተ ዘመዱን ችግርና ሚስጥር ስለሚያውቅ ችግሩ ከመድረሱ በፊት ይጠነቀቃል ተብሎ ይታሰባል (ቃለ መጠይቅ፣ድሉ ተፈራ፣ 06/06/2013)፡፡

አሰዳሪን ባዳ ማድረግ የተከለከለ መሆኑ በማህበረሰቡ የጋብቻ ቀናት ግጭቶች ከመከሰታቸው በፊት ቅድመ መከላከል በመሆን አገልግሏል፡፡ እነዚህም የሙሽሮችን ንብረት እንዳይዘረፍ፣ ሙሽሮች በጋብቻቸው ቀን በሚፈጠር እረብሻ እንዳይደናገጡ፣ ዕለተ ጋብቻውን ለመታደም የመጡት ሰዎችም ተረጋግተው እንዲስተናገዱ ለማድረግና እንደ ሙሽሪት ቤተሰቦች የኑሮ ደረጃ ሚዜ እንዲያስተናግድ ለማድረግ ሚናው የጎላ የነውር አይነት ነው፡፡

ይህ ነውር በጋብቻ ቀን በስካር መንፈስም ይሁን ታስቦበት በስር ሚዜ የሚፈጠርን ፆታዊ ትንኮሳዎች ለመከላከልም ይጠቅማል፡፡ ሙሽሪትን ሳትሳቀቅ የፈለገችውን ነገር እንድትጠይቅ፣ በማድረግ የሴቶች ፆታዊ ጥቃት የሚፈፀምባቸውን መንገዶች አስቀድሞ ለመቆጣጠር ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ አለው፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ የስር ሚዜን ባዳ ማድረግ በማህበረሰቡ እምነት የሚከተሉትን ችግሮች ያስከትላል፡፡[3]

**ሁለተኛ** የስር ሚዜን ባዳ ማድረግ የሙሽሮችንነገመና በማጋለጥ ለሀፍረት ይዳርጋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ የስር ሚዜን ባዳ ማድረግ በግብረ ስጋ ግንኙነት፣ በአነጋገር፣ በአመጋገብና በሽንት ቤት አጠቃቀም ዙሪያ በሙሽራውና በሙሽሪት በኩል የሚታዩ የነውሮች ጥሰት ቢያጋጥሙ ሚስጥራቸውን አውቀውም ይሁን ሳያውቅ የፈጸሙትን ነውር ለሰው በመናገር ያሳፍራቸዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በማህበረሰቡ እምነት ሙሽራውና ሙሽሪት የግብረስጋ ግንኙነት መፈፀም ያለባቸው በቀደሙት ዘመናት ከአስር ቃን በኋላ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ስዓት ግን ከአራት ቀን

---

[3]አሳዳሪና የስር ሚዜ ልዩነት አላቸው፡፡ የስር ሚዜ ሙሽሪትን ሊንከባከብ በቃለ መሀል የሚረከብ ሲሆን አሳዳሪ ‹‹በልክ አውጥቼ በልክ አስገባለሁ›› ብሎ ቃለ መሀላ በመፈፀም ሙሽሪትን ለመውሰድ የመጡ ሚዜዎችን ሽመል ቆጥሮ የሚረከብ፣ ንብረታቸውን ከዘራፊ ሰዎች የሚቆጣጠር እና ምግባቸውን የሚያቀርብ የሚያስፈልጋቸውን ከሴት ቤተሰቦች እየጠየቀ የሚያስተናግድ ነው፡፡ መረጃው ከአቶ ድሉ ተፈራ ጋር በቀን 06/06/2013 ከተደረገ ቃለ መጠይቅ የተወሰደ ነው፡፡

በኋላ ወይም ከመልስ በኋላ ነው፡፡ ሙሽሮች የግብረ ስጋ ግንኙነታቸውን መፈፀም ያለባቸው ሙሽራው ሙሽሪት ከመምጣቷ በፊት አስቀድሞ ከቤታቸው በጓሮ ወይም ከከብቶች ቤት ውስጥ በሰራው አልጋ ላይ ነው፡፡ ከመልስ በኋላ እንግዳው ወጥቶ ሲጠቀልል ሙሽራው አስቀድሞ በሰራው አልጋ የግብረ ስጋ ግኙንታቸውን ይፈፅማሉ (ቃለ መጠይቅ፣ አገውላንቺ መንግስቴ፣ 07/06/2013)፡፡

ሙሽራው ሙሽሪትን ከመልስ በፊት ወይም ወዲያው እንዳመጣት ማታውን ከሷ ፈቃድና ከተቀመጠው ህግ ውጭ በሆነ መንገድ እንዳይደፍራት የስር ሚዜው ከፍተኛ ቁጥጥር ማድረግ እንዳለበት ይታመናል፡፡ ሚዜው ተቆርቋሪ ካልሆነና ባዳ ከሆነ ሙሽራው እንዲደፍራት መብት በመስጠት ቤት ዘግቶ ትቷቸው ይሄዳል፡፡ በዚህ ሰዓት ሙሽሪት ከጋብቻ በፊት የግብረ ስጋ ግኘኙነት ፈፅማ የማታውቅ ከሆነ ልትደናገጥና ልትጮህ ትችላለች፡፡ ይህ አይነት ችግር ተፈፅሞ ከሆነ ጧት ለመመረቅ ከዳሱ ወደ ሙሽራው ቤተሰቦች መኖሪያ ቤት ሲገቡ ታዳሚውን ለማየት ያፍራሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡ ሙሽራውንም ምን አይነት ሴሰኛ ነው እያሉ ይወቅሱታል፡፡ የስር ሚዜ ነውር ሰራ የሚባለውም እንደዚህ አይነት ስህተቶች ሲፈፀሙና በአጠገባቸው ሆና ሳይመክርና ሳይቆጣጠር ሲቀር ነው (ካሳየ ፈቃዱ፣ቃለ መጠይቅ፣ 05/062013)፡፡

ይህ ነውር የሙሽሮች የግብረ ስጋ ግንኙነት መቼ እና የት መደረግ እንዳለበት ማህበረሰቡ ያወጣው ህግ ነው፡፡ በመሆኑም ነውሩ የግብረ ስጋ ግንኙነት ካለሰዓቱና ካለቦታው መፈፀም እንደሌለበት ከተፈፀመም አሳፋሪ ድርጊት እንደሆነ ለማስተማር ይጠቅማል፡፡

**ሶስተኛ** የስር ሚዜ ባዳ ከሆነ በሙሽሮች ላይ የሚታዩ አንዳንድ ስህተቶችን አይሸፍንም ተብሎ ይታሰባል፡፡ ሙሽራው ለመልስ ተጠርቶ ሲሄድ የሙሽሪትን ቤተሰቦችንና የአካባቢውን ሰው እንዳያፍር የስር ሚዜው ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡ ሙሽራው ከሙሽሪት ቤተሰቦች ቤት ተጠርቶ ሲሄድ የስር ሚዜው እና ከሌሎች ሚዜዎች አንድ ላይ ሆነው አብረው ይሄዳሉ፡፡ በሙሽሪት ቤት ተቀምጠው ሲበሉ ሲጠጡ ሙሽራው ስህተት እንዳይፈፅም በማንሾካሾክ የሚመክር የስር ሚዜ ነው፡፡ ለመብላት እና ለመጠጣት እንዳያፍርም ያበረታታዋል፡፡ ሙሽራው መልስ ጨርሶ ወደ ቤተሰቦቹ ቤት ሲሄድ ለአቅመ ሄዋን የደረሰች ሴት ከሙሽራው ቤተሰቦች ቤት አብራ መሄድ አለባት፡፡ በዚህ ሰዓት ሙሽሪት ተመልሼ ወደ ባል ቤተሰቦች ቤት አልሄድም ብትል

ሙሽራው አዲስ በመሆኑ ለማሳመንና ለመናገር ይከብደዋል፡፡ በዚህ ሰዓት የስር ሚዜው ካለ ግን እምቢ ብትል እንኳ አማላጅ ይሆነዋል ተብሎይታሰባል፡፡

ሙሽራው ከሙሽሪት ቤተሰቦች ቤት የተለያዩ ስህተቶችን ቢፈፅም እንኳ ገመናውን አይሸፍንለትም፤ ከታዳሚው ጋር አብሮሊያፌዝበት ይችላል፡፡ ዘመድ ቢሆንማ የእኔም ሀፍረት ነው ስጋየ አይደል ብሎ ያስባል (ቃለ መጠይቅ፣ ምናለ ጣሹ፣11/06/2013/)፡፡

የስር ሚዜንና አሳዳሪን ባዳ ማደረግ የሙሽሮችን ደህንነት ለመጠበቅና ዕለተ ጋብቻ በሰላም እንዲጠናቀቅ ለማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ የስር ሚዜና አሳዳሪን የተመለከቱ ነውሮች ታማኝነትን ተያቂነትን እና ሚስጢር ጠባቂነትን ለማስተማር ይጠቅማሉ፡፡ የስር ሚዜው ሀላፊነቱን ካልተወጣ በሙሽሪት ቤተሰቦችና በአካባቢው ማህበረሰብ ወቀሳ ይደርስበታል፡፡ ድጋሜ በስር ሚዜነት እንዳይመረጥ በአካባቢው ማህበረሰቡ ሊታገድ እንደሚችል ሀላፊነቱን ማይወጣ የስር ሚዜ ሚመርጠው ወጣትም እንደሌለ ከመረጃ አቀባዮች ለመረዳት ተችሏል፡

በአጠቃላይ ዕለተ ጋብቻን የተመለከቱ ነውሮች በሙሽሮች ላይ ይደርሳል ተብሎ የሚታሰብን ክፉ መንስ ለመከላከል፣ እለተ ጋብቻ በሰላም እንዲጠናቀቅለማድረግ፣ ሙሽሮችን ሊያፍሩና ግራ ሊያገቡ የሚችሉ ድርጊቶች እንዳይከሰቱ ለማድርግ የሚጠቅሙና ሙሽሮች ከጋብቻ በኋላ ያላቸው ህይወት (ሀብትና ጤናን በተመለከተ) መሰናክል የበዛበት እንዳይሆን ሲባል የሚከበሩ ናቸው፡፡እነዚህን ነውሮች መጣስ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚያስፈራ ተግባር ሲሆን በስር ሚዜና በአሳዳሪ፣ በአጋቢ ዳኞችና በሙሽሮች ከተጣሱ ለክፉ መንፈስ በማጋለጥና የእርስ በርስ ግጭትን በመፍጠር ተጋቢዎችና የተጠኘው ማህበረሰብን አባላት አብሮነት ያሻክራሉ ተብለው የሚታሰቡ ናቸው፡፡

## 5.3. የድህረ ጋብቻ ነውሮች ትንተና

የዕለተ ጋብቻ ነውሮች ባልና ሚስቱ ከጋብቻ በኋላ ለሚኖራቸው የትዳር መፅናት መሰረቶች ናቸው፡፡ ማለትም የዕለተ ጋብቻ ነውሮች ሳይጣሱ በሰላም ከተጠናቀቁ የተጋቢዎችንከጋብቻ በኋላ ያለውን ኑሮ የተስተካከለ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡ ከጋብቻ በኋላ ባልና ሚስቱ ትዳራቸው እንዲፀና፣ ባልና ሚስቱ ከጎረቤቱ እና ከአካባቢው ጋር ተፋቅረው እንዲኖሩ የሚያደርጉ ሰነፍ ባልና ሚስትን የሚገልፁ ነውሮችና ተረኮች ናቸው፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ከጋብቻ በኋላ ያሉ ነውሮች አብዛኛዎቹ የባልና ሚስቱ የመጥፎ ስነምግባርና የመልካም ስነ ምግባር

መለያዎች ሲሆኑ እነዚህም ቢጣሱ ለትዳር መፍረስና ለባልና ሚስቱ ግጭት መንስኤ መሆንን፣ በአካባቢው ጠብን አስነስቶ መገዳደልንና ድህነትን ያስከትላሉ ተብለው የሚታሰቡ ናቸው፡፡ማህበረሰቡ ድህረ ጋብቻ ነውሮች ሲጣሱ የጣሰውን አካል የሚቀጣበትና ነውሩ ተፈፅሞበት ያለውን አካል በመምክር የሚያረጋጋበት መንገድ አለው፡፡

በአጠቃላይ ድህረ ጋብቻ ውስጥ የሚጠቃለሉና በመረጃ ስብሰባ ወቅት የተገኙ መረጃዎች የሚስት ቤተሰቦችን ጣልቃ ገብነት ለመከላከል በአማች የሚከበሩ ነውሮች፣ ሚስት ባሏን ማክበሯን የሚያሳዩ ነውሮች፣ ስንፍናንና ያታዊ ትንኮሳን ለማውገዝ በባል የሚከበሩ ነውሮች፣የከብት እና የሰው በሽታን እንዳያመጡ የሚያከብሯቸው ነውሮች እና ድህረ ጋብቻ አለባበስና አጊያጊያጥ ነውሮች በማለት በአምስት ዋናዋና አቢይ ርዕሶች ተከፋፍለው ቀርበዋል፡፡

### 5.3.1. የሚስት ቤተሰቦችን ጣልቃ ገብነት ለመከላከል በአማች የሚከበሩ ነውሮች

በተጠኘው ማህበረሰብ አማች ማክበር የሚጠበቅበት ነውሮች አሉ፡፡ አማችከሚስቱና ከሚስቱ ቤተሰቦች ጋር ያለው ግንኙነትና አብሮነት ይቀጥል ዘንድ አማችን የተመለከቱ ነውሮች መከበር ወሳኝ ነው፡፡ አማችን የሚመለከቱ ነውሮች ከተጣሱ በሚስቱ ቤተሰቦች ቁጣን የሚቀሰቅሱና ጣልቃ ገብነትን ሊያስከትሉ የሚችሉ ናቸው፡፡ የሚስት ቤተሰቦች በአማችን የሚቆጡትና ልጃቸውን ለመፋታት ጣልቃ የሚገቡት ሰነፍ መሆኑን የሚገልፅ ድርጊት፣ ሚስቱንና የሚወለደውን ልጅ እንዳልወደደ በሚያሳያቸው ሁኔታዎችና የሚስቱን ቤተሰቦች እንደናቃቸው የሚያመላክቱ ነውሮችን ጥሶ ሲገኝ ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህን ጉዳዮች የተመለከቱ ነውሮች በአማች መከበር የሚገባቸው ናቸው፡፡

አማች የሚስትን ቤተሰቦች ሊያስቀይሙ የሚችሉ ነውሮችን ካላከበረባልና ሚስቱ እስከ መፋታት ሊያደርሳቸው ይችላል፡፡ የሚስትን ቤተሰቦች ሊያስቀይሙ ከሚችሉ ነውሮች ውስጥ አማች ከአማት ቤት ሲጠራ መቅረት፣ አማች (የልጅ ባል) ሚስቱ ስትወልድ አንቀልባና የሚታረድ በግ ሳይዝ መሄድ፣አማች አማቱ(የሚስቱ አባት) ወደ ቤት ሲገባ አለመነሳት ተጠቃሽ ነውሮች ናቸው፡፡

እነዚህ ነውሮች በልጅ ባል (በአማች) መከበር የሚገባቸው ናቸው፡፡ ካልተከበሩ የሚስት ቤተሰቦችን ቁጣ በመቀስቀስ በባልና ሚስቱ መካከል ጣልቃ ሊገቡ የሚችሉበትን አጋጣሚ የሚፈጥሩና በመካከላቸው ያለውን ግኙነት ሊያሻክሩ የሚችሉ ናቸው፡፡

አማች ከአማት ቤት ሲጠራ መቅረት የሚስትን ቤተሰቦች ሊያስቀይሙ ከሚችሉ ነውሮች ውስጥ ተጠቃሽ ነው፡፡ ቤተሰብ ጣልቃ ከሚገባባቸው እና ልጃቸውን ለማፋታት ከሚሞክሩባቸው ምክንያቶች ደግሞ ባል የጠሩትን የሚስትን ቤተሰቦች አክብሮ በተባለው ጊዜና ቀን መገኘት አለመቻል ነው፡፡ ይህ ካልሆነ የሚስትን ቤተሰቦች ንቆና ጋብቻውም እንዳላስደሰተው ቆጥሮ ቀረ ያስብለዋል፡፡

ይህ ነውር በሚስት ቤተሰቦች ትኩረት የሚሰጠው እና እንደዋዛ የማያሳልፉት ተግባር ነው፡፡ ነውሩ ተጋቢዎቹ ቤት ከያዙና ከወለዱ በኂላ ያለውን ጊዜ አይመለከትም፡፡ ምክንያቱም ሀብት ንብረት ይጠፋል፤ ልጆችን የሚንከባከብ አይኖርም ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ ስለዚህም ባል ወይም ሚስት ብቻ ሊሄዱ ይችላሉ፡፡

ሚስት ከባሏ ቤተሰብ እያለች ቤተሰቦቿ ሲጠሩ ባሏ አልሄድም ቢላት ጥላው መሄድ የተከለከለ ነው፡፡ ለዚህም የሚያቀርቡት ምክንያት ባል ከእርሱ ቁጥጥር ውጭ እንደሆነችና እንደናቀችው ይቆጠራል፡፡ ቤተሰቦቿም ልጃችን አውሬ ቢያስደነግጣት ውሃ ቢበላትለምን ብቻዋን ሰደዳት ብለው የልጅ ባላቸውን (አማቻቸውን) ይቆጡታል(ቃለ መጠይቅ፣ምናለ ጣሹ፣ 11/06/2013)፡፡

አማች ከሚስቱ ቤተሰቦች ቤት ሂዶ መሳሪያና ከዘራ(የሽመል አይነት) ይዞ መቀመጥ የተከለከለ ነው፡፡ አማች ከሚስቱ ቤተሰቦች ተጠርቶ ሲሄድ ቤተሰቦቹ ሽመሉን ይቀበሉታል፡፡መሳሪያ ይዞ ከሆነ ለሴት አማት እንድታስቀምጠው ይሰጣታል፡፡ ሽመሉንና መሳሪያ ይዞ የሚቀመጥ አማችየሚስቱን ቤተሰቦች የማያከብርና መጥፎ ስነ ምግባር ያለው ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ምግብ የሚያቀርቡና ቡናና ጠላ የሚያሳልፉ ሰዎችን የያዘው ሽመል ጠልፎ ይጥላቸዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡

ከዘራ ወይም መሳሪያ ይዞ መቀመጥ በማህበረሰቡ የትዕቢተኛ ሰውና በጥሩ ስነ ምግባር ያላደገ ወንድ ልጅ መገለጫ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የሚስቱን ቤተሰቦች የሚያከብር አማች ከዘራውንና መሳሪያ ካለው መሳሪያውን ይዞ አይቀመጥም፡፡

> የልጅ ባል ከአማቱ ቤት ሲሄድ መሳሪያ ካለው መሳሪያ ይዞ ይሄዳል፡፡ ከሌለው ከዘራውን ይዞ ኩታውን ለብሶ ይሄዳል፡፡ ቤት ሲደርስ ድምፁን በሩቅ ያሰማል፡፡ የሚስቱ ቤተሰቦችም ውሻ እንዳይባላቸው ወጠው ከዘራውንና መሳሪያውን ተቀብለው ያስቀምጡለታል፡፡ በዚህን ሰዓት አሱ ይገፍ እቀመጣለሁ ቢል ነውር ነው፡፡ ምክንያቱም

> የሄደው ከጠላት ቤት አይደለም። እነሱም እንዳላመናቸውና ሰላማዊ ሰው እንዳልሆነ ይቆጥሩታል። ጥሪውን አክብሮ የመጣ ሳይሆን ጠብ ለማንሳት እና በሆዱ ቂም ይዞ እንደመጣ መለያ ተደርጎ ይወሰዳል (ቃለ መጠይቅ፣ ድሉ ተፈራ፣ 06/06/2013)።

ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ የትዳር ህይታቸው ሰላማዊ ሆኖ እንዲቀጥል አማች የሚስት ቤተሰቦችን በአነጋገሩ፣ በአመጋገቡ፣ በአቀማመጡና በአለባበሱ ማስቀየም የለበትም። በአነጋገሩ ከሚስቱ ቤተሰቦች በተለይም ከእናትና ከአባቷ በፊት ቶሎ ቶሎ የሚናገር ከሆነ እንዳላከበራቸው መገለጫ አድርገው ይወስዱታል። በዚህም ስርዓት የሌለው ተደርጎ ስለሚቆጠር በባልና ሚስቱ ጣልቃ በመግባት እንድትፈታው ይገፋፏታል። ሲናገር የተረጋጋና ሀሳባቸውን እንዲገልፁ ቅድሚያ ለእነሱ መብቱን መስጠት የሚስቱን ቤተሰቦች እንዳከበረ መገለጫ ነው።

ይህ ነውር ከቤተሰብ ጋር ያሉ እና ጎጆ ያልወጡ ተጋቢዎችን የሚመለከት ነው። አማች ከሚስት ቤተሰቦች ቤት በየበዓላቱ ይጠራል። ባልና ሚስት ቤት ሳይወጡ (ከቤተሰቦቻቸው ጋር እያሉ) ሚስት አንድ ወር ከቤተሰቧ ሌላኛውን ወር ከባሏ ቤተሰቦች እየሆነች ታገለግላለች። የሚስት ቤተሰቦች ልጃቸው ስትናፍቃቸው እና እሷም ቤተሰቦቿን እንድታይ ሲፈልጉ ይጠሯታል።

በዚህ ሰዓት ባሏ አልሄድም ቢል የተከለከለ ነው። ለዚህም ምክንያቱ ባል የሚስትን ቤተሰብ አያከብርም፤ የሚስቱን ፍላጎትም አይጠብቅም። ሳይወልድ የኮራውና አማቶቹን ንቆ የቀረ ለልጃቸው አይሆንም ተብሎይታሰባል።

> በመጀመሪያው ቀን ሲጠራ የቀረ የልጅ ባል ለሁለተኛ ጊዜደግመው ይጠሩታል። የዛን ጊዜ ሲመጣ ልጃችን ቶሎቶሎ ስንጠራህ አምጠህ ካላሳየኸን አንሰጥም። ከኛ ጋር ትከርማለች ብለው ሳይሰጡይልኩታል። ከዚያም በሌላ ቀን መጦ ተለማምኖ ይወስዳታል። በሚስት ቤተሰብና በአማችመካከል ያለው መዋደድና መከባበር ይቀንሳል (ቃለ መጠይቅ፣ ምናለ ጣሹ፣ 11/06/2013)።

ይህ ነውር በቤተሰብ እና በአማች (በልጅ ባል) አለመግባባት ምክንያት የሚመጡ ግጭቶች እንዳይኖሩ ለማድረግ ይጠቅማል። ባልና ሚስት ተፋቅረው ይኖሩ ዘንድ ቤተሰብ የልጃቸውን ባል መውደድና ማክበር ባልም የሚስቱን ቤተሰብ ትዕዛዝ ማክበር ጥሩ ትዳርን ለማፅናት የሚጠቅም ስልት ነው። ለዚህም ባልና ሚስቱ በቤተሰብ ቁጥጥር ስር እስካሉ ድረስና

ተጋቢዎች የራሳቸውን ቤት እስካልመሰረቱ ድረስ የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ለመፋታት ያደርሳቸዋል፡፡

ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪ ቢጣሱ የሚስትን ቤተሰቦች ሊያስቀይሙ ከሚችሉና አማች ከሚስት ቤተሰቦች ሲሄድ ማክበር ከሚገባው ነውሮች ውስጥ አማች(የልጅ ባል) ሚስቱ ስትወልድ አንቀልባና የሚታረድ በግ ሳይዝ መሄድ ተጠቃሽ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ሴት ልጅ የመጀመሪያ ልጇን የምትወልደው ከእናቷና ከአባቷ ቤት ነው፡፡

8 ወር ሲሆናት ከእናቷና ከአባቷ ቤት ትሄዳለች፡፡ ይህ የሚሆነው የተለያዩ ችግሮች በህፃኗና በእሷ ላይ ይደርሳሉ ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የሚንከባከባት ሰው አይኖርም፤ ቢኖሩም እንደ እናት አይሆኑም፡፡ ስለዚህም ለክፉ መንፈስ ልክፍት ትጋለጣለች ተብሎ ይታሰባል፡፡ መጀመሪያዋ እንደመሆኑ መጠን የልጅ አስተዛዘልና አስተቃቀፉን አትችልበትም ተብሎ ይታሰባል፡፡ በሰላም ተገላግላ ወለደች ሲባል ባል የሚታረድ በግ እና የልጅ ማዘያ አንቀልባ ሳይዝ መሄድ የተከለከለ ነው፡፡ የበጉስጋ በምጥ ለተጎዳው ሰውነቷ መጠገኛ ይሆናል ተብሎ ይታሰባል፡፡

አንቀልባው (የልጅ ማዘያ) ለተወለደው ልጅ ማዘያ ይሆን ዘንድ የሚገዛ ሲሆን ባይገዛ ግንሚስት በወለደችው ልጅ ባል ደስተኛ እንዳልሆነ ማሳያ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ይህንን ባያደርግ ለሚስቱ ፍቅር እንደሌለው የሚስቱ ቤተሰቦች ይቆጥራሉ፡፡ ባይኖረው እንኳ ተበድሮ ይገዛል፡፡የሚስት ቤተሰቦች የልጃቸው ባል ሚስቱን የማይንከባከብ መስሎ ስለሚታያቸው ለእሱያላቸው አመለካከት እንደ ቀደመው አይሆንም (ቃለ መጠይቅ፣ ምናለ ጣሹ፣ 11/06/2013)፡፡

ይህነውር ባልለሚስት ያለው ፍቅር እስከምን ድረስ ነው የሚለውን ለመገምገም የተጠቀሙበት ነው፡፡ ባል ለሚስቱ ያለውን እንክብካቤ ማሳያ በመሆንም አገልግሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቤተሰቦቿ ለባሏ ያላቸው ፍቅር እንዲቀጥልና በሁለቱ መካካል ያለው ግንኙነት የሻከረ እንዳይሆን አገልግሏል፡፡

ሌላው አማች ወንድ አማቱን እንዳላከበረ ከሚያሳዩ ድርጊቶች ውስጥ አማት የሚስቱ አባት(አማቱ) ሲገባ አለመነሳት ነው፡፡ አማት (የሚስቱ አባት) ከብት ለማሰማራት፣ ሽንት ቤት ለመጠቀምና ሌሎችን ስራዎች ለማከናወን ከቤት ውጭ ቆይቶ ሲገባ አማች በመነሳት እና ዝቅ ብሎ ‹‹ይቀመጡ›› በማለት እስኪቀመጡ ይቆማል፡፡

አማትም በተራው የልጅ ባሉን (አማቹን) አመስግኖ ይቀመጣል፡፡ [4] ይህ ነውር የመከባበር እሴትን ለማስተማር እና የሰዎችን ግንኙነት ለማጠናከር ከፍተኛ የሆነ ሚና አለው፡፡ አማቱ ሲገባ ሳይነሳ ከቀረ በአማቱ ከፍተኛ የሆነ ቁጣን ይቀሰቅሳል፡፡ ምክንያቱም አማች አማቱን እንዳከበረውና እንደናቀው እንዲሁም አማቻቸው ስርዓታ አልባ እንደሆነ የሚያስቆጥር ነውር ነው፡፡ በዚህ ምክንያት አማትና አማች ላይግባቡና በሀሳብ ላይስማሙ ይችላሉ፡፡ አማት (የሚስት አባት) በግልፅ እንዴት ብትንቀኝ ነው የማትነሳ ብሎ ሊወቅሰው ይችላል (ይመኑ መኮነን፣ ቃለ መጠይቅ፣15/06/2013)፡፡

አማች ከሚስት ቤተሰቦች ቤት ሲሄድ ማክበር ከሚገባው ነውሮች ውስጥ ከአማት ቤት ሂዶ ምግብ እስኪዘጋጅ ከቤት ወጥቶ መቆየትን ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ነባርም ሆነ አዲስ የልጅ ባል ጠዋት ከተነሳ በኋላ ስራ ከሆነ አጨዳ፣ ወይም እርሻ ከአማቱ ጋር ወይም ከሚስቱ ቤተሰቦች ጋር ወጥቶ ይቆያል፡፡ ማህበረሰቡ ስራ የማይሰራበት ቀን ከሆነ በሬዎችን ወይም ላሞችን ከሚያበላ ሰው ጋር ወጣ ብሎ ይቆያል እንጅ እቤት አይቀመጥም፡፡ ጠዋት እንደተነሳ ከአማቱ ቤት ቁጭ ማለት የተከለከለ ነው፡፡ ለዚህም የሚያቀርቡት ምክንያት ወሬኛና ስራ የማይወድ ወንድ ወይም ሰነፍ ወንድ ሴት ምግብ ስታዘጋጅ አብሮ ይቀመጣል፡፡

ሴት ስታዘጋጅ አብሮ ቁጭ የሚልን ወንድ ማህበረሰቡ ‹‹ሴት አጫዋች›› የሚል ቅፅል ስም ያወጣለታል፡፡ የአማትን ገመና ምትሰራውን ምትጠቀመውን አያየ እንከን ይፈልጋል፡፡ ምትቀምሰውን ልቅመስ ምትሰራውን ልስራ ይላል፡፡ ይህ ደግሞ አማቱን ብቻ ሳይሆን ሚስቱ ምግብ ስታበሳስል አብሮ ቁጭ በማለት ጊዜውን በወሬ የሚያባክን፣ ስራ የማይወድና ልጆቹን ለርሀብ የሚያልጥ ወንድ መለያ ተደርጎይወሰዳል (ቃለ መጠይቅ፣ የመንግስት አካሉ፣ 30/05/2013)፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ የልጅ ባል የሴት አማት ምግብ ስታዘጋጅ አብሮ በመቀመጡ ተከሰተ ያሉትን በተረክ እንደሚከተለው ገልፀውልኛል፡፡

---

[4] ከላይ በተገለፀው ሀሳብ የልጅ ባል እና አማች እያልሁ ቀያይሬ የተጠቀምሁት በተጠኝው ማህበረሰብ እየቀያየሩ ስለሚጠቀሙበት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በቃለ መጠይቅ ወቅት ቀያይረው መጠቀማቸውን ስለተገነዘብሁ ነው፡፡ ሰላምታ ሲሰጣጡ ሲቀላለዱ ‹‹አማቼ›› የሚለውን ስም ይጠቀማሉ፡፡ ሰላምታ የሚሰጡት ሰው ጋር በጣም የሚግባቡ ከሆነ አማች ብለው የሚጠሩ ሰዎች አሉ፡፡ የአገባቻትን ልጅ ባሏን ቤተሰቡና ጎረቤቱ በስሙ ከመጥራት በተጨማሪ የልጅ ባላችን /የልጅ ባላችሁ በሚል አጠራር ይጠሩታል፡፡

አንድ የልጅ ባል ከምኝታው ተነስቶ አማት ከምታበስልበት ቦታ አብሮ ይቀመጣል። ከዚያም አያወሩ እያለ ከወጡ ቅቤ አርጋ እንጨት መለቃቀም ትሄዳለች። የልጅ ባልየው ምን ያንገበግባታል እንዲጥም ብዙ አታረግም ብሎ ከቅቤ ቅሉ እጁን ከቶ አወጣሁ እና ጨመርሁ ሲል እጁን ይዞ አለቀው ይላል። የዛን ግዜ አማቱ ድርስ አለች። አሱም ደንግጦ ምኽነኝ ይልቀቁኝ ብሎ ወጦ ሲገለገል በኩታው አዳፍኖት የነበረው ቅል ፅሀይ ሲነካው ከጁ ወርዶ ዱብ አለ። እሱም አይ ‹‹ቅልዎት ከያዘ አይለቅ እርስዎም ከለመኑ አይለቁ›› ብሎ አላት ይባላል (ቃለ መጠይቅ፣ የመንግስት አካሉ፣ 30/05/2013)።

ከዚህ ተረክ ላይ የምንረዳ ወንድ ልጅ ከሴት ልጅ ጋር አብሮ መቀመጥ ለተለያዩ ስህተቶች ይጋለጣል ብለው እንደሚያሰቡ ነው። ከዚህም በተጨማሪ የልጅ ባል ቢመቸውም ባይመቸውም አማት ያቀረበችለትን መብላት እንጅ እንደተሳሳተች መቁጠር፣አሰራሯ ልክ እንዳልሆነ መቁጠርና በድርጊት ማሳየት የተከለከለ መሆኑን እንረዳለን። ምክንያቱም በማህበረሰቡ አማት ለልጅ ባሏ ቤቷ ያፈራውን በጥንቃቄና በአክብሮት ታስተናግዳለች። ያላቀረበችው ስለተቸገረች ሊሆን ይችላል።

### 5.3.2. ሚስት ባሏን እንዳከበረች የሚያሳዩ ነውሮች

ሚስትን የተመለከቱ ነውሮች ከጋብቻ በኋላ ከትዳር አጋሯ ጋር በምታሳልፏቸው ጊዜያት ለባሏ ያላትን እንክብካቤና ለስራ ያላትን ትኩረት መሰረት ያደረጉ ናቸው። በማህበረሰቡ መልካም ሚስት ከምትገለፅባቸው ስነ ምግባሮች ባል እርሻ ውሎ ሲመጣ ተገቢውን እንክብካቤ ማድረግ የምትችል፣ በሰፈር እየዞረች ወሬ ማታበዛ፣ ከሌላ ወንድ ጋር ቀልድና ጨዋታ የማታበዛ፣ በስራና ልጅ በማሳደግ ትጉ የሆነች፣ በሙያዋ ብቁ የሆነች፣ ባል ያመረተውን እህል በአግባቡ መጠቀም፤ ከጎረቤት ጋር ባላት ግንኙነት አሉቧልታ አለማምጣት የታታሪ ሴት መገለጫ ነው።ሚስትን ባሏን እንዳከበረቻው የሚያሳዩ ነውሮች የሚስትን ስንፍናና መጥፎ ስነ ምግባር በመተቸት መልካም ስነ ምግባርን የሚያፀድቁ ናቸው። ሚስት ማክበር ከሚገባት ነውሮች ውስጥ ባሏን እንደናቀችው ከሚያሳዩ ድርጊቶች መቆጠብ (ከባሏ ጋር የተጣላች ሴት ባሏ እያለ ከቤት ወጥታ ወደ ቤተሰቦቿ ቤት መሄድና ሚስት ከባሏ ቀድማ መንዝ)፣ ስራ ውሎ ሲመጣ ተገቢውን እንክብካቤ ማድረግን የተመለከቱ ነውሮች ናቸው፡

በማህበረሰቡ ሚስት ባሏን እንደናቀችው የሚያሳዩ ድርጊቶች መተግበርና መጣስ በባልና ሚስቱ መካከል ግጭትን የሚያጭሩ ነውሮች ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሚስት ባሏን ያላከበረች ሴት መሆኗን ስለሚያመላክቱ የሚስትን መጥፎ ስነ ምግባር ገላጮች ናቸው፡

ከባሏ ጋር የተጣላች ሴት ባሏ እያለ ከቤት ወጥታ ወደ ቤተሰቦቿ ቤት መሄድ ሚስት ባሏን እንደናቀችውና እንዳላከበረችው ከሚያሳዩ ድርጊቶች ውስጥ ተጠቃሽ ነው፡፡ ምክንያቱም ባሏን ብትፈራው ኖሮ  እያለ አትሄድም ነበር፡፡ አቁማው ሄደች እያሉ የሚሳለቁ ብዙዎች ናቸው፡፡ በዚህም ባል በሚስቱ እንደተሸነፈ እና በጓደኞቹፊት ወንድነት የሚባለውን ስያሜን እንደተነጠቀ ይቆጥራል፡፡ በመሆኑም የባሏን የበላይነት አምና የተቀበለች ሴት በተለያዩ ችግሮች ባልና ሚስቱ ቢጣሉና ባል ሚስትን ቢደበድባት፣ ሚስት ከቤቷ ወጥታ ከቤተሰቦቿ ለመሄድ ካሰበች ባል በሌለበት ሰዓትና ለስራ ሲወጣ ጠብቃ መሆን አለበት፡፡ባሏን እቤት ውስጥ እያለ  እሄዳለሁ ማለት የተከለከለ ነው፡፡ ምክንያቱም ባል በንዴት ይመታታል፡፡ አሱ በአካባቢው አለመኖሩን ጭምር ማረጋገጥ አለባት፡፡ በአጋጣሚ ወጥታ ስትሄድ ቢያያትበመንገድ እሩጦ አቋርጦ ደብድቦ ያስመልሳታል፡፡ ይህን የሚያደርገው እንደናቀችው ስለሚቆጥርና መረጃው ከቤተሰቦቿ ከደረሰ በመሀል ጣልቃ ገብተው ያጣሉናል በሚል ፍራቻ ነው፡፡

> *ሚስት ባሏን አቁማው ከሄደች ነይ እንጅ ወደ ቤትሽ ይቅርታ ብሎ ከእናቷ ቤት መለመን አይሄድም፡፡ መጀመሪያ እኔን አቁማኝ የሄደች ጠግባ ነው ብሎ ዝም ይላል፡፡ ባሏም አቁማኝ ሄደች በሚል ንዴት ይቅርታ አድርጊልኝ ለማለት ከቤታቸው ሲቀር የሚስት ቤተሰቦች የልጃችን ንብረት ስጠን ብለው ይሄዳሉ፡፡ የሚስት ቤተሰብም ለምኖ መውሰድ ሲገባው ለግልብጥ ኑ ውሰዱ አለን፤ ልጃችን ጠልቷት አይደል መጦ ማይለምን ብለው ጠቡን ያባብሱታል፡፡*
>
> *አማቱ ልጁን ወደ ባሏ ይዞ ካልፈለግሀት ሀብቷን ስጣት ይላል ጠቡ ከሮ እስከመፋታት ሊያደርሳቸው ይችላል (ቃለ መጠይቅ፣ አገውላንች መንግስቱ፣ 07/06/2013)፡፡*

ነውሩን ማክበር ባልና ሚስት ተረጋግተው እንዲወስኑ ወይም ንዴታቸው ሲያልፍ ወደ እርቅ እንዲገቡ ለማድረግ የሚጠቅም ነውር ነው፡፡ ሚስት ለሰራ እስኪሄድ በምትጠብቀው ባሉት ሰዓታት ውስጥ ከንዴትና ከጭንቀት ወጥታ ተረጋግታ ልታስብና በይቅርታ ሊተላለፉ ይችላሉ፡፡ ለምን አቁማኝ ትሄዳለች? በሚል የባል ንዴት ከሚመጣ የጠብ መባባስ በመቆጣጠር

ከፋተኛ እንደሆነ የሚያስብበትን ጊዜ እና ባሉት ሰዎች ፊት ይቅርታ የሚጠይቅበትን ጊዜ እንዲኖረው በማድርግከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ አለው፡፡

ሌላው ሚስት ባሏን እንዳከበረችው ከሚያሳዩ ነውሮች ውስጥ ባልን ከፊት እንዲጓዝ ቅድሚያ መስጠት ነው፡፡ ሚስት ባሏን ቀድማ መጓዝ እንደናቀቻው ማሳያ ተደርጎ ይታሰበል፡፡በተጠኘው ማህበረሰብ ባልና ሚስት የራሳቸው የአጓጓዝ ስርዓት አላቸው፡፡ ባልና ሚስት በጣም ሳይራራቁም በጣም ደግሞ ሳይቀራረቡ ባል ከፊት ሆኖ መሄድ አለባቸው፡፡ ይህ የአጓጓዝ ስርዓታቸው ባልና ሚስቱን ከሚያደርሱባቸው የተለያዩ ግጭቶችና አደጋዎች ይከላከላል ተብሎ ይታሰባል፡፡

ለነውሩ ሶስት ምክንያቶችን ያቀርባሉ፡፡ የመጀመሪያው ባል ውሻ ሲመጣ ለመከላከል ደፋር ነው፡፡ የሚሻገሩት ውሃ ቢኖር ውሃውንም መሬቱንም እየመረመረ ያሻግራታል፡፡ ሲሄድ ከፊት የሚመጣ ሰው ወይም አውሬ ቢኖር እንዳትፈራ ይነግራታል፡፡ በድፍረት ወንድ ልጅ ይበልጣል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ ሁለተኛው ሚስት ከፊት ከሄደች ባሏ ሚስቱን ማዘዝ አይችልም፤እሷም ቅድሚያ የማትሰጠው ባለማክበር ነው፡፡

ስለዚህም እሱ የቤቱ መሪ እንደሆነና እሷም ለእሱ ቅድሚያ የምትሰጥ መሆኗን ማሳያ ነው (ቃለ መጠይቅ፣ አገውላንቺ መንግስቴ፣ 07/06/2013)፡፡ ሶስተኛው ምክንያት ባል ሚስትን ጠይቆ እንዳገባት ማሳያ ተምሳሌት ነው፡፡

> ሚስት ከፊት አትሄድም፡፡ እሱ ቤተሰቦቿን ለምኖ እሷንም ወዶ አገባት እንጅ እሷ አለመነችውም ጠይቃም አታገባውም፡፡ አጭተኛ ተልኮና ቤተሰቧን አስጠይቆ አገባት እንጅ የሴት ቤተሰቦች ከወንድ ቤተሰቦች ሂደው ጠይቀው አይጋቡም፡፡ ለዚህም ወንድ ከፊት ሴት ከኋላ ትሄዳለች፡፡ ጠይቄ አገባኋት ከእሷዋ በፊት እኔ ከቤተሰበቿ በመሄድ ልጃቸውን እንዲሰጡኝ ቀድሜ ጠየቅኋት በማለት ወንድ ከፊት ይሄዳል (ቃለ መጠይቅ፣ድሉ ተፈራ፣06/06/2013)፡፡

በእነዚህ ምክንያቶች ባልና ሚስት በጣም ከተዋደዱ ጎን ለጎን ወይም በጣም ሳይራራቁና ሳይቀራረቡ ወንድ ከፊት ሆኖ ይሄዳሉ፡፡ ይህንን ነውር ቄስ ገበየሁ ተበጀን ቃለ መጠይቅ አድርጌ ወደ ውፍታ ዳጢ ቀበሌ ስመለስ ባገኘሁት አጋጣሚ ምልከታ አድርጊያለሁ፡፡



**ፎቶ ሶስት፡-** ወጣት አንዱ ዓለም የጊላ ከሚስቱ ጋር ከስማቸው በላይ ቤት በቀን 12/06/2013 ሚካኤል ማህበር ሲሄዱ የሚያሳይና የባልና ሚስቱን አንንዝ ስርዓት የሚያሳይ ፎቶ

የሚስትን ስንፍና ከሚገልፁና ለግጭት ከሚዳርጉ ነውሮች ውስጥ የሚስት ዟሪና ወረኛ መሆን ተጠቃሽ ነው፡፡ ትዳሯን የምታከብር ሴት ባሏ ከተለያየ ቦታ ውሎ እስኪመጣ የቤተሰብ ሃላፊነቷን በስርዓት የምትወጣ እንጅ በሰፈር በመዞር የሰማቸውን ሁሉ ለባለቤቷ መናገርና ስራ ፈታ መዋል የሚደገፍ ተግባር አይደለም፡፡

> ‹‹ዟሪና ነገረኛን ሴት ሳታቃጥል በቅጠል ነው›› (ቃለ መጠይቅ፣ ይመኑ መኮነን፣ 15/06/2013)

ከጋብቻ በኂላ ሴት ልጅ ባለቤቷ ከስራ ሲመለስ ልጆችን ለስራ አሰማርታ እሷም ቤት ያፈራውን እራት ወይም ምሳ አዘጋጅታ ቤት መቆየት አለባት፡፡ ይህን ሳታደርግ ስትዞር በሰፈር ወሬ እያወራች የምትውል ከሆነ በባልና ሚስቱ መካከል ግጭት ይፈጠራል፡፡ ይህ ተግባር ነውር የሆነበት ምክንያት ሴት ነገረኛና የአንዱን ሰምታ ከአንዱ የማድረግ ባህሪ አላት ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ ስለዚህም ባሏንና አካባቢውን ታጣላለች፡፡ እሷም ከባሏ ጋር ስትዞሪ ስራ

ሳትሰሪ ዋልሽ በሚል ጠብ ይፈጠራል፡፡ እንደዚች አይነት ሴት አማቷንም አታከብርም፤ ጎረቤቶቿም አይወዷትም ተብሎ ይታሰባል (ቃለ መጠይቅ፣ ይመኑ መኮነን፣15/06/2013)፡፡

ይህ ነውር በአሉቧልታ ምክንያት የሚመጣ ጠብን በመከላከልና በባልና ሚስት እንዲሁም በአካባቢው መካከል አንድነትን ፈጥሮ በሰላም ለመኖር ይጠቅማል፡፡ ከላይ ወደ ተገለፀው ምሳሌያዊ አነጋገር ስናመራ ሴት ልጅ ዟሪ ከሆነች ቶሎ ፍታት፤ ሰፈሩንም ሆነ አንተን ትረብሻለች፡፡ ስለዚህም ፍሬ ሳታፈራ (ሳትወልድ ወይም ነገረኛ የሆኑ ሴቶችን ሳትተካ) ፍታት የሚል መልዕክት አለው፡፡ በዚህ አውድ ይህ ምሳያዊ አነጋገር ተግባሩ ለመቆጣጠርና ለመትከል ነው፡፡ ምክንያቱም ተጠኝው ማህበረሰብ ያለውን ግንኙነት አጠናክሮ ለመቀጠል ወይም አብሮ የመብላትና የመጠጣት ባህሉ ሳይሸራረፍ እንዲዘልቅ በመካከል ያሉ ክፉ ነገሮችን እና ጠብን የሚዘሩ ሰዎችን ማስወገድ፣ የሚስትን በመልካም ስነ ምግባር ለመቅረፅና ለማህበረሰቡ የአብሮነት ህልውና መጠበቅ ከፍተኛ ሚና ስላለው ነው፡፡

ሌላው ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚታየው የባሏን ክብር የምትጠብቅ ሴት የሚለብሳቸውን ልብሶች ማዘጋጀት ነው፡፡ በተለይም ባል ቢለብሳቸው በሌሎች ሰዎች እይታ እንደ ነውር የሚቆጠሩ አለባበሶች አሉ፡፡ ሚስት ለበሏ ቢያንስ አንድ ኩታ ልታሰራለት ይገባል፡፡ በተጠኝው ማህበረሰው ቢያንስ አንድ ኩታ(ጋቢ) የሌለው ወንድ የለም፡፡ አሁን አሁን ቀረ እንጅ ኩታው ከገበያ የተገዛ ከሆነ ሚስትን ያስወቅስ ነበር፡፡ በአሁኑ ሰዓት እየቀረ ነው የተባለው ኩታ መልበሱ ሳይሆን ሚስት ከቤት ፈትላ ከአካባቢው ለሚኖር የሽማ ሰሪ ማሰራቱን ነው፡፡ ለሚሰራው ጋቢ ጥጥ ተፈትላ እና ድር ገዝታ በባህላዊ ሽማኔዎች ታሰራለች፡፡ ይህን ያደረገች ሚሰት ታታሪና ባሏን አክባሪ እንደሆነች መገለጫ ነው፡፡

አማች ከሚስቱ ቤተሰቦች ተጠርቶ በሚሄድበት ወቅት በተባለው ቀንና ስዓት ኩታ (ጋቢ) ለብሶ ለሚስቱ ቤተሰቦች ያለውን አክብሮት በሚገልፅ መልኩ ይሄዳል፡፡ የስራ ልብሶቹን ለብሶ ከሄደ በአማቱ (በሚስቱ ቤተሰቦች) ቅሬታን ይፈጥራል፡፡ አማቻቸው አለባበሱን አስተካክሎ የሚሄድ ከሆነ ልጃቸውን ለእሱ በማጋባታቸው ደስተኛ ይሆናሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአካባቢው ማህበረሰብ የስራ ልብሶችን እንደ ፎጣ ያሉትን ለብሶ ከሄደ ሚስቱን ያስወቅሳል፡፡ መፍተል ስለማትችልና ሰነፍ ስለሆነች ባሏን ፎጣ አስለብሳ ወደ ቤተሰቦቿ ቤት ይዛው መጣች እያሉ የሚሳለቁ ብዘዎች ናቸው (ቃለ መጠይቅ፣ ድሉ ተፈራ፣06/06/2013)፡፡

ሚስትን ባሏን በማክበር ከምታከብራቸው ነውሮች ውስጥ ወደ ስራ ቦታ ሲሄድ ቡናን ሰዓቱን በጠበቀ መልኩ አፍልታና አስተናግዳ መሸኘት ነው፡፡ ሚስትበሰኔ ወር ከረፈደ ቡና ማፍላትና ባሏን ቆይቶ እንዲጠጣማድረግ የተከለከለ ተግባር ነው፡፡ በሰኔወር ታታሪ ሴቶች ከአስራ ሁለትሰዓት በፊት ተነስተው እስከ አንድ ሰዓት ድረስ ወጥ ሰርተው ቡና አፍልተው ባላቸውን ወደ ስራ ይሸኛሉ፡፡ መሄድ ካለባቸውም ከባላቸው ጋር አብረው ይሄዳሉ፡፡

አርፍዳ ተነስታ ቆይ ቡና ላፈላ ነው የምትል ሴት በማህበረሰቡ ሰነፍ ሴት ትባላለች፡፡ ከዚህ ላይ ቡና መጠጣት የስንፍና ምልክት ተደርጎ የተወሰደበት ምክንያት ቡናው የገባበት አውድ ነው፡፡ ቡና ፆም ከሆነ ከስራ በኋላ ይፈላል፡፡ ፍስክ ከሆነ ከስራ በፊት በጥዋት መጠጣት በማህበረሰቡ ልማድ ነው፡፡ በሰኔ ወር አውድ ቡና ማነቃቂያ ከሚል አገልግሎቱ ይልቅ‹‹የድካም ማሳለፊያ›› በሚል አገልግሎት ይታወቃል፡፡ ቡናን በዘር ወቅት ከረፈደ መጠጣት የተከለከለው ስራዎችን ያደናቅፋል፤ ሰዓት ይፈጃል፤ለምርት ውጤታማነት አደናቃፊ ነው በሚል እሳቤ ነው፡፡

> በሰኔ ከረፈደ ተነስታ ቡና ጠጡ ምትል ሴት ክፉ ናት፡፡ ቡናውን ከባሏ ጋር ስጠጣ አርፍዳ ይወጣና ፈሰስ ሳይቀደድ ወይም ዘሩ ሳያልቅ ዝናቡ ይመጣል፡፡ ጎርፉ የታረሰውን አፈር እና የተዘራውን ዘር ይወስደዋል፡፡ እሱም ቢሆን ቆይ እንጅ ጠጣ ስትለው መጠበቁ ሰነፍ ነው፡፡ ጎበዝ ገበሬዎች በሰኔ ሽንታቸውን ለመሽናት እንኳ ሰዓት የላቸውም (ቃለ መጠይቅ፣ ይመኑ መኮንን፣ቃለ መጠይቅ፣ 15/06/2013)፡፡

ይህ ነውር ቡና በሚል ሰበብ የስራ ሰዓትን መሸራረፍ አግባብነት የሌለው መሆኑን ያስረዳል፡፡ ቡና መቼና የት መጠጣት እንዳለበት በማሳወቅ በቡና ሰበብ የሚባክኑ ዓታትን ለመቆጠብና እግረ መንገዱን የጊዜ አጠቃቀሙን ለልጆቻቸው ለማስተማር ይጠቅማል፡፡

ሚስት ለባሏ ምግብ ቶሎ አለማቅረብ ሚስት ሰነፍ እንደሆነችና ለባሏ አክብሮት እንደሌላት የሚያመላክት ነውር ነው፡፡ የግብርና ስራ አድካሚ እንደመሆኑ መጠን ከጭቃው ወይም ከፀሐዩ ጋር አብሮ የዋለ ገበሬ ውሃ ጥም እና እራብ እንዳይጎዳው እንክብካቤ ያስፈልገዋል፡፡ ለዚህም ሴት ልጅ አብራ ስራ እስካልወጣች ድረስ ባል ስራ ቆይቶ ሲመጣ ምግብ ቶሎ ብላ ማቅረብ አለባት፡፡ በስንፍና ምክንያት ከመተሳሰብና ከእንክብካቤ ችግር የሚመጣ የባልና ሚስት መኮራረፍም ከበዛም ግጭት ማስነሳትን ሊፈጥር የሚችል ነውር ነው፡፡

ቤት ያፈራውን አዘጋጅታ ትቆየዋለች፡፡ ካለም ቡና ቆልታ ጠላ ጠምቃ ትቆየዋለች፡፡ ይህን የምታደርግም ታታሪና ለባሏ ታዛዥ ሴትናት፡፡ በገጠሩ ማህበረሰብ ለምን በእያይነት የተዘጋጀ ምግብ አልቀረበልኝም ወይም ቤቱ ተስተካክሎና አምሮ አልጠበቀኝም በሚል ሰበብ ግጭት አይነሳም፡፡ ግጭቱ ባል ስራ ውሎ ሲመጣ ቤት ያፈራውን እንደሚርበው ገምታና ተረድታ ቶሎ ባለማቅረብ ነው፡፡

ባል ሚስቱን ለምን ቶሎ ምግብአልቀረበልኝም ብሎ ብቻ አይጣላትም፡፡ እሱን እንዳላከበረችው ስራ ፈታ እንደዋለች በመቁጠር ነው፡፡ ከቻለች ለበሬዎች ሳር እና ገለባ አቅርባ የእግር ውሃ አሙቃ መቆየት አለባት (ቃለ መጠይቅ፣ ሙሉ አድማስ፣ 20/06/2013)፡፡

በተጠኘው ማህበረሰብ ሴት ልጅ ቤት ከዋለች ይርባታል ተብሎ አይታሰብም፡፡ ምክንያቱምምግብ ሰላታዘጋጅ ላበቱ ያጠግባታል፡፡ ወንድ ልጅ ከሴት ልጅ ይልቅ እርሀቡ ትኩስ ነው፡፡ ስለዚህም ከተለያየ ቦታ ሲመጣ ሚስት ቀልጠፍ ብላ ምግብ ማቅርብ አለባት የሚል እምነት አላቸው፡፡

### 5.3.3. ስንፍናና ጾታዊ ትንኮሰሳን የሚያወግዙና በባል የሚከበሩ ነውሮች

ተጠኘው ማህበረሰብ ድህረ ጋብቻ ላይ ያለን ፈት ወንድ (ሚስት ፈቶ የቆየ) እና በትዳር አጋር ያለው ወንድ ማክበር እንደሚገባው አምነው የተቀበሏቸው ነውሮች አሉ፡፡ በዚህ ስር የሚታዩ ነውሮች ሁለት ሲሆኑ የባልን ስንፍና ለማውገዝ እና ትዳር ላይ ያለ ወንድ በሌሎች ወንዶች ሚስቶች ላይ ፆታዊ ትንኮሳ እንዳያደርግ የሚከላከሉ ናቸው፡፡ ቢጣሱ ሚስት በስንፍናው ምክንያት እንድትንቀውና እንዳትፈታው ለማድረግ የሚያደርሱ እንዲሁም ከሌሎች ወንዶች ጋር ከፍተኛ የሆነ ግጭት ሊያስከትሉ የሚችሉ ናቸው፡፡

ባል በሚስት እንዲናቅ ከሚያደርጉና ሚስቱ ጥላው እንድትሄድ/እንድትፈታው ከሚያደርጉ ተግባራት ውስጥ ሚስት ፈቶ የቆየ ወንድ (ፈት ወንድ) ድጋሜ ሲያገባ ላመጣት አዲስ ሚስት ከጎታው በቂ እህል አለማቆየት ነው፡፡

ሚስት ፈቶ የቆየ ወንድ ላገባት አዲስ ሚስት ከጎታው በቂ እህል አለማቆየት የባልን ሰነፍ መሆን ከሚገልፁና ሚስቱን ባሏን በመናቅ ለመፋታት ከሚያደርሱ ነውሮች ውስጥ ተጠቃሽ ነው፡፡ ይህ ነውር በማህበረሰቡ አግብታ የኖረችን ሴት(ፈት ሴትን) በቤቱ ውስጥ ማስገባትን ወይም የጋለሞታ ጋብቻ በመባል የሚታወቀውን የሚመለከት ነው፡፡

ሚስት አግብታ የቆየች እና እሱም ቤት ይዞ አግብቶ የቆየ እንደመሆኑ መጠን ሚስቱን ሲያገባ በቤቱ ለአመት የሚሆን ቀለብ ማቅረብ የሚችል መሆን አለበት፡፡ ይህን ሳያደርግ ሚስቱን ቢያመጣ ሰነፍ ገበሬ መሆኑን ከመገምገም ባለፍ ሚስት ብዙ ሳትቆይ ጥላ ለመሄድ የሚያደርስ ነውር ነው፡፡ ምክንያቱም ሚስት ወዲያው እንደመጣች ማታውን ወይም በማግስቱ በቤቱ ያለውን እቃና በየጎታው ያለውን የእህል አይነት ማየት አለባት፡፡

ምንም እህል ከሌለ ወይም በየእህል አይነቶቹ የተወሰኑት እንኳ ከሌሉ ያገባችው ባል ሰነፍ ገበሬ እንደሆነ መለያዋ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የድሮ ሚስቱ ወይም የፈታት ሚስቱ ጥላው የሄደችው ምክንያት በስንፍናው ነው ብላ ታስባለች፡፡ ስለዚህም የተወሰነ ቀን በመቆየት አዲስ ከአገባችው ባል ቤት ወጥታ ወደ ነበረችበት ቦታ ትሄዳለች፡፡ ቤተሰቦቿ ያጋቧት ባል (አማቻቸው) የወደፊት ኑሮዋን አያሳምርም ብለው ስለሚያስቡ ያገባችውን ባል ጥላ እንድትመጣ ያበረታታሉ፡፡

> አግብታ የቆየችን ሴት ድጋሜ በሚያገባበት ጊዜ በቤቱ ሰርቶ ወይም ከተሰራ ቤት ስለሚወስዳት ቤቱን አዘጋጅቶ መቆየት አለበት፡፡ ከጎታውም እህል ሊያቆያት ይገባል፡፡ ከቤት ያለውን እህል ላመጧት አዲስ ሙሽራ ወዲያው የሚያሳዩም  የማያሳዩም አሉ፡፡ የመጣቻት አዲስ ሙሽራ ካላሳያት እሱ ሲወጣ አይታ ከንዳ ውስጥ ትገባና ጎታውን በአጇ መታ መታ ታደርገዋለች፡፡ ካለው ድምፁ ወፍራም ነው ከሌለው ድምፁ ቀጭን ነው፡፡ ካለበቀር ትልቅ እንጨት ታመጣና ወደ ጎታው ውስጥ ትሰደዋለች፡፡ ከዚያ ካለው እንጨቱ ከቅርብ ይቀራል፡፡ ከሌለው እሩቅ ይሄዳል፡፡ በዚህ መንገድ ለይታ ጎታው እህሉ በጣም አነስተኛ ከሆነ ወይም ከሌለው የብቸኝነት ኑሮየ ይሻላል፤ ከእኔ ካልተሸለሳ ምን ያደርግልኛል ብላ ጥላው ትሄዳለች (ቃለ መጠይቅ፣ ገነት ደሴ መርሻ፣ 29/05//2013)፡፡

ነውሩ ባልና ሚስት እንዳይፋቱ ቀድሞ የመቆጣጠርና ጋብቻቸው ዘላቂ እንዲሆን ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡፡ ቤተ ፈትነት፣ ሴተኛ አዳሪ፣ የተወለዱ ልጆች በእሱም በእሷም በኩል ካሉ የጎዳና ተዳዳሪ እንዳይሆኑ ለማድረግና ቀድሞ ለመቆጣጠር ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

ባል በሚስቱ እና ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለው መልካም ግንኙነት እንዲቀጥል ለትዳር አጋሩና ለሌሎች ወንዶች የትዳር አጋር የሆኑ ሴቶችን ማክበር ነው፡፡ የሰውን ሚስት ያታዊ ትንኮሳ ለማድረግ መሞከርና አተኩሮ ማየትየተከለከለ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ወንድ ልጅ ከአካባቢው

ማህበረሰብ ወግና ስርዓት ሲያፈነግጥና ከፆታዊ ትንኮሳዎች ጋር በተያያዙ ድርጊቶች ሲጠረጠር ከማህበረሰቡ አባላት ጋር ግጭት ይፈጠራል፡፡

አንድ ወንድ ትዳር ያላትን ሴት አተኩሮ ካያት እንደወደዳትና ለእሱ ማድረግ እንደፈለገ ይታመናል፡፡ ለመድፈር መሞከር ጸብን ከመጫር አልፎ መገዳደልን የሚያስከትል የነውር አይነት ነው፡፡ እነዚህ ነውሮች አብዛኛውን ጊዜ ሲጣሱ የማይስተዋሉ ናቸው፡፡ ሚስት አጋጣሚ ሆኖ በየሄደችበት የሚከታተላትን እና የሚያተኩርባት እንዲሁም ለመድፈር የሚሞክር ቢኖር እንኳ ወዲያውኑ ለባሏ አትናገርም፡፡ ቀኑ ከአለፈና ከተረሳ በኋላ ልትናገር ትችላለች፡፡

የማህበረሰቡ አባላት ወንዶች ከተለያዩ ቦታዎች ሲሄዱ፣ አማችም ከአማቱ ቤት እንግድነት በሄደበት ሰፈር እና ወይም ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ትዳር ያላትን ሴት ለፆታዊ ትንኮሳ አተኩሮ ማየት እና የሌላቸውንም ቢሆን ፆታዊ ትንኮሳ ማድረግ ትንኮሳው በደረሰባቸው ሴት ቤተሰቦች ከፍተኛ ግጭትን የሚቀሰቅስ ነው፡፡ ባልየው አጋጣሚ ሆኖ ሌላ ወንድ ሚስቱን ለመድፈር የሞከረ እንደሆነና በአይኑ እየተከታተላት (እያተኮረባት መሆኑን ካየ) ወይም ከሰማ ከዚያ ሰው ጋር ግጭት ይፈጠራል፡፡ ጉዳዩ በአጭር ጊዜ በሽምግልና ካልተፈታ የሁለቱ ጠብ ከሮ እስከ መገዳደል ይደርሳሉ፡፡ ይህንን ነውር በተመለከተ ከወይዘሮ የመንግስት አካሉ ጋር በቀን 30/05/2013/ ባደረግሁት ቃለ መጠይቅ በቅርብ ጊዜ ተከሰተ ያሉትን ተረክ እንደሚከተለው ገልፀውልኛል፡፡

> እዚህ እኛ አባድራው ድልድይ ላይ ካለው ባህር ዛፍ አጠገብ አባድራ ያለች ሴትን ግራርጌ ያለ ሰውየ አግኝቶ የማነሽ ብሎ አቁሞ ሲያናግራት ቆየ፡፡ ከዚያ ሊይዛት ሲል ተው ባክህ የወንድ ምሽት ነኝ ስትለው ለማምለጥ ብለሽ እንጅ አይደለሽም አላት፡፡ አንገቷን አንቆ ሊደፍራት እያለ ባለባጃጅ አይቶ አስጣላት፡፡ ባሏም ግራርጌ ቀበሌ ሂዶ ምሽቴን ሊደፍራት ሲል ባለባጃጅ አስቀረልኝ ብሎ ሲናገር ቀበሌው ሰውየውን አቅርቦ ከህዝብ መኃል አስቁሞ ባንቱ እሰከሚቀር ሱሪውን አስወልቆ አሳፈረው፡፡ ሰውየውም ቀበሌውንም የሴትይቱን ባልም ይቅርታ አለ፡፡ እንደዚህ አይነት ህግ ስላለ ሚተናኮልብዙም የለም፡፡ ለቀበሌ ሳይናገሩ ሚደባደቡም አሉ፡፡ እንዲያውም አብዛኞቹ መናገርን እንደ ውርደት ስለሚቆጥሩት አይናገሩም፡፡

ከዚህ ተረክ ላይ ሁለት ዋና ዋና ነገሮችን እንረዳለን፡፡ አንደኛው ነውሩ ያመጣውን ጦስ እና ነውሩን በነውር የመቅጣት ህግ በተጠኘው ቦታ እንዳለ ነው፡፡

በተረኩ እንደተገለፀው የሴቶችን የፆታዊ ጥቃትን ለመፈፀም የሚሞክር ወንድ መቀጮው እስር ቤት ገብቶ መታሰር ብቻ አይደለም፡፡ ወደህግ ከመሄዳቸው በፊት በሽምግልና ወይም በባህላዉ ፍርድ የሚያስቀምጠው የሞራል ቅጣት ነው፡፡ ድርጊቱን ሁለተኛ ጊዜ እንዳይፈፅም በጓደኞቹም በቀበሌዎች ሴትም አሳውቆ ነውር የሆነውን ከሰው ፊት ሱሪ ማውለቅ አስወልቆ ሰውየውን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መቅጣት ነው፡፡ ነውሩን በነውር መቅጣት ለምን አስፈለገ የሚለውን ስንመለከት የሰው ልጅ በየአደገበት ማህበረሰብ ያለውን ነውር ሲሰራ ይሸማቀቃል፡፡ ለስህተቱ ማረሚያ ሆኖት ከነበረው መጥፎ ስነ ምግባሩ ይመለሳል፡፡ ስለዚህም ይህ ነውር ሰውየውን አሸማቆ ድርጊቱን ሁለተኛ ጊዜ እንዳይፈፀም በጓደኞቹ ፊት ማውገዝ ነው፡፡

### 5.3.4. የከብት እና የሰው በሽታን እንዳያመጡ የሚያከብሯቸው ነውሮች

በዚህ ስር የሚጠቃለሉ ነውሮች በቤተሰቡ አባላትና በእንስሳቶቻቸውላይ የተለያዩ የጤና ችግሮችን የሚያስከትሉ ናቸው፡፡ በአንድ የቤተሰብ አባላት ውስጥ በቤተሰብ ደረጃ የሚያምኑበት እምነት ይኖራል፡፡

በቤተሰብ ደረጃ የሚያምኑትን እምነትም በሚከበርበት ወቅትና ቀን ጠብቀው ካላከበሩ ወይም ለእምነቱ የሚያቀርቡት ቁስ ካልተጠቀሙ በቤተሰቡ አባላትና በእንስሳቶች ላይ የተለያዩ በሽታዎች ይከሰታሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡ በተጠኘው ማህበረሰብ እንስሳቶቻቸው ለተለያዩ በሽታዎች እንዳይጋለጡና የመጣው በሽታ በከብቶች ጸንቶ እንዳይቆይ የሚፈፅሟቸው ሀገረሰባዊ እምነቶች አሉ፡፡ በአጠቃላይ በዚህ አቢይ ርዕስ ስር የማዝ በሽታን ለመከላከል ሚጠቅሙ ነውሮች፣ የቤታቤት እምነት ሲከበር የሚጠነቀቋቸው ነውሮች፣ ለክፉ አጋጣሚ ይዳርጋሉ በሚል የሚፈሯቸው ነውሮች በመባል ተከፋፍለው ቀርበዋል፡፡ እነዚህን ነውሮች ማህበረሰቡ ለመጣስ የሚፈራቸውና ወቅታቸውን ጠብቆ የሚያከብራቸው ናቸው፡፡

### 5.3.4.1. የማዝ በሽታን ለመሸኘትና ለመከላከል የሚጠቅሙ ነውሮች

የተመረጡት ተጠኝ ማህበረሰቦች ከሚተዳደሩባቸው የኢኮኖሚ ዘርፎች መካከል እንስሳት እርባታ ተጠቃሽ ነው። የእንስሳቶቻቸውን ደህንነት ለመጠበቅ የተለያዩ ዘመናዊ የህክምና አይነቶችን ይጠቀማሉ። ነገር ግን ዘመናዊ ህክምና አያድነውም ብለው የሚያስቡትን የህመም አይነት የተለያዩ እምነታዊ የሆኑ ድርጊቶችን በመፈፀም የከብቶቻቸውን ጤንነት ይጠብቃሉ።በተጠኝው ማህበረሰብ ዘመናዊ ህክምና አያድነውም ተብሎ የሚታሰበው የከብትበሽታ አይነት የማዝ በሽታ ነው።

የማዝ በሽታን ማህበረሰቡ በሌላ አጠራር የከብት ዛር በማለት ይጠራዋል። ይህ በሽታ የከብቶችን እግርና ሰኮና በማቁሰል፣ ፀጉራቸውን በማቆምና ወገባቸውን በመሰባበር ለሞት የሚዳርግ ነው። በሽታው ከክፉ መንፈስ የተላከ ነው ተብሎ ይታሰባል።የማዝ በሽታ የሚይዛቸው ከብቶችበመልክም በአካል መጠንም ደህናውን መርጦ ነው። በመሆኑም ማህበረሰቡ ይህንን በሽታ በሚመጣበት ወር ሁሉ ሀገረሰባዊ እምነቶችን በመከወንያከብረዋል። የማዝ በሽታ በአካባቢው በሚከሰትበት ወቅት በሽታው ተመልሶ እንዳይመጣ የራሱ የአከባበር ስርዓት አለው። የማዝ በሽታ ከበራ ዋና አላማ በሽታውን ለመሸኘት ነው።

በሽታውን ለመሸኘት ቅዳሜ፣ ሰኞ እና ሀሙስ ተመራጭ ቀናት ናቸው። እነዚህ ቀናት ውጭ በሽታውን መሸኘት የተከለከለ ነው።[5] ለዚህም የሚያቀርቡት ምክንያት የገበያ መንገድ ሰው ስለሚበዛበት በሽታው አካባቢውን ለቆ ከሰው ጋር ተከትሎ እንዲሄድ በማሰብ ነው። ቀናቶቹ ተመራጭ የሆኑት የተለየ ትርጉም ኑሯቸው ሳይሆን የገበያ ቀን ስለሆኑ ነው። በሽታው ሲሸኝ ከፊት ጅራፍ እየገረፈ የሚሄድ ልጅ አለ።ጅራፍ እየገረፈ የሚሮጠውን ልጅ የሚከተል ሌላ ልጅ

---

[5] የማዝ በሽታ ለመሸኘት የራሱ የሆነ ክዋኔ አለው። የማዝ በሽታን ለመሸኘት በአራት ማዕዘን (መስቀልያ) የገበያ መንገድ ላይ ገንፎ፣ ንፍሮ፣ ቡናና አረቄ ተደርጎ በማዘጋጀት ይከበራል። ከንፍሮው የተወሰነውን በመዝገን በአራቱም ማዕዘን እየተወረወረ ይጣላል። ገንፎው በእርጥብ ብሳና እንጨት የሚደረግ ነው። በእርጥብ ብሳና መሆኑ ከብቶች እንዲረቡ ተብሎ ስለሚታሰብ ነው። የማዝ በሽታ በሚ በሽታበሚከበርበት ጊዜ ከብቶች በከበራው ቦታ አጠገብ መሆን አለባቸው። መረጃው ከገነት ደሴ መርሻ በቀን 28/05/2013 በቃለ መጠይቅ ወቅት የተገኘና ሌሎቹም ጭምር የተጋሩት ሀሳብ ነው።

አለ፡፡ የሚከተለው ልጅም ‹‹ማዝ አልፊህ ያዝ እያለ›› ይሮጣል፡፡ በዚህ ሁኔታ ልጆች የተወሰነ እርቀት ይሄዳሉ፡፡ የሚሮጡት ልጆች ዙረው አያዩም (ቃለ መጠይቅ፣ ገነት ደሴ መርሻ፣ 29/05/2013)፡፡

ልጆች ጅራፍ እየገረፉ ፊትና ኋላ ሆነው የሚሮጡት በሽታው ደንግጦ በፍጥነት አካባቢውን እንዲለቅ በማሰብ ነው፡፡ ልጆች ዙረው እንዳያዩ መከልከላቸው በሽታ ተመልሶ መጥቶ ከብቶችን እንዳይዛቸው ነው፡፡ በመሆኑም የማዝ በሽታ አከባበር ክዋኔዎች አግባብነት ከሌላቸው የያዛቸው በሽታ ከቦታው ለረጅም ጊዜ በመቆየት የእንስሳትን ሞት ያስከትላል ተብሎ ይታሰባል፡፡

### 5.3.4.2. የቤታቤት እምነት ሲከበር የሚጠነቀቋቸው ነውሮች

በቤተሰቦቻቸውና በእንስሳቶቻቸው ላይ የጤና ችግርን ያደርሳሉ ከሚባሉ ነውሮች ውስጥ የቤታቤት እምነት ተጠቃሽ ነው፡፡ የቤታቤት በማህበረሰቡ በቤተሰብ ደረጃ የምትከበር እምነት ናት፡፡ የምትከበርበት ቀን ሰኞ፣ ማክሰኞ እና ሀሙስ ነው፡፡ እምቷን ለማክብር ከወራት ውስጥ ህዳርና ግንቦት ተመራጭ ወራት ናቸው፡፡

ከማክሰኞ ከሰኞ እና ከሀሙስ ቀን ውጭ የቤታቤት እምነትን ማክበር የቤተሰቡን አባል ሆድ በመንፋት፣ በመቁረጥ እና ሰውነቱን በማሳበጥ ትገላለች፡፡[6]የቤታቤት እምነትን ለማክበር ከወራት ግንቦት ተመራጭ የሆነበት ምክንያት በልግ ወቅት በመሆኑ ላሞች እንዲረቡ በሚል እሳቤ ሲሆን ህዳር ተመራጭ የሆነበት ምክንያት ደግሞ በማህበረሰቡ የተዘራው እህል የሚሰበሰብበት ስለሆነ የገባውን ሰብል እንዲባረክ በሚል እምነት ነው፡፡

---

[6]የቤታ ቤት እምነት አመጣጧ ከቅድመ አያቶች እቃዋ በፈረስ ተጭኖ ከሌላ ቦታ ወደ ተጠኘው ቦታ እንደገባች ይነገራል፡፡ እምነቷ የራሷ የሆነ ክብት ይቋቋምላታል፡፡ በእሳት ያልተተኮሱ እቃዎች ይዘጋጁላታል፤ እቃዎቿ አይታጠኑም፡፡ የከብቶቿን ወተት ባዳ አይጠጣውም፡፡ ቅቤዋም ገበያ አይሸጥም፡፡ የእቃዎቿ የራሷ ማስቀመጫ ጓዳ አላት፡፡ በዓሏ ሲከበር በአካባቢው ዘመድ ያልሆነ አይገባም፡፡ የማይገባበት ምክንያት የቤታቤቷ ችግር ታደርስበታለች በሚል ፍራቻ ነው፡፡ በዓሏን የሚያከብሩ የቤተሰብ አባላት የጤፍ ዱቄት ቡና ወይም ብር ይዘው መምጣት አለባቸው፡፡ ይዘው ባይመጡ አመቱን ጠብቃ ትገላቸዋለች ተብሎ ይታሰባል፡፡ በመጨረሻም በዓሏ ተከብሮ ሲያበቃ የቤቱ ጥራጊ ባህር ላይ ይጣላል፡፡ የቤታቤት እምነትን ሲያከብር የነበረ ሰው ማክበሩን ቢተው የእምነቷን ላምና እምነቷን ለማክበር የሚጠቀምበትን ቁሳቁሶች ከቤቱ ማስቀመጥ የለበትም፡፡ የእሷን ክብቶች ሽጦን ለሶስት ቤተክርስትያን ከፋፍሎ ገንዘቡን ያስገባል፡፡ እቃዎችን አውጥቶ ይጥላል፡፡ መረጃው ከአቶ ገነት ደሴ መርሻ፣ ከአቶ አዲሱ አረጋ እና ከወ/ሮ የመንግስት አካሉ የተሰበሰበና ተጨምቆ የተወሰደ ነው፡፡

ይህች እምነት የራሷ የሆነ ላም፣እና የቤት እቃዎች አሏት፡፡ ላሟ የቤታቤት ተብላ ለምትጠራት እምነት የተሰጠች ስለሆነች ከቤተሰቡ ያሉትን ላሞች እንዲረቡ ታደርጋለች ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ እምነቷን በአሁኑ ሰዓት በመጥፋት ላይ ያለች ናት፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት በሃይማኖት በአባቶች የባዕድ አምልኮ ናት ተብሎ ስለታሰበ ነው (ቃለ መጠይቅ፣ አዲሱ አረጋ፣ 04/06/2013)፡፡

ሰዎች ድህነትን እና ጤና ማጣትን አጥብቀው ይፈራሉ፡፡ የድህነትና የጤና ማጣታቸው መንስኤ ይሆናል ብለው የሚያስቡትም ባህሉ ያፈራውን ህሊናቸው ያመነበትን ድርጊት አለመከወን ነው ብለው ያምናሉ፡፡ በመሆኑም ሀብት ለማግኘት ሲሉ ሚጨርሱት ብዙ ጊዜ ለመቀነስና የጤና ማጣት ችግር እንዳይከሰትየቤታ ቤት እምነት ወሳኝ መሆኑን አምነው በቀኑ እና በወሩ ጠብቀው ያከብራሉ፡፡በመሆኑም የቤታቤትን እምነትን ቀን ጠብቆ ማክበር ይደርስብኛል፤ ብለው ከሚፈሩት በሽታና የሀብት ማጣት የሚመጣ ጭንቀትን ለመከላከል ተጠቅመውበታል፡፡

### 5.3.4.3.ለክፉ አጋጣሚ ይዳርጋሉ በሚል የሚፈሯቸው ነውሮች

በጥናቱ የተመረጠው ተጠኝ ማህበረሰብ እንቅስቃሴውና የስራ ሁኔታው ቀናትን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ለክፉ አጋጣሚ ይዳርጋሉ ተብለው የሚታሰቡትን ቀናት ብንጥሳቸው የእብድ ውሻ ልክፍት ይገለናል፣ እባብ ያስፈራራናል፣በመንገድ አደጋ ያገኘናል፣ ከሰው ጋር እንጣላለንበሚል ፍራቻ የሚያከብሯቸው ውስጠ እምነቶች ናቸው፡፡ ሰዎች ከጋብቻ በኋላ ልጅ ሲያሳድጉ ማህበራዊ ግንኙነት ሲጀምሩ የተለያዩ ክፉ ገጠመኞችን ሊያሳልፉ ይችላሉ፡፡ክፉ አጋጣሚያመጣል በሚሉት ቀን እንዳስፈላጊነቱ ጊዜያቸውን በተለያዩ ተግባራት ያሳልፋሉ፡፡ለክፉ አጋጣሚ ይዳርጋሉ ተብለው የሚታሰቡ ቀናትን አለማክብር በቤተሰብ አባላትና በእንስሳቶቻቸው ላይ ክፍተኛ ችግር የሚያደርሱ ናቸው፡፡

ለክፉ አጋጣሚ ይዳርጋሉ ተብለው ከሚታሰቡ ቀናት ውስጥ እሮብ ቀንና የወር መጀመሪያ ቀን መንገድ መውጣት ተጠቃሽ ነው፡፡ ማህበረሰቡ ገበያ ለመውጣት ቀኖችን ይመርጣል፡፡ ከተለየዩ ቦታዎች ደርሰው ሲመለሱ ችግር እንዳያገኛቸው ቀናትን ይመርጣሉ፡፡ የመረጣቸውን ቀኖች ጠብቆ የሚፈልገውን ለመግዛት ይንቀሳቀሳል፡፡ እሮብ ቀንና ወሩ በገባ በአንድ ቀን መንገድ መውጣት ችግር ያጋጥመናል፣ አይቀናንም የሚል እሳቤ አለቸው፡፡

አሮብ ቀን ለንግድ እንቅስቃሴ ወደ ገበያ መሄድበጫከው ሽፍታ ተደብቆ ገንዘባችንን ይቀማል፤እኛንም ይደበድበናል፤ በንግዱ ውጤታማ አንሆንም የሚል እምነት አላቸው (ቃለ መጠይቅ፣ ምናለ ጣሹ፣ 11/06/2013)፡፡

ወሩ በገባ በአንድ ቀን በማህበረሰቡ የመባቻ ቀን ተብሎ ይጠራል፡፡ በዚህ ቀን እሩቅ ቦታ እና ብዙ ኪሎ ሜትር አቋርጦ መሄድ የተለያዩ ችግሮችን ያስከትላል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በመሆኑም ይህ ነውር ማህበረሰቡ ይደርስብኛል ካለው የተለያየ አደጋ ለመከላከል ያገለገለ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሰው ልጅ ከወራት ውስጥ የሚያርፍበትን ቀን ይፈልጋል፡፡ ቡናውን አፍልቶ ጠላውን በጥብጦ ከልጆቹ ጋር ማሳለፍና ቤቱን ለማቃናት በበዓለት የተሸራረፈውን ጊዜ ማካካስ ይፈልጋል፡፡ በመባቻ ቀን አጨዳ፣ እርሻ፣ ጉልጓሎ በራይ እና ሌሎቹንም ስራዎች ይሰራል፡፡ ነገር ግን በመባቻ ጠብ ማንሳትና መደባደብ እና መንገድ መውጣት የሚደገፍ ተግባር አይደለም፡፡

> እኔ በመባቻ ቀን ሲሆን ቡናየን አፍልቼ ጮሌ (ሳር) ነስንሼ ቤቴ ነው ምውል፡፡ በጣም ችግር ካልሆነ መንገድ አልወጣም፡፡ የቅርብ ዘመድ ካልሆነ እልቅሶም ቢሄድ ደስ አይለኝም፡፡ ከልጆቸ ጋር ስንበላ ስንጠጣ በሰላም እና በደስታ በፍቅር መባቻን ካሳለፍነ ወሩን ሁሉ በደስታና በፍቅር እናሳልፈዋለን፡፡ የመባቻ ቀን መንገድ ከወጣን ወይም ከሰው ጋር ከተጣላን የሚመጣው ወርም አይባረክም፡፡ በእኔ ባይደርስ እንኳ በልጆቸ ወይም በከብቶቼ እክል አያጣኝም (ቃለ መጠይቅ፣ ሙሉ አድማስ፣ 19/06/2013)፡፡

በመሆኑም ማህበረሰቡ ወሩ በገባ አንድ ቀን ከላይ ከተገለፁት ተግባራት መቆጠቡ ራሳቸውን ከአደጋ ለመከላከልና የእርስ በእርስ ግጭትን ለመቀነስ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ ይህ ነውር ከጠብና ሰውን ከመረበሽ ይልቅ በፍቅርና በስራ የሚገኘውን በረከት ለማስተማር የሚጠቅም ነው፡፡

ወሩ በገባ በ10ኛው ቀን ስራ መስራትና የቤት እቃዎችን አውጥቶ ለሰው መስጠት ለክፉ አጋጣሚ ከሚደርጉ ቀናት ውስጥ ተጠቃሽ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ይህንን ቀን የሚያከብሩ ሰዎች አብዛኛዎቹ የቤታቤት እምነትን ከቤታቸው አስገብተው ሲያከብሩ የነበሩ ነገር ግን አሁን ላይ እቃዋን አውጥተው የጣሉ ናቸው፡፡

እነዚህ ሰዎች ይህንን ቀን ብንሽር በቤታቤት እምነት ወጦ መውደቅ ምክንያት በሚመጣ ቁጣ በሽታው ተመልሶ ይይዘናል እምነቷም ቁጣዋን አትተውም በሚል ፍራቻ ነው። ሌሎቹ በዚህ ቀን ተጠምቀው የዳኑ እና በጸበል በእምነቱ የተፈወሱ ሰዎች ያከብሩታል። አንዳንዱ በቀኗ የቤት እቃዎችን አውጥተን አንሰጥም፣ከብትና የጋሬ እቃ አውጥተን አንሰጥም። ከሰጠነ ተለምኖ የሄደው እቃ በሰላም አይመለስም፤ ጋሪ የሚሰራው በቅሎና የሚያርሰው በሬ ይታመማል። በዓሉን ለማክበር የተሳሉት ስለት በመርሳት በዓሉን ቢሽሩ ጉንዳን ቤታችንን ይወርሳል ብለው ያስባሉ (ቃለ መጠይቅ፣ ገነት ደሴ መርሻ፣ 28/05/2013)።

ሌላው ለክፉ አጋጣሚ የሚደርጉ ቀናትን ባለማክበር በእንስሳቶቻቸው ላይ እና በራሳቸው ላይ የጤና ችግርን ከሚያስከትሉ ቀናት ውስጥ ወር በገባ በ13ተኛው ቀን የተለያዩ ስራዎችን መስራት ነው። ወሩ በገባ በ13 ቀን አብዛኛውን የማህበረሰብ ክፍል ስራ የማይሰራበት ቀን ነው። በዓሉ የሚከበረው የቅዱስ ዘብረአብሩክ ወርሐዊ መታሰቢያ በዓል ሆኖ ነው። በተጠኘው ማህበረሰብ የዚህ ቀን መከበር ልዩ ምክንያት የእብድ ውሻ ቫይረስ ሰዎችን ወይም ከብቶችን ሲይዝ በፀበሉ ስለሚፈውስ ነው።

በማህበረሰቡ የእብድ ውሻ ቫይረስ አስቻጋሪና በተደጋጋሚ የሚከሰት ነው። በመሆኑም ለልጆቻቸውና ለከብቶቻቸው ፀበሉን ካጠጡ በኋላ ወሩ በገባ በ13 ቀን ስራ አይሰሩም። ለዚህም የሚያቀርቡት ምክንያት በዓሉን ስንሽር በህልማችን ውሻ ይነክሰናል። በሽታውም በተደጋጋሚ በውሾቻችን ይከሰትብናል፤ የእብድ ውሻ ቫይረሱ ከብቶቻቸውንና ልጆቻቸውን በመያዝ ያሳብዳቸዋል በሚል ፍራቻ ነው (ሙሉ አድማስ፣ ቃለ መጠይቅ፣ 20/06/2013)።

ከአንድ የቤተሰብ አባላት ውስጥ የእብድ ውሻ ቫይረስ ቢከሰት ወደ ዘመናዊ ህክምና አይሄዱም። የዘብረአብሩክ ፀበልን ያልጠጡና ሂደው ያልተሳሉ ሰዎች ደግሞ በአካባቢው ከሚገኝ የእብድ ውሻ ቫይረስን የሚለይና መዳህኒት የሚሰጥ ባህላዊ ሀኪም ቤት ሂደው ለበሽታቸው ፈውስ ያገኛሉ።

ስለዚህ ነውሩ በሽታን ከመከላከል እና ከመቆጣጠር አንፃር ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። በተጠኘው ማህበረሰብ ለተለያዩ ችግሮች ያጋልጣሉ ተብለው ከሚታሰቡ ቀናትበተጨማሪ ለክፉ መንፈስ ያጋልጣሉ ተብለው የሚታሰቡ ሰዓታትም አሉ። ሰዎች የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ሲያከናውኑ ሰዓታትን መሰረት አድርገው ነው። ምክንያቱም ለክፉ መንፈስ የሚያጋልጡ፣ ለዘራፊና ለቀማኛ የሚያጋልጡ፣ ለመደብደብ የሚዳርጉ አሉ።

ሰዓታትን በተመለከተ በመረጃ ስብሰባ ወቅት የተገኙ ነውሮች ሁለት ናቸው፡፡ እነሱም ከምሽቱ ሶስት ሰዓት በኋላ ሶስት ጊዜያት ሳይጣሩ አቤት ማለት እና ከቀኑ ስድስት ሰዓት እስከ ሰባትሰዓት ባሉት ጊዜት ውሃ ለመቅዳት ወንዝ መውረድ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በማህበረሰቡ ከምሽቱ ሶስት ሰዓት በኋላ ሶስት ጊዜ ሳይጣሩ መውጣት የተከለከለ ነው፡፡ በዚህ ሰዓት ሰው ከብት ጠፍቶት ወይም ሰው ታሞበት ቢጠራ አንድ ጊዜ እንደ ተጣራ አቤት ማለት ለክፉ መንፈስ ያጋልጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡

ሰውየው ሶስት ጊዜ እስኪጣራ መጠበቅ ይመከራል፡፡ የተጣራው ሰው ብቻ ሳይሆን ቡዳ ወይም በሰው ተመስሎ የመጣ ክፉ መንፈስ ሊሆን ይችለል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ሰው ከሆነ አስከ ሶስት ጊዜ ይጣራል፡፡ ሰው ካልሆነ ሶስት ጊዜ አስኪሞላ አይቆይም የሚል እምነት አላቸው(ቃለ መጠይቅ፣ የመግስት አካሉ፣ 30/05/2013)፡፡

ይህ ነውር በጨለማ የሰውን ህይወት ለማጥፋት የሚመጡ ሰዎችንና ክፉ መናፍስቶችን ለመከላከል አገልግሏል፡፡

ለክፉ መንፈስ ከሚዳርጉ ሰዓታቶች ውስጥ ከስድስት ሰዓት እስከ ሰባት ሰዓት ውሃ ለመቅዳት ወንዝ መውረድ ተጠቃሽ ነው፡፡ በተመረጠው ተጠኝ ማህበረሰብ ውሃ የሚቀዱት በሁለት ቦታዎች ነው፡፡አንደኛው የቧንቧ ውሃ ባለበት ቦታ ሂደው ሲሆን ሁለተኛውምንጭ ካለበት ቦታ በመሄድ ነው፡፡ ውሃውን የሚቀዱበት ሰዓት አላቸው፡፡ ጧት እስከ አምስት ሰዓትእና ከሰዓት ከስምንት ሰዓት በኋላ ነው፡፡ ውሀን ለመቅዳት ስድስት ስሰት እስከ ሰባት ሰዓት ባለው መሄድ ለክፉ መንፈስ ልክፍት ያጋልጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ክፉ መንፈስ ስድስት ሰዓት እስከ ሰባት ሰዓት ባለው (በቀትር) ክፉ መንፈስ ወንዝ ይወርዳል፡፡ ዛሮች ቡና የሚያፈሉበት ሰዓት ነው፡፡ በዚህ ሰዓት ሰው ካገኙ ይይዛሉ ተብሎ ይታሰባል (ቃለ መጠይቅ፣ ሙሉ አድማስ፣ 20/06/2013)፡፡

### 5.3.5. ድህረ ጋብቻ አለባበስና አጊያጊያጥ ነውሮች

በተመረጠው ተጠኝ ማህበረሰብ እንዳይለብሱና እንዳያጌጡባቸው የሚከለከሉ የልብስና የጌጣጌጥ አይነቶች አሉ፡፡ ልብሶቹ እንደተገኙ በዘፈቀደ የሚለበሱ ሳይሆኑ ታጥበው ከመሰጣት ጀምሮ ደርቀው እስከ መለበስ ባሉት ጊዜያት ጥንቃቄ ይደረግላቸዋል፡፡

እነዚህ የአለባበስ ስርዓቶች አብዛኛዎቹ እናት ልጆቿን ስታሳድግ ለልጆቿ ማድረግ ያለባትን አለባበስና አጊያጊያጦችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ይህም የሚሆነው በህፃናት ላይ የክፉ መንፈስ በሽታ እንዳያድር በሚል እሳቤ ነው፡፡ የህፃናትን ልብስ ከማልበስና የልብስ አይነትን ከመምረጥ በተጨማሪ ከጋብቻ በኂላ የሚከበሩ አለባበስና አጊያጊያጦች አብዛኛዎቹ የሚስትን የአንገት ጌጥ አጠቃቀምና አገልግሎቱን የሚያሳዩና የፀጉር አስተካከልን የሚመለከቱ፣ የቀሳውስትንና የዲያቆናት አለባበስ ስርዓቶችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡

### 5.3.5.1. ህፃናትን ከክፉ መንፈስየሚከላከሉ አለባበስና አጊያጊያጥ ነውሮች

በተመረጠው ተጠኝ ማህበረብ ህፃናት ከተወለዱበት ቀን ጀምሮ የተለያዩ የአለባበስና የአጊያጊያጥ ነውሮች አሉ፡፡ የህፃናት አለባበስና አጊያጊያጥ ነውሮች መጠበቅ የጤና ችግር እንዳያጋጥማቸው በማድረግ ጥሩ ደረጃ እንዲደርሱ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ የህፃናትን ደህንነት ለመጠበቅ የሚያገለግሉ ነውሮችን ከመጣስ ይጠነቀቃል፡፡ ከእነዚህ መካከል የህፃናትን ልጬ ፀጉር ከክንዳቸው አለማሰር የተከለከለ ነው፡፡ ህፃናት በተወለዱ በአስር ቀናቸው ፀጉራቸውን ይላጫሉ፡፡ ልጬ ፀጉራቸውን ከመሬት መጣል የተከለከለ ነው፡፡ ተሰብስቦ በልብስ ይጠቀለላል፡፡ የተጠቀለለው ፀጉር በልብስ ይሰፋል፡፡ ከተሰፋ በኂላ ከእጃቸው ይታሰራል፡፡ ክርስትና ሲነሱ ከዚያው ከቤተክርስቲያኑ አጥር ግቢ ውስጥ ተበጥሶ ይጣላል፡፡ በጨርቅ ተጠቅልሎ ከእጃቸው መታሰሩ ህፃናት ክርስትና ተነስተው ማተቡ እሰኪጠብቃቸው ድረስ ለክፉ መንፈስ እንዳይጋለጡ ነው፡፡

ከቤተክርስትያን አጥር ግቢ ውስጥ መጣሉ ህፃኑ የክርስትና ኦርቶዶክስ ሃይማኖትን መቀበሉን ለማመልከት ነው፡፡ ክርስትና ከተነሱ በኂላ እጃቸው ላይ ያለው ፀጉር ሳይሆን ከአንገታቸው የታሰረው ማተብ ይጠብቃቸዋል ተብሎ ይታሰባል (የቡድን ቃለ መጠይቅ፣ 21/06/2013)፡፡

ህፃናት ፀጉር የሚላጩበት ህግ እንዳለው ሁሉ ጥፍራቸውንም የሚቆረጡበት ጊዜ አለው፡፡ ህፃናት እንደተወለዱ ጥፍራቸውን አይቆረጡም፡፡ ጥፍራቸውን የሚቆረጡት አመት ሲሞላቸው ነው፡፡ ለዚህ ነውር በቃለ መጠይቅ የተሳተፉ ሰዎች ሁለት አይነት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ወይዘሮ የመንግስት አካሉ ሌባ ይሆናሉ ተብሎ ስለሚታሰብ መሆኑን ስትገልፅ ሙሉየለት እንየው ደግሞ ጣታቸው እንዳይደማ ተብሎ እንደሚታሰብ ገልፀዋል፡፡ በቡድን ቃለ መጠይቅ በቀን 21/06/2013/ እንደተረጋገጠው ህፃናት አመት ሳይሞላቸው ጥፍራቸውን የማይቆረጡበት

ምክንያት ሰውነታቸው ስላልጠነከረ ሲቆረጥ ይደማል ብለው በማሰብ እንደሆነ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በጥናቱ የተመረጠው ተጠኝ ማህበረሰብ የህፃናትን ልብስ አጥበው ከጨመቁ በኋላ በዘፈቀደ አያሰጡም፡፡ በሚለብሱት ልብስ አድሮ ክፉ መንፈስ ጤና እንዳያሳጣቸው የልብሳቸው አሰጣጥና ከደረቀ በኂለ ያለው የአለባበስ ስርዓት ጥንቃቄ የተሞላ መሆን አለበት፡፡ ህፃናት ተወልደው ክርስትና እስኪነሱ ድረስ ልብሳቸው ተገልብጦ ይሰጣል፡፡ በማህበረሰቡ እምነት ይህንን ሳያደርጉ ማስጣት ክፉ መንፈስምራቁን ይተፋበታል፡፡ በመሆኑም ምራቁን በተፋበት ልብስ አድሮ ህፃናትን ጤና ያሳጣቸዋል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ ገልብጦ ባለማስጣት ይመጣል ተብሎ የሚታሰበው የጤና ችግር እከክና የቆዳ በሽታ ነው (ቃለ መጠይቅ፣ ሙሉ አድማስ፣ 20/06/2013)፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ክርስትና ያልተነሳ ህፃንልብስ ብቻውን አይሰጣም፡፡ክርስትና  እስኪነሱ ድረስ ልብሳቸው ጠባቂያ ስፈልገዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡

ማጭድ፣ ዘነዘና፣ ማረሻናቢላ ይቀመጥላቸዋል፡፡ ህፃናት ሲተኙም ከላይ የተጠቀሱት ብረቶችን ያደርጉላቸዋል፡፡ ይህ ነውር ህክምና በሌለበት ቦታና ለማሳከም አቅም ለሌላቸው ሰዎች የእከክ በሽታን የመከላከል ፋይዳ አለው፡፡

ማህበረሰቡ ብረታማ ነገሮች ክፉ መንፈስን የመከላከል አቅም አላቸው ብሎ ያምናል፡፡ለህፃናት ብቻ ሳይሆን አዲስ አራስ እናት ስትተኛ ከትራሷ ይቀመጥላታል፡፡ በመሆኑም ህፃናት ሲተኙ ትራሳቸው ላይ እና ልብሳቸው ሲሰጣ ከልብሳቸው ላይ ማስቀመጥ ክፉ መንፈስ ከአጠገባቸው እንዳይደርስ በማስደንገጥ እንዳይላከፋቸውለማድረግ ይጠቅማል፡፡ ከልብሳቸው ላይ ብረት መደረጉ ክፉ መንፈስ ከልብሱ ጋር በመግባት ልብሱን ሲለብሱት በሰውነታቸው ይዋሀዳል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው (የቡድን ቃለ መጠይቅ፣ 21/06/2013/)፡፡

ይህ ነውር የቤተሰቡ አባላት ለተለያየ ስራ ሲወጡ እናት ብቻ ከቤት ስትሆን ህፃኑን/ኗን ብቻዋን/ውን ጥላ ለመውጣት ትቸገራለች፡፡ ብቻውን እንዳይሆንም ስለምታስብ አብሮ የሚሆን ኀደኛ ትፈልጋለች፡፡ይህንም የምታደርገው እንዲጠብቀው ለማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ብረቱ የሚጠብቀውን ልጅ ተክቶ የተቀመጠ ነው፡፡ የሚጠብቅልጅ ተክቶ የተቀመጠው ብረት ከክፉ መንፈስ ይጠብቃል ብላ ስለምታስብ ነውና የእናትን ጭንቀትና ስጋት ለመቀነስ አገልግሏል፡፡

እናት ሰው የለም ብላ ሳታስብ ሰው እንዳለ በመቁጠር የዕለት ተግባሯዋን በመተማመን ትጨርሳለች፡፡አቶ ሙሉየለት እንየው የተባሉት መረጃ አቀባይ በቀን 07/06/2013/ እንደነገሩኝ ከሆነ ልጇን ብረት ሳታደርግ አስተኝታ ስራ የምትሰራ እናት ለድንገት ልጇ ቢታመምና ጤና ቢያጣ ፀፀቱ አይወጣላትም፡፡ ልጄ የታመመው በእኔ ስንፍናና መዘናጋትነው ብላ እንደምታስብ ገልፀውልኛል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ መነሳት ያለበት ሌላው ነውር ልብሱ ተጨምቆ ከተሰጣ በኋላ ወይራ ሳያጥኑ ማልበስ ነው፡፡ የደረቀው ልብስ ስለደረቀ ብቻ አንስቶ ማልበስ እንደ ነውር ይቆጠራል፡፡

> ልብሳቸውን በወይራ ወይም በጥንጅት አጥነን እናለብሳቸዋለን፡፡ በወይራ ጢስ ሳናጥን አናለብሳቸውም፡፡ ከዳሪ ተሰጥቶ ስለቆየ ነፍሳት አብሮ ገብቶ ሰውነታቸውን ይነክሳቸዋል፡፡ ወይራ ለልብሱ ሽታን ጥሩ እንዲሆን ለማድረግናልጆችን የሚጠናወት ሰይጣን ለመከላከል ጥሩ ነው (ቃለ መጠይቅ፣ሙሉ አድማስ፣ 20/06/2013)፡፡

ይህ ነውር ሁለት አይነት ጠቀሜታ አለው፡፡ አንደኛው በማህበረሰቡ ዳይፐር ስለማይጠቀሙ ህፃናት ሽንታቸውን ከልብሳቸው ይሸናሉ፡፡ በመሆኑም በወይራ መታጠኑ ልብሳቸው ጠረኑን ቀይሮ ሽታው እንዳይረብሽ ለማድረግ ይጠቅማል፡፡

የወይራው ጭስ ሽቶ የማይጠቀሙ እናቶች ብዙ ስለሆኑ እንደ ሽቶ አገልግሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በኖህ ዘመን እርግብ የጥፋት ውሃ መጉደሉን ያበሰረችበት ቅጠል የወይራ ቅጠልነው (አሪ.ዘፍ፣ 8÷11)፡፡ በመሆኑም በዚህ አውድ ወይራ የህፃናትን ደህንነት ይጠብቃል፡፡ ለክፉ አሳልፎ ከመስጠት ይልቅ ማዕዛቸውን ይቀይራል፡፡ ወይራ የጥፋትን ውሃ እንዳጎደለ የተበሰረበት በመሆኑ ለክፉ መንፈስ ተባባሪ አይደለም፡፡ሁለተኛ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና ሃይማኖት የአቢይ ፆም መጨረሻ ሳምንት አርብ ዕለት(የስቅለት ዕለት) ካህናት ምዕመናኑን በወይራ ቅጠል ጀርባቸውን ይቸበችባሉ፡፡ ይህ የሚሆነው ከሰዎች ላይ ያለ ክፉ ስራ(ሀጢያት) እንዲሰረይላቸው ነው፡፡ በመሆኑም ወይራ በማህበረሰቡ ሰፊትርጉም ያለው ነው፡፡ ስለዚህም በወይራ ልብሶችን ማጠን ለክፉ መንፈስ መከላከያ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ከሚታዩት ነውሮች ውስጥበቀለማቸው ደማቅ የሆኑ ልብሶችን ለህፃናት ማልበስ እናየእናትን የአንገት ጌጣጌጥ ለሴት ልጆች ማልበስ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በተጠኘው ማህበረሰብ ህፃናት ለበሽታ የሚዳርጉ ልብስን አጥቦ ከማስጣትና ከማልበስ ጋር የተያያዙ ነውሮች ብቻ አይደሉም፡፡ የሚለብሷቸውን የልብስ አይነቶች መምረጥ ለጤንነታቸው ወሳኝ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ አልባሳት በአይነታቸው የተመረጡ ካልሆኑና ከህፃናት ባህሪያት ጋር የማይስማሙ ከሆነ ህፃናትን ለበሽታ ይዳርጋሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡

ህፃናትን ለክፉ መንፈስ የሚያጋልጡ የልብስ አይነቶች አሉ፡፡ ክፉ መንፈስን ከህፃናት ላይ ያዋህዳሉ ተብለው ከሚታሰቡ የልብስ አይነቶች ውስጥ በቀለማቸው ደማቅ የሆኑ ልብሶችን ማልበስ ተጠቃሽ ነው፡፡ በቀለማቸው ደማቅ ከሆኑ ልብሶች ውስጥ ቀይ እና ነጭ ልብሶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ቀይና ነጭ ቀለም ያላቸውን ልብሶች ለህፃናት ማልበስ ነውር የሆነበት ምክንያት ክፉ መንፈስ በልብሱ ተስቦ ከህፃናት ላይ ያርፋል፤ቡዳ ይበላቸዋል በሚል እሳቤ ነው፡፡

> ሾላውና ዋርካው አልቋል፡፡ ዛፎች ተመናምነው ባዶ ሜዳ ቀርቷል፡፡ ታዲያ ህፃናትን አግኝቷቸው ነው፤ ከምኑ ይሰፍራል፡፡ ድሮ የሚያምር ትፍትፍ ለብሰን ጫካ ስንዞር ምንም አይለንም ነበር፡፡ዛሬ ልጆቻችን በልክፍት ተቸግረዋል፡፡ እንዲያውም በጣም ሚያምሩና ቀይ ከሆኑ በቀለሙ ደብዛዛና ጠቆር ያለ እናለብሳቸዋለን (ቃለ መጠይቅ፣ ይመኑ መኮነን፣ 15/06/2013)፡፡

ነውሩ ክፉ መንፈስን ከመከላከል በተጨማሪ የልጆችን የልብስ ፍላጎት ገደብ እንዲኖረው ለማድረግ እና የእናትን የስራ ጫና ለመቀነስ ይጠቅማል፡፡ በአሁኑ ዘመን ልጆች ያዩትን ሁሉ የመልበስ ፍላጎት አላቸው፡፡ በቀለማቸው ቀይ እና ነጭ የሆኑ ልብሶች በሩቅ ደምቀው የመታየት ባህሪ አላቸው፡፡ በዚህን ጊዜ ህፃናት ከሩቅ ደምቀው በሚታዩት ልብሶች ተስበው እንዲገዛላቸውም ቤተሰብን ያስቸግራሉ፡፡ ማህበረሰቡ ይህንን ፍላጎታቸውን ለመገደብ ሲል ህግ ያወጣላቸዋል፡፡ በመሆኑም ይህ ነውር ህፃናት በሩቅ ደምቀው ሊታዩ የሚችሉ ልብሶችን በማየት የተለበሰውን አይተው ግዙልኝ እንዳይሉ ፍላጎታቸውን ለመገደብ ተጠቅመውበታል፡፡ ሁለተኛው የእናትን የስራ ጫና ለማቅለል ነው፡፡ነጭ ልብስ ቆሻሻ አይችልም፡፡ ህፃናትም ቶሎ ቶሎ ስለሚያቆሽሹ ልብሱ ተመራጭ አይደለም፡፡ በመሆኑም እናት የእነሱን ልብስ ለማጠብ የምታወጣውን ጉልበት ይቀንሳል፡፡

በተመረጠው ተጠኝ ማህበረሰብ እንደ ልብስ አይነቶች ሁሉ ለክፉ መንፈስ የሚያጋልጡና ክፉ መንፈስን ከአንዱ ወደ አንዱ እንዲተላለፍ የሚያደርጉ የአንገት ጌጥ አይነቶች አሉ፡፡

ከእነዚህ የአንገት ጌጣጌጥ አይነቶች ውስጥ ድሪና ብርቅጥል ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህን የእናቶችን የአንገት ጌጣጌጦች ለሴት ልጆች ማልበስ የተከለከለ ነው፡፡ በተለይም ቅድመ ጋብቻ ላይ ላሉ ወጣት ሴቶች እና ለህፃናት ሴቶች ማልበስ ለክፉ መንፈስ በሽታ ይዳርጋቸዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በሽታው የሚመጣው ከእናት ወደ ልጅ በመተላለፍ ነው፡፡

እናቶች ከሚጠቀሟቸው ጌጣጌጦች ውስጥ ድሪና ብርቅጥል ቀዳሚዎች ናቸው፡፡ ድሪና ብር ቅጥል ለማጌጫ ከመጠቀማቸው ባለፈ በክፉ መንፈስ ምክንያት ከሚመጣባቸው በሽታ ለመከላከልና ይዟቸው ከሆነም ለክፉ መንፈሱ ማስታገሻና መደለያ አድርገው ይጠቀሙበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ዛር ያለባቸው ሰዎች ዛሩ እንዳይረብሻቸውና እንዳያማቸው ቀይ ጥለት ተገዝቶ ሰውነታቸውን በጥለቱ ዳስሰው ነጠላ ወይም ቀሚስ ያሰሩታል፡፡ ነጠላው ወይም ቀሚሱ በዘመን መለወጫ በዓልና ዛሩ ሲነሳባቸው ብቻ ይለበሳል፡፡

እናት ብትሞት የእሷን የአንገት ጌጣጌጥ በትዳር ያለች ሴት ልጅ ካለች ዝም ብላ አንስታአትለብስም፡፡ በአንጥረኛ ፈርሶ እንደገና ከተሰራ በኋላ መልበስ ትችላለች፡፡ ካለበሰችው ደግሞ ተሽጦ ገንዘቡን መጠቀም ነውር አይሆንም፡፡ በመሆኑም የእናቶችን ጌጣጌጥ ለህፃናትና ላላገቡሴት ወጣቶች ማልበስ ከእናቲቱ የነበረ ክፉ መንፈስ ካለ ወደ ለበሰችው ሴት ይተላለፋል ተብሎ ይታሰባል (ቃለ መጠይቅ፣የመግስት አካሉ፣30/05/2013)፡፡ የዚህ ነውር ዋና ጠቀሜታ የክፉ መንፈስ ተስተላልፎን መቆጣጠር ነው፡፡

የእናትን ብርቅጥል ለሴት ልጆች ማልበስ የተከለከለ እንደሆነ ሁሉ አንድ እናት ከአንገቷ ብርቅጥል አለማድረግ ነውር ነው፡፡ ምክንያቱም እናቶች ምጥ በሚጠነክርባቸው ሰዓት የሚጠቀሙበት የአንገት ጌጥ አይነት በመሆኑ ነው፡፡ ዘመናዊ ህክምና በአካባቢው ቢስፋፋም አስከ አሁን ድረስ ቤት የሚወለዱ እናቶች አሉ፡፡ ነውሮቹ አሁን ላይ ሙሉ በሙሉ ያልጠፉ ቤት የሚወልዱ እናቶች ብቻ የሚጠቀሙባቸው ናቸው፡፡

ሴት ልጅ ከአንገቷ ብርቅጥል አለማድረግ በወሊድ ስዓት ምጥ እንዲጠንክር መንስዔ ይሆናል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ክፉ መንፈስ ከሰው ላይ ከሚያርፍባቸው ጊዜያት ውስጥ በወሊድ ስዓት እንደሆነ ይታመናል፡፡ በወሊድ ስዓት እናቶችን ልባቸውን በመሰወር ለሞት የምትዳርግ ሰራቂያን የተባለች መንፈስ እንዳለች ይታመናል፡፡

ይህች መንፈስ ለመከላከል ብርቅጥል ወሳኝነት አለው ተብሎ ይታሰባል፡፡ ለዚህም እናቶች በወሊድ ስዓትም ሆነ በዘወትር ተግባራት ከአንገታቸው እንዳይወልቅ ይመከራል፡፡ ያገቡ ሴቶች ከሚጠቀሙባቸው የአንገት ጌጦች ውስጥ ብርቅጥል አንዱ ነው፡፡

በተጠኝው ማህበረሰብ ያገቡ ሴቶች እንዳላቸው የሀብትና መጠን አንድ እስከ አምስት ብርቅጥል አላቸው፡፡ በኢኮኖሚ ዝቅተኛ የሆኑ ሴቶች ቢያንስ አንድ ብርቅጥል አላቸው፡፡ በመሆኑም ብርቅጥል አለማድረግ እንደ ነውር ይቆጠራል፡፡ አቶ በቃሉ ፈጠነ በማህበረሰቡ እንደ ነውር የሚቆጠር ድሪ ነው በማለት ‹‹ተይ ድሪ ተይ ድሪ ድሪ ይሻልሳል አሁን እኔ ብሞት ምን ያደርግልሻለ›› ተብሎ እንደሚገጠምና ድሪ ክቡር እንደሆነ ቢገልፁልኝም ከሌሎቹ መረጃ አቀባዮች ደግሞ ብርቅጥል አለማድረግ ነው የሚል የተለያየ መልስ ተገኝቷል፡፡ ይህንን የተለያየ ሀሳብ ባደረግሁት የቡድን ቃለመጠይቅ ማረጋጋጥ ችያለሁ፡፡

> ሴቶች ሲወልዱም ሰራቂያን የምትባል ሴት መንፈስ አፍና አፋቸውን ገጥማ ትሰውራቸዋለች፡፡ በዚህ ሰዓት ብርቅጥሉን ጥርሷን ፈልቅቀን አስገብተን እንድትይዘው እናደርገል፡፡ ብርቅጥሉ ጠባቂ በመሆኑ ይመልሳታል፡፡ አንድ ሴት ከአንገቷ ብርቅጥል አድርጋ ካየን ባል እንዳለት እንረዳለን ከአንገቷካላየን ባል የላትም ብለን እናስባለን (የቡድን ቃለ መጠይቅ፣ 21/06/2013)፡፡

የዚህን ነውር ጠቀሜታ በሁለት መልኩ መመለከት ይቻላለ፡፡ የመጀመሪያው ብርቅጥል ለማጌጫነት ብቻ ሳይሆን ወንዶች ባል ያላት ሴት መሆኑን ተረድተው ያታዊ ትንኮሳ ከማድረግ እንዲቆጠቡ እና ክፉ መንፈስን የመከላከል ፋይዳ እንዳለው መረዳት ይቻላል፡፡

ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪ ለሚስት ምጥ መጠንከር ምክንያት የባሏ ቂም ያዥ መሆን ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ ስለዚህም ሚስትበምጥ ስዓት እያለች ባል ቀበቶውን አለመፍታት የተከለከለ ነው፡፡ ቀበቶውን ካልፈታ ቂሙ አይፈታም፤ ቂሙ ካልተፈታ ደግሞ ሚስት ቶሎ አትገላገልም የሚል እምነት አላቸው፡፡ ከአቶ ይመኑ መኮነን ጋር በቀን 15/06/2013 ባደረግሁት ቃለ መጠይቅ በአሁኑ ስዓት እየቀረ ያለና ምጥ ሲጠነክርባቸው ቀበቶ ከማውለቅ ይልቅ ድርሳነ ሩፋኤል የሚያነብ ቄስ በማምጣት ችግሩ እንደሚፈታላቸው ገልፀውልኛ፡፡

#### 5.3.5.2. ለተቃራኒ ፆታ ግንኙነት መጋለጥን የሚከላከሉ የአለባበስ/ አጊያጊያጥ ነውሮች

በዚህ ርዕስ የቀረቡ ነውሮች ድህረ ጋብቻ ላይ ያሉ ባልና ሚስትን የሃይማኖት አባቶችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ የሃይማኖት አባቶች ቤተክርስትያን የምትፈቅድላቸውን አለባበሶችና አጊያጊያጦች ካልተጠቀሙ በሃይማኖቱ ተከታዮች ዘንድ ታማኝነትን ያጣሉ፡፡

ለተቃራኒ ፆታ ግንኙነት መጋለጥን የሚከላከሉ አለባበስና አጊያጊያጥ ነውሮች ከተጣሱ የሃይማኖት አባቶችን ቤተክርስትያን የገቡት ከግብረስጋ ግንኙነት ንፁህ ሆነው እንዳልሆነ የሚያስቆጥሩ፣ በስካርና በዝሙት ተሸናፊ እንደሆኑ የሚያሳዩ ነውሮች ናቸው፡፡

ባልና ሚስትን ሚስትን ለተቃራኒ ጾታዊ ግንኙነት ያጋልጣታል በሚል ፍራቻ ከሚከበሩ ነውሮች  መካከል የገበሬ ሚስቶች ፀጉር ቤት ሂደው ፀጉራቸውን መስተካከል ተጠቃሽ ነው፡፡ በተጠኘው ማህበረሰብ ሴቶች አልፎ አልፎ ፀጉራቸውን ያሳድጋሉ፡፡ ፀጉራቸውን ያላሳደጉ ሴቶችከቤታቸው ሆነው በመቀስ ይስተካከላሉ፡፡

ነውር የሆነበት ምክንያት ፀጉሯን በሚያስተካክላት ጊዜ ሲዳብሳት የተለየ ስሜት ይሰማታል፡፡ ፀጉር አስተካካዩም በውበቷ ተማርኮ ያፈቅራታል፡፡ እሷ እምቢብትል እንኳ ‹‹ቤት ዘግቶ ሊደፍርብን ይችላል›› የሚል እምነት አላቸው፡፡

> ሚስቶቻችን ጠጉራቸውን በመቁረጫት (መቀስ) ይስተካከላሉ፡፡ የገበሬ ሚስቶች ሲገቡ ብናይ ኸረ የእገሌን ሚስት ፀጉር ሚያስተካክለው ሰውየ ለምዷታል መሰል ትመላለሳለች ተብሎ ይወራል፡፡ ሚስቴም ብትሆን ለምዷት ነው እንጅ ምናባቷ ማድረግ ኸደች ብየ እናደዳለሁ፤እሷንም እጣላታለሁ፤ እንድትቀርና ሁለተኛ እንዳትሄድ አደርጋታለሁ (ቃለ መጠይቅ፣ ካሳየ ፍቃዱ፣ 05/06/2013)፡፡

ይህ ነውር ከጊዜ በኂላ ነውር ሆኖ አይቀጥልም የሚል ግምት አለኝ፡፡ ምክንያቱም በአካባቢው ማህበረሰብ ያሉ የፀጉር ቤት ሰራተኞች ወንዶች ናቸው፡፡ በተለይ በአየኂቸው 3 የገጠር ከተማዎች ማለትም በውፍታ ዳጢ ሮቢት ምትባል ከተማ ፣ በአባድራ አባድራ ከተማ እና በዳንግላ ቀበሌ 3 ከተማ ፀጉር የሚያስተካክሉ ሁሉም ወንዶች ናቸው፡፡ በመሆኑም ባሎቻቸው ሚስቶቻቸውን እንዲጠራጠሩ ያደረጋቸው ሴቶች በፀጉር ማስተካከል ስራ አለመሰማራታቸው ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

በተመረጠው ተጠኝ ማህበረሰብ ስልጣነ ክህነት ያላቸው የሃይማኖት አባቶች ለግብዣ ከተጠሩበት ቤት መስቀል እረስተው መውጣት፣ የተለያዩ የፊትና የፀጉር መዋቢያዎችን መጠቀም እንደነውር ይቆጠራል፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን በቅዳሴና በቅኔ ማህሌት የሚያገለግሉ የሃይማኖት አባቶች የሚተገብሯቸውን የተለያዩ ድጊቶች በማስተዋልና በጥንቃቄ መሆን አለበት፡፡ በክርስትና፣ በሰርግ፣ በተስካርና በተለያዩ ግብዣ በተጠሩባቸው ቦታዎች ሲጠጡ በልክ መሆን አለበት፡፡ በእነዚህ በተጠቀሱት ግብዣዎች መስቀላቸው ካስቀመጡበት ቦታ ከኪሳቸው ሾልኮ ቢወድቅ ወይም ከተቀመጡበት ቦታ አስቀምጠውት መውጣት በሃይማኖቱ ተከታዮች ዘንድ እንዳይታመኑ ያደርጋል፡፡ ምክንያቱም መስቀላቸውን በየሄዱበት የሚጥሉ የሃይማኖት አባቶች ሰካራም ናቸው ተብሎ ይታሰባል፡፡

የሃይማኖት አባቶች እናዲያቆናት ሰው ሰራሽ የሆኑ ማጌጫዎችን፣ ቅባቶችንና ባዝሊኖችን በመጠቀም ፀጉራቸውንና ፊታቸውን ማስዋብ የተከለከለለ ተግባር ነው፡፡ የሃይማኖት አባቶች በተፈጥሮ ውበታቸው ብቻ እንዲያጌጡ ይመከራል፡፡ ፀጉራቸውንም ሽታው ሰዎችን የመሳብ አቅም ባለው ሳሙና መታጠብም የተከለከለ ነው፡፡ የተጠቀሱትን ማጌጫዎችና መዋቢያዎች ተጠቅመው ቢታዩ ስልጣናቸውን እንደጣሉና በዝሙት መንፈስ እንደተሸነፉ ይቆጠራል (ቃለ መጠይቅ፣ ቄስ ገበየሁ ታገለ፣ 12/06/2013)፡፡

ይህ ነውር ድህረ ጋብቻ ላይ ያሉ የሃይማኖት አባቶችን ብቻ ሳይሆን ቅድመጋብቻ ላይ ያሉ ዲያቆናትን ጭምር የሚያጠቃልል ነውር ነው፡፡

ድህረ ጋብቻ ላይ ያሉ የሃማኖት አባቶች ሌሊት ወደ ቤተክርስትያን በሚሄዱበተ ጊዜ የለበሱትን ልብስ በሚገባ ማስተዋል አለባቸው፡፡ አንድ የቤተክርስትያን አባት የሚስቱን ነጠላ የእሱ ኩታ/ጋቢ መስሎት ለብሶ ቢሄድ መቀነቷን ሻሽ መስሎት ጠምጥሞ ቢወጣና ከነጋ በኋላ ሰው ቢያየው ከሚስቱ ጋር አብሮ አድሮ ቤተክርስትያን እንደገባ ይቆጠራል፡፡ የሃይማኖት አባቶችን በተመለከተ የተዘረዘሩት የአለባበስና የአጊያጊያት ነውሮች የሃይመኖቱ ተከታዮች ከሀይማኖት አባቶች ጋር ግንኙነታቸው የጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ የሚጠቅሙ ናቸው፡፡

## 5.4. የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች

በቅድመ ጋብቻ ያሉ ነውሮች ቅድመ ጋብቻ ላይ ያሉ ወጣቶችን በስነ ምግባርለማነፅ፣ በትጭጭት ላይ ያሉ ወጣቶች የጋብቻ ፍላጎታቸው እውን እንዲሆን ለማድረግና የቅድመ ጋብቻ አፈፃፀም ስርዓት ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው፡፡

በመረጃ ትንተናው ወቅት የተገኙ ቅድመ ጋብቻ ነውሮች ቅድመ ጋብቻ ላይ ባሉ ሴቶች ማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ችግሮች እንዲሁም ያታዊ ትንኮሳዎች ከመድረሳቸው በፊት ቅድመ መከላከሎች በመሆን የሚያገልግሉ መሆናቸው በጥናቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡ እነዚህ ነውሮች ከተጣሱ የእርስ በርስ ግጭትን እንዲሁም መገዳደልን እንደሚያስከትሉና በትጭጭት ላይ ያሉ ተጋቢዎችንና ቤተሰቦቻቸውን ለስነ ልቦናዊና ማህበራዊ ችግር እንደሚያጋልጡ በጥናቱ ታይቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቅድመ ጋብቻ ማንነት ገለጭ አለባበስና አጊያጊያጥ ነውሮች ማህበረሰቡ ወንጀል ለመስራት የተዘጋጀን ሰው ለመለየት፣ ወጣቶች ለተቃራኒ ፆታዎች ግንኙነት እንዳይሳቡ ለማድረግ የሚያገለግሉ መሆናቸው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

ዕለተ ጋብቻን በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች ትንታኔ እንደሚያመላክተው ቀጣርን የተመለከቱ ነውሮች በጋብቻ ውል አፈጻፀም ላይ የሚፈጠር አለመግባባትንና የሀሳብ ልዩነትን ለማጥበብ የሚጠቅሙ ናቸው፡፡ ሙሽሮችን የተመለከቱ ነውሮች በዕለተ ጋብቻ ቀናቸውና ከተጋቡ በኋላ ይደርስባቸዋል ተብሎ የሚታሰብን ችግር በመፍራት የሚያከብሯቸው መሆናቸውን በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የስር ሚዜንና አሳዳሪን በተመለከተ የሚፈሯቸው ነውሮች በዕለተ ጋብቻ ፆታዊ ትንኮሳዎች እንዳይፈጠሩና የእለተ ጋብቻ ስርዓቱ በሰላም እንዲጠናቀቅ ለማድረግ የሚጠቅሙ ሲሆኑ ሀላፊነት መወጣትንና ሚስጥር ጠባቂነትን የሚሰብኩ ናቸው፡፡

ድህረ ጋብቻ ነውሮች በባልና ሚስት መካከል አለመግባባቶች እንዳይፈጠሩ ለማድረግና በሚስት ቤተሰቦች ጣልቃ ገብነት ምክንያት የሚፈጠሩ ግጭቶችን በመቆጣጠር አብሮነትን፣ የመከባበር እሴትንና ይቀር ባይነትን ለማስተማር የሚጠቅሙ እንዲሁም የባልና ሚስት ስንፍናን የሚያወግዙ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ድህረ ጋብቻ ላይ ያሉ ሰዎች ነውሮችን በልጆቻቸውና በንብረቶቻቸው በክፉ መንፈስ ምክንያትየሚመጣን የጤና ችግር ቀድመው ለመከላከልና ተስተላልፎውን ለመግታት የሚጠቀሙባቸው ሲሆኑ ከአለባበስና ከአጊያጊያጥ እንዲሁም ከቀናት አከባበር ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ድህረ ጋብቻ ላይ ያሉ ነውሮችን መጣስ ጤና ማጣትን፣ የእርስ በርስ ግጭትን፣ በሰዎች ዘንድ አሜኔታ ማጣትን የሚያስከትሉ ናቸው፡፡

## ምዕራፍ ስድስት፡- ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ‹‹የጋብቻ ነውሮች በዳንግላ ወረዳ›› በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ የዳንግላ ወረዳ ከሌሎች ወረዳዎች ተመራጭ የሆነበት ምክንያት በአዊ ዞን ከሚገኙ ወረዳዎች ከቋንቋና ከትራንስፖርት አገልግሎ አንፃር ምቹ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

የጥናቱ ዋና አላማ የዳንግላ ወረዳ ማህበረሰብ የሚያከብሯቸውን የጋብቻ ነውሮችን በመተንተን ያላቸውን ፋይዳ መግለፅ ነው፡፡ በቅድመ ጋብቻ ወቅት የሚከበሩ/ለመጣስ የሚፈሯቸውን ነውሮች መተንተንሚዜን፣ አሳዳሪን እና ሙሽሮችን የሚመለከቱ ነውሮችን ማብራራት፣ ድህረ ጋብቻን የተመለከቱ ነውሮችን መግለጽ፣ የጋብቻ ነውሮች በምሳሌያዊ ንግግሮች እና በተረኮች እንዴት እንደሚገለፁ ማሳየት የሚሉት ንዑሳን አለማዎች አሉት፡፡

ጥናቱ የተጠቀመው ንድፍ ሀሳባዊ ማዕቀፍ የተግባራዊነትን ንድፍ ሃሳብ ነው፡፡ ንድፍ ሀሳቡ ነውሮችን ያላቸውን ጠቀሜታ ለመተንተን ተመራጭ ሆኖ በመገኘቱ በጥናቱ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ጥናቱ በወረዳው ከሚገኙ 32 ቀበሌዎች ውስጥ አራት ቀበሌዎች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ እነዚህ ቀበሌዎች የተመረጡበት ምክንያት ሙሉ በሙሉ የአማርኛ ቋንቋ የሚነገርባቸው እና የክርስትና ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች በመሆናቸው ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በወረዳው ውስጥ የሚገኙ ቀበሌዎች የጋብቻ ስርዓት ባህላቸውና የጋብቻ ነውሮች ተመሳሳይነት ስላላቸው እነዚህ ቀበሌዎች ሁሉንም ይወክላሉ ብየ በማሰብ ነው፡፡

በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታና በቡድን ቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች ቅድመ ጋብቻ፣ ዕለተ ጋብቻ እና ድህረ ጋብቻ ተብለው የተከፋፈሉ ሲሆን ጭብጣዊ የአተናተን ስልትን ተከትለው ይበልጥ ወደ ሚቀርባቸው ይዘት ተመድበው ተተንትነዋል፡፡

በቅድመ ጋብቻ ሴት ልጅ ከጋብቻ በፊት መድረግ የሌሉባትን ነውሮች፣ ለጋብቻ የተጫጩ የሴትና ወንድ ቤተሰቦችን የሚመለከቱ ነውሮች እመዲሁም ማንነት ገላጭ አለባበስና አጊያጊያጥ የሚሉት በዝርዝር ተብራርተው ቀርበዋል፡፡

ዕለተ ጋብቻ ነውሮች አጋቢ ዳኞችን፣ ሙሽሮችን፣ አሳዳሪና የስር ሚዜን የተመለከቱ ሲሆኑ እያንዳንዳቸውን በየ ንዑስ ርዕሶች ውስጥ ተካተው ቀርበዋል፡፡ በዚህ ውስጥ ተጋቢዎችን ለክፉ መንፈስ የሚያጋልጡ ነውሮችና ለሙሽሮችን መልካም ምኞት የሚገልፁ ቁሳቁሶች አጠቃቀም ነውሮች በትንታኔው ታይተዋል፡፡

ድህረ ጋብቻ ላይ ያሉ ሰዎች ለቤተሰባቸው አባላትና ለእንስሳቶቻቸው የጤና ችግርን ያደርሳሉ ተብለው የሚታሰቡ ቀናትን በተመለከተ ለምን እንደሚያከብራቸው ከህገረሰባዊ እምነቶችና ልማዶች አንፃር በመፈተሽ ተተንትነዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሚስትን የሚመለከቱ ነውሮች፣ አማችን የሚመለከቱ፣ የህፃናትን ልብስ አለባበስና አጊያጊያጥ በተመለከተ ልጆችን በሚያሳድጉበት ወቅት ወላጆች ማክበር የሚገባቸው ነውሮች ታይተዋል፡፡

# ዋቢ መጻህፍት


ሞላ ጀምበሬ። (2009)። የነውር እሳቤ በሊሞ ከምከም ወረዳ ማህበረሰብ እምነት። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ ለፎክሎር ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት።

ቅዱስ ቁርኣን። (1997)። አዲስ አበባ፣ ነጃሺ አሳታሚ ድርጅት።

አለቃ ኪዳነ ወለድ ክፍሌ። (1948ዓ.ም)። *መጻፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ*። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ኤፍሬም አሰፋ። (ዓ.ም ያልተጠቀሰ)። *እንግሊዘኛ አማርኛ መዝገበ ቃላት።*

የኢትዮጵያ መጽሃፍ ቅዱስ ማህበር።(1981ዓ.ም)። የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት። *መጽሐፍ ቅዱስ።* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

የኢትዮጵያ መጽሃፍ ቅዱስ ማህበር። *የመጽሃፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት።* (1993)። አዲስ አበባ፣ ባናዊ ማተሚያ ቤት።

የዳንግላ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ፅህፈት ቤት። ባህልና እሴት ኢኮኖሚ ልማት ቡድን። (2011ዓ.ም)። *በሰረግ ስነ ስርዓት ላይ የተዘጋጀ ፅሁፍ፣* ያልታተመ።

የዳንግላ ወረዳ የኢኮኖሚ ልማት ፕላን ኮሚሽን በጀት አመት። (2013ዓ.ም)። *ስታቲካል መፅሄት፣* ያልታተመ።

Agbemenu et,al. (2017). sex will make Fingers grow thinand thin then you dia. The interplay of Culture, Myth, and taboo on African Immigrant Mothers, perceptions of reproductive Health education with ther Dougther Age 10-14. Journal of Immgrants and minority Health.

Angsongn, Alexander et.al. (2016). A systematic review of resource habitat taboos and human health outcomes in the context of global environmental change, Global Biothics. Vol. 27, NOS. 2—4, 91—111.

Bascom, W. (1954).four function of folklore. Vol.67, No.226. pp 333-349.

Birhanu Takele. (2017). AThematic analysis of Linguistic Taboo and their corresponding Euphemistic expression in Oromo. Addis Ababa university, college of Humanites, Language studies, Jornalism and communication college.

Chigidi, William Lungisani. (2009).Shona taboos: The language of manufacturing fears for sustainable development.The Journal of Pan African Studies, pp174-188.

Dawit Assefa, et al. (2005). Harmful Traditional Practices in Ethiopia. Ethiopian Public Health, Training Initiative, Training Module.

Dawson, Catherine. (2002). *Practical Research Methods: A user- Friendly guide to mastering techniques and projects*. Published by Ltd, 3, Newtec Place, Magdalen Road.

Diago, Gomez. (2020). Functionalist Theory. In Merskin, L. Debra. (ed.), *The SAGE International Encyclopedia of Media and Society*. SAGE Publication, Lnc.

Dilshad, Muhammad and Latif, Muhammad. (2013). Focus group interview as a Tool Qualitative Research: An Analysis. Pakistan Journal of Social Sciences, Vol. 33, No.1, pp191-198.

Dodo, Obediah. (2015). *Endogenous Conflict Prevention: Mythand Realities*. Bindura University Press.

Freud, Sigmund. (1913).*Totem and Taboos:* Some Points of Agreement between the Mental Lives of Savages and Neurotics, (J. Strachey, Trans.). London and New york, published by Hugo Heller.

Getanhe Haile. (2007). the contribution of GUDO Forest conservation culture is keyto bio diveresty conservation. Jiggiga University.

Golding, Johan and Folke, Carl.(2001). Inivsibel Systems of Lokale Resource Management and Biological Consrevation. vol.11, No. 2, pp584-600.

Mabay. (2002). linguistic taboo in Africa marriag: the study of Oromo LIguu. In Nordic Journal of African Studies, 224-225.

Maru et.al. (2020). Indigenous ways of environmental protection in Gedio community, southern Ethiopia: A siocio ecological perspctive. College of agricultural and natural resources. Department of Natural resources Management, Dilla University.

Masaka, Dennis and Chemhuru, Munamato. (2010). TaboosAs Sources of Eniviromental Ethics. Journal of Sustainable Development in Africa, Vol 12, No.7, PP 121-133.

Nejimu, B. Z. (2015). Food Taboos and Misconceptions among Pregnant Women of Shashemene District, Ethiopia. Science Journal of Public Health, pp 410- 416.

Ombola, Odejob. (2013). An overview of taboo and Superstition among the Yoruba of Nigeria. Mediterraen Journal of Social Sciences.

Oring, Elliot. (1976). Three Functions of Folklore: Tradition Functionalism as Explanation in Folklristics. Vol. 89, No. 351, pp 67-80.

Osei, Joseph. (2006). The value of African taboos for biodiversity and sustainable development. Journal of Sustainable Development in Africa'', 42-61.

Saggaf, Yeslam. (2008). Breaking the taboos: the cause of Marriage education communities in Sudi Arbia. Harles Sture University, IADIS International Conference, Conference Paper.

Sciortion, Giuseppe. (2009). Functionalism and Social System Theory. In Turner, Bryans. (ed.), *Blackwell Companion to Social Theory*. A John Wiley and sons. Ltd, publication.

Sims and Stephens. (2005). *living folklore*: an introduction to the study of people and their traditions. Utah State University Press.

Wellelaw Getnet, (2018). Determinants of Food Taboos in the pregnant women of the Awabel District, east Gojjam zone. Debremarkose university.

**አባሪ አንድ፡- ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ ዋናዋና ጥያቄዎች**

1. ነውር ማለት ለእርስዎ ምን ማለት ነው?
2. በቅድ ጋብቻ ማን ምን ቢፈፅም ነውር ይሆንበታል? ለምን ነውር ተባለ?
3. በአካባቢያችሁ ቅድመ ጋብቻ ላይ ያሉ ሰዎች ምን አይነት አለባበስ/አጊያጊያጥ ቢለብሱ/ቢያጌጡ ነውር ይሆናል? ለምን ነውር ተባለ?
4. ዕለተ ጋብቻን በተመለከተ ከሚዜዎች ከአጋቢ ዳኖች እንዲሁም ሙሽራውንና ሙሽሪትን በተመለከተ የሚያውቁት ነውር ካለ ቢገልፁልኝ?
5. ገበያ ቢወጡ፣ ለቅሶ ቢሄዱ፣ ሽምግልና ቢቀመጡ ለእርሰዎ፣ ለልጆችዎና ለንብረትዎ መሰናክል ይሆናሉ፤ለክፉ አጋጣሚ ይዳርጋሉ የምትሏዋቸው ነውሮች ካሉ ቢነግሩኝ?
6. ነውሮች ለመግለፅና እንዳይጣሱ ለማደረግ የምትጠቀሚቸው ተረኮችና ምሳሊያዊ አነጋገሮች ካሉ ቢነግሩኝ?
7. ነውር ጠቀሜታ አለው ካሉ ጠቀሜታውን ጉዳት አለው ካሉ ጉዳቱን ያለዎትን ሀሳብ ቢገልፁልኝ? ሌሎች እነዚህን ጥያቄዎች ሊደግፉ የሚችሉና ለመረጃ አቀባዮች ግልፅ እንዲሆንላቸው ሲባል የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ከዚህ ላይ የተጠቀሱት ዋናዋናዎቹ ብቻ ናቸው፡፡

**አባሪ ሁለት፦ በዚህ ስር የመረጃ ሰጭዎች ፎቶ እና ዕለተ ጋብቻ (በሰርግቀን) ክዋኔዎች አጋጣሚ ነውሮችን በሚሰበሰቡበት ወቅት ለመረጃው አስፈላጊ የሆኑ ፎቶዎች የቀረቡበት ነው፡፡**





አጥኘዋ ከአቶ ከገነት ደሴ ጋር እና ከአቶ ድሉ ተፈራ ጋር ቃለመጠይቅ ስታደርግ የሚያሳይ ፎቶ



አጥኝዋ በወጣት ስመኝ እጀጉ እና ታረቀኝ አለምነህ የጋብቻ ቀን ሙሽሮችን ምልከታ ስታደርግ



አጥኝዋ በእጅጉ ታየ ቤት ጓሮ በስመኝ እጅጉ እና በታረቀኝ አለምነህ የጋብቻው ቀን ከሙሽራው ቀድመው የሚመጡ አጋቢ ዳኞች የጋብቻውን ሲያፀድቁ  ምልከታ ስታደርግ





ሙሽሪትን ሳትይዘው ብትሄድ ነውር የሚሆነውን ሙዳይ የሚያሳይና በውስጡ የሚቀመጡ ማጌጫዎችን የሚያሳይ ፎቶ





አጥኝዋ የቡድን ቃለ መጠይቅ ስታደርግ የሚያሳይና የተሳተፉ የቡድን አባላትን የሚያሳይ ፎቶ

**አባሪ ሶስት ፡- በቡድን ቃለ መጠይቅ የተሳተፉ፣ በቁልፍ መረጃ አቀባይነት፣ የተሳተፉ እና ሌሎቹ መረጃ አቀባዮች**

**በቡድን ቃለ መጠይቅ የተሳተፉ ሰዎች**

| ተ.ቁ | ስም | ፆታ | እድሜ | ስራ | ቀበሌ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ሙሉየለት እንየው | ወ | 38 | አርሶ አደር | ውፍታ ዳጢ |
| 2 | አቶ ተረፈ ስዩም | ወ | 48 | አርሶ አደርና ሚኒሻ | ውፍታ ዳጢ |
| 3 | አቶ በእውቀቱ ተሻለ | ወ | 60 | አርሶ አደር | ውፍታ ዳጢ |
| 4 | አቶ ትዕዛዙ ገነት | ወ | 52 | አርሶ አደር | ውፍታ |
| 5 | ወ/ሮ የመንግስት አካሉ | ሴ | 50 | የቤት እመቤት | ውፍታ ዳጢ |
| 6 | አቶ ክንዴ ተስፋ | ወ | 54 | አርሶ አደር | ውፍታ ዳጢ |
| 7 | አቶታፈረ ሰዋገኝ | ወ | 70 | አርሶ አደር | ውፍታ ዳጢ |
| 8 | አቶደሳለኝ መብራቱ | ወ | 65 | አርሶ አደር | ውፍታ ዳጢ |

## ቁልፍ መረጃ አቀባዮች

| ተ.ቁ | ስም | ፆታ | እድሜ | የስራ ሁኔታ | ቀበሌ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ከፋለ ነጋ | ወ | 81 | አርሶ አደር | አጋጋ |
| 2 | አቶ ድሉ ተፈራ | ወ | 66 | አርሶ አደርና የአባት አርበኛ | አባድራ |
| 3 | አቶ ገነት ደሴ | ወ | 69 | አርሶ አደር | ውፍታ ዳጢ |
| 4 | አቶ በቃሉ ፈጠነ | ወ | 72 | አረሶ አደር | ውፍታ ዳጢ |
| 5 | ወ/ሮ የመንግስት አካሉ | ሴ | 50 | የቤት እመቤት | ውፍታ ዳጢ |
| 6 | አቶይመኑ መኮነን | ወ | 70 | አርሶ አደር | አጋጋ |
| 7 | አቶ ባንቲገኝ ስሜነህ | ወ | 41 | የዳንግላ ወረዳ ባህልና ተሪዝም ሃላፊ | ዳንግላ 05 ቀበሌ |
| 8 | አቶ አዲሱ አረጋ | ወ | 65 | አርሶ አደር | አጋጋ |

## ሌሎቹ  መረጃ አቀባዮች

| ተ.ቁ | ስም | ፆታ | እድሜ | ስራ | ቀበሌ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወ/ሮ አገው ላንች መንግስቴ | ሴ | 50 | የቤት እመቤት | ውፍታ ዳጢ |
| 2 | አቶዳኛው በላይ | ወ | 65 | ወታደር | አጋጋ |
| 3 | አቶ ምናለ ጣሹ | ወ | 84 | አርሶ አደር | ወንደፋይ |
| 4 | አቶ አስፋው ብሩ | ወ | 70 | አርሶ አደር | ውፍታ ዳጢ |
| 5 | ወጣትካሳየ ፈቃዱ | ወ | 32 | አርሶ አደር | አጋጋ |
| 6 | ወ/ሮ ሙሉ አድማስ | ሴ | 40 | | ወንደፋይ |
| 7 | ቄስ ገበየሁ ታገለ | ወ | 55 | የቤተክርስትያን አገልጋይ ካህን | ወንደፋይ |